ምዕራፍ 5

ዋጋ ያስከፍላሃል!

"ባደካሞች መንገድ ላይ እንቅፋት የነበረው ጥቁር ድንጋይ
በጠንካሮች መንገድ ላይ የመረማመጃ ድንጋይ ይሆናል"
ቶማስ ካርልይል።

ምናልባት ዊልማ ሩዶልፍ የተባለ ስም ሰምታችሁ ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ደግሞ ታሪኳ ዊልማ በተሰኘው የቴሌቪዥን ተንቀሳቃሽ ፊልም የተነገረና ምስሏም በዩናይትድ ስቴትስ የፖስታ ቴምብር ላይ የታየ ከፍተኛ አትሌት መሆንዋን ታውቁ ይሆናል። በእርግጥ፣ ይህች ልዩ ሯጭ፣ አሠልጣኝና የስፖርት ዘጋቢ የሆነች ከፍተኛ እውቅናንና አድናቆትን ያገኘች ሴት ናት፣ ነገር ግን እርሷ ወደዚህ ግብ ለመድረስና ሕልሟን እውን ለማድረግ ምን ያህል ዋጋ እንደከፈለች ታውቃላችሁን?

ዊልማ በታላቅ የኢኮኖሚ ውድቀት ተጽእኖ ውስጥ ይማስን በነበረ ድሀ ቤተሰብ ውስጥ ከሃያ ሁለት ልጆች ሃያኛዋ ሆና ያለ ቀኗ የተወለደች ነበረች። በተጨማሪም ገና በጨቅላ ሕፃንነቷ በቀይ ትኩሳት (ስካርሌት ፊቨር) እና እጥፍ በሆነ የሳምባ ምች የተሰቃየች ከመሆኗም በላይ ከመወለዷ ጀምሮ በልጅነት ልምሻ (ፖሊዮ) ስለተመታች ሕክምና ወደ ምታገኝበት ወደ ጥቁሮች ሆስፒታል በሳምንት ሁለት ጊዜ ሃምሳ ማይል ርቀት በመኪና ትወሰድ ነበር። እንደገናም እናቷ ለዓመታት በቀን አራት ጊዜ እግሮችዋን ማሸት ነበረባት አንድ ጊዜ፣ ዶክተሮች ከቶ ልትራመድ እንደማትችል ነግረዋት ነበር፣ ሆኖም የብረት ማሠሪያ (ብሬስ) ተደርጉላት እስክ ዘጠኝ ዓመት እድሜዋ ድረስ መራመድ ስለቻለች ዶክተሮቹ መሳሳታቸውን ቀስ በቀስ አስመስክረች።

በመጨረሻም ዐሥራ ሁለት ዓመት ሲሆናት በደህና ሁኔታ መራመድ ቻለች። ከአራት ዓመታት በኋላ፣ በዐሥራ ስድስት ዓመት ዕድሜዋ፣ የመጀመሪያውን የኦሊምፒክ ሜዳሊያ አገኘች። እንደገና ከአራት ዓመት በኋላ፣ በ1960 በሮም ኦሊምፒክ በሦስት የስፖርት ዓይነቶች ተሳትፋ ሦስት የወርቅ ሜዳሊያ አገኘችና የዓለም ዐቀፍ ኮከብ ለመሆን በቃች።

ከቶ ለመራመድ አትችይም የተባለችው ትንሿ ልጃገረድ - በዓለም ውስጥ ከማንኛዋም ሴት-በተሻለ ሁኔታ ለመሮጥ በቃች። ነገር ግን እርስዋ ይህን ያደረገችው ያለ ስቃይ፣ ያለ መስዋዕት፣ ያለ ሥነ ሥርዐትና ያለ ዋጋ ክፍያ አይደለም። ምኞቷ ሲፈጸም ለማየት ፈለገች፣ ደግሞም ፈጸመችው፣ ምክንያቱም እጅ ስላልሰጠች ነው።

እጅ የማይሰጡ ሰዎች ለመሆን፣ ዊልማ ሩዶልፍ እንዳደረገችው የተፈጥሮ እንቅፋቶችንና እንደ ቁጣ፣ ይቅርታ ቢስነት፣ የበደለኝነት ስሜትና ፍርሃት የመሳሰሉትን የማይታዩ ጎይሎች አልፈን ወደፊት መንገዝ ያስፈልገናል። በሚቀጥሉት ጥቂት ምዕራፎች ውስጥ ወደ ኋላ የሚጐትታችሁን ማንኛውንም ነገር አልፋችሁ እግዚአብሔር እንድትሆኑ ወደሚፈልጋችሁ ወደ ማንኛውም ሁኔታ እንድትደርሱ እነዚህን ጉዳዮች የምታሸንፉበትን ዘዴ በዝርዝር እጽፍላችኋለሁ። ወደ ግባችሁና ወደ እምቅ ጎይላችሁ እንድትደርሱ አሁን ወደ ውስጥ ግቡ፣ ወደፊት ግፉ፣ አልፋችሁ ሂዱና ዋጋውን ክፈሉ።

አልፎ መሄድ

ሁላችንም በሁኔታዎች ውስጥ አልፈን እንሄዳለን። ብዙ ጊዜ "በአንድ ነገር ውስጥ እያለፍሁ ነው" የሚለውን ዐረፍተ ነገር መናገር ዜና እንደሆነ እናስባለን፣ ነገር ግን ሁኔታውን በትክክል ካየነው በውስጡ ማለፍ መልካም መሆኑን እንገነዘባለን፣ በአንድ በታ አልተቀረቀርንም ማለት ነው። ችግሮች አጋጥመውን ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ቢያንስ ቢያንስ ወደ ፊት እየተንቀሳቀስን ነው።

በኢሳይያስ 43÷2፣ "በውሃ ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፣ ወንዙን ስትሻገረው አያሰጥምህም፣ በእሳት ውስጥ

ስትሄድ አያቃጥልህም፤ ነበልባሉም አይፈጅህም" ይላል። በዚህ ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል ግልጽ ነው፤ በአንዳንድ ነገሮች ውስጥ እናልፋለን። በሕይወታችን መከራዎች ያጋጥሙናል። ያ መጥፎ ዜና አይደለም፤ እርሱ ተጨባጭ ነገር ነው።

እንደገና ልድገመው፦ ሁላችንም በሁኔታዎች ውስጥ እናልፋለን፤ ነገር ግን የምናልፍባቸው ነገሮች ችግርን እንዴት ማሸነፍ እንዳለብን እንድናውቅ የሚያደርጉን ችግሮቹ፤ ተግዳሮቶቹና ሁኔታዎቹ ራሳቸው ናቸው። በመልካሙ ጊዜ ልናድግ ወይም ጠንካሮች ልንሆን አንችልም፤ የምናድገው በችግሮች ውስጥ እጅ ሳንሰጥ አልፈን ስንሄድ ነው።

በሚያዝያ ወር 2007፤ አንድ ታጣቂ በቨርጂኒያ ትምህርት ቤት ተኩስ ከፍቶ ሠላሳ ሦስት ብሩህ፤ ወጣትና ተስፋ የሚጣልባቸውን ተማሪዎችና ራሱን በጭካኔ የገደለበትን ቀን ታስታውሱ ይሆናል። በዚያን ቀን ከተገደሉት ተማሪዎች መካከል አንዷ ኬትሊን ሐማሬን የተባለች፤ ንቁ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ የነበረች ከሁለት ምስኪን ወላጆች የተወለደች ብቸኛ ልጅ ነበረች። የኬትሊን እናት፤ ማሪያን፤ ይህን የመሰለ ከፍተኛ ጉዳት አልፋ ወደፊት ለመቀጠል የሚያስችላትን ጎይልና ቁርጠኝነት ማግኘት ነበረባት።

ከኬትሊን ሞት በኋላ፤ ባለሥልጣናት የእርሷን ላፕቶፕ ኮምፒውተር ለእናቷ ለማሪያንና ለአባቷ ለክሪስ ሰጡአቸው። እነርሱም ኮምፒዩተሩን ሲከፍቱት በኮምፒውተሩ አናት ላይ "እግዚአብሔር ሆይ፤ ዛሬ እኔና አንተ በአንድነት ልንቆጣጠረው የማንችለው ምንም ነገር እንደማይከሰት አውቃለሁ" የሚል ማስታወሻ ተጽፎ አገኙ። ኬትሊን እነዚያን ቃላት በሙሉ ልቧ እንዳመነች እናቷ አወቀች፤ ነገር ግን እርሷ መላዎቿን በሕይወቷ ላይ በደረሰው በዚያ ታላቅ አደጋ ውስጥ እንኳ ለራሷ አላመነቻቸውም።

ከኬትሊን ሞት በኋላ ባሉት ሳምንታትና ወራት፤ እናቷ ማሪያን ጉዳቷን በትዕግስት ለመቀበልና የሕይወቷ ማዕከል የነበረችውን ኬትሊንን አጥታ ለመኖር የምትችልበትን ጥንካሬ ለማግኘት ታገለች።

ስለ መንፈላዊነት የሚናገሩትን መጻሕፍት እያደነች ተመገበችና ለብዙ ዓመታት ያላደረገችውን የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ጀመረች። በሂደቱም ከኬትሊን ኮምፒውተር ላይ ከነበረው ማስታወሻ የተገኙት ቃላት በማሪያን ሀሳቦች ላይ ብቅ ማለታቸውን ቀጠሉ። ነገር ግን ከቨርጂኒያ ትምህርት ቤት ጭፍጨፋ ከአራት ወራት በኋላ እነዚህ ቃላት ለእርሷ በጣም የግል ሆኑላት። ለእርሷ በቀጥታ እንደሚናገሩለት ሆኖ ትሰማቸው ነበር፤ ለራሷም ልታምናቸው ቻለች።

ማሪያን ጋይድ ፓስት በተሰኘው መጽሔት፤ "የኬትሊን በሞት መለየት እኔን ከአሮጌው ዓለም ወደ ዐዲስ አሸጋገረኝ። ይህ ዓለም እኔ እንደዚህ ይሆናሉ ብዬ ከምገምተው በላይ ነገሮች የሚዛበቡበት ዓለም ነው። ነገር ግን በጌታ እርዳታ እኔ ላልፍበት ከምችለው በላይ ምንም ነገር - ፍጹም ምንም ነገር - ሊከሰት አይችልም ነበር" በማለት ጻፈች።

ዛሬም፤ ማሪያንና ክሪስ በአንድ ልጃቸው ሞት ከደረሰባቸው ጉዳት ጋር እየታገሉ ይገኛሉ። ከኬትሊን ሞት በኋላ የነበረው የምስጋና ቀንና የገና በዓል እጅግ አስቸጋሪ ነበር፤ ከኬትሊን ጋር ሊያከብሩአቸው ያልቻሉትን ብዙ የሕይወት ምዕራፎች በሀዘን ያሳልፉአቸው ነበር። ነገር ግን በየቀኑ ጥንካሬን እያገኙ ሲሆን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውም ግንኙነት ስፋትና ጥልቀት አግኝቶአል። ክሪስ በጦር ሠራዊት ውስጥ መጋቢ መሆንን በጥልቀት እያሰበበት ነው፤ ማሪያንም ሌሎችን በስቃይ ሁኔታዎቻቸው ለመደገፍና ለመውደድ የራስዋን ስቃይ ትጠቀምበታለች።

ስቃይና አደጋ የሕይወት አንዱ ክፍል ናቸው። እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ እንደምንሰቃይና መከራ እንደሚያገኘን ይነግረናል፤ ስለዚህ ሥቃዮቻችን እኛን እጅ እንዲያሰጡን በመፍቀድ ፈንታ እነርሱን የምናሸንፍበትን መንገድ መማር ይገባናል። እኔ በኬትሊን ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ላይ የተጻፈውን ማስታወሻ እወደዋለሁ፤ እናንተም የግላችሁ እንድታደርጉት አደፋፍራችኋለሁ፤ "እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔና አንተ በአንድነት ልንቆጣጠረው የማንችለው ምንም ነገር እንደማይከሰት አውቃለሁ" ይላል።

በእድገትና በመከራ መካከል ሚዛናዊ የሆነ አመለካከት ሊኖረን ይገባል፤ ምክንያቱም እድፋት የችግር ቀጥተኛ (አውቶማቲክ) ውጤት ስላልሆነ ነው። ችግሮች በውስጣችን የግድ እድገትን ወይም ጥንካሬን ላያስገኙ ይችላሉ፤ ነገሩ እንደዚህ ቀላል አይደለም። አንዳንድ ሰዎች ችግሮች ሲመጡ ወደ ኋላ ያፈገፍጋሉ፤ ወይም ይፈረካከሳሉ። ማሪያን ሐመራን እንደ ተማረችው ሁሉ፤ እኛም የምናድገው በችግር ውስጥ በእግዚአብሔር መንገድ ስናስብና ስናደርግ ነው። አስቸጋሪ፤ የማይመች ወይም የማያስደስት ነገር በሚሆንበት ጊዜ ትክክለኛ መስሎ የሚታየንን ነገር ስናደርግ መንፈሳዊ እድገት ይኖረናል፤ ጥንካሬንም እናገኛለን። "ትርፍ መኖሩ" ሳይሰማን ለረጅም ጊዜ ትክክለኛውን ነገር በማድረግ ልንቆይ እንችላለን፤ ነገር ግን በታማኝነት ክፀናንና እጅ መስጠትን እምቢ ካልን፤ መልካም ውጤቶች ይመጣሉ። በሚያጋጥሙን ችግሮችና ተግዳሮቶች ውስጥ ካለፍን በኋላ፤ በእነርሱ ውስጥ ስንገባ ከነበርንበት ሁኔታ የተሻልን ሆነን እንወጣለን።

በሕይወታችሁ በሚያጋጥማችሁ በእያንዳንዱ ችግር ውስጥ እስከ መጨረሻው ድረስ አልፎ ለመሄድ ቁርጠኝነት ይኑራችሁ። ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን፤ ወደፊት ለመሄድ አሁኑኑ ውሳኔ አድርጉ። ይህን በማድረጋችሁ እንደምትደሰቱ እኔ አረጋግጥላችኋለሁ።

ቀጥሎ ያለው ጥቅስ በራሴ ሕይወት ባካሄድኋቸው ብዙ ውጊያዎች ድፍረትንና መጽናናትን ሰጥቶኛል፤ እናንተንም እንደሚያደፋፍራችሁ አምናለሁ፦ "ጌታ እግዚአብሔር ኃይሌ፤ የግል ብርታቴና የማይሸነፍ ሠራዊቴ ነው፤ እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርግና እንድራመድ [በሸብር እንድቆም ሳይሆን እንድራመድ] እንዲሁም በከፍታ ስፍራዎቼ [በችግር፤ በስቃይና በኃላፊነት ውስጥ] [መንፈሳዊ] እድገት እንዳሳይ ያደርገኛል!" ይላል (ዕንባቆም 3÷19)።

በምንም ሁኔታ ትክክለኛውን ምርጫ አድርጉ

ከቶ እጅ ላለመስጠት ዋናው ነገር፤ ስትጉዱ፤ ተስፋ ስትቆርጡ፤ ስትበሳጩ፤ ግራ ሲገባችሁ፤ ወይም በተጽእኖ ሥር ስትሆኑ ትክክለኛውን ምርጫ ማድረግ ነው። ትክክለኛው ምርጫ ብዙ

ጊዜ ጠንካራ (hard) ከባዱ ምርጫ ነው። በአስከፊ ጫና ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ፤ ብዙ እንቅፋት የሌለበትን ጉዳና ለመያዝ መፈለጋችን የተለመደ ነው። ነገር ግን እነዚያ አስቸጋሪውን ምርጫ ለማድረግ ራሳችሁን የምታለማምዱባቸው ትክክለኛ ወቅቶች ናቸው። በሕይወት ውስጥ "ትክክለኛ" ውጤቶችን ለማጨድ፤ ትክክለኛውን ለማድረግ በማይለማችሁ ጊዜ እንኳ ትክክለኛውን ነገር ማድረግ ነው። እኔ ይህንን "ወደ ውስጥ መግባትና ወደፊት መግፋት" ብዬ እጠራዋለሁ፤ ይህንን ማድረግን ማወቅ በራሱ ከቶ እጅ የማይሰጥ ሰው ለመሆን በጣም አስፈላጊው ክፍል ነው።

> እድገት ዋጋ አለው፤ ከቶ እጅ የማይሰጥ ሰው መሆንም አንድ ነገር ያስከፍላችኋል።

አያችሁ፤ እድገት ዋጋ አለው፤ ከቶ እጅ የማይሰጥ ሰው መሆንም አንድ ነገር ያስከፍላችኋል። በሕይወት መንገዳችሁ ላይ በቆሙት እንቅፋቶችና ችግሮች አልፋችሁ ለመሄድና መስዋዕት ለመክፈል ፈቃደኞች ካልሆናችሁ ለመሆን ወደምትፈልጉበት ስፍራ ለመድረስ አትችሉም። እንቅፋታችሁ ምናልባት ዝንባሌአችሁ፤ የሁኔታዎች ክምችት፤ ግንኙነታችሁ፤ ካለፈው ጊዜ የመጣ ችግራችሁ፤ አስተሳሰባችሁ ወይም የአእምሮ ዝንባሌአችሁ፤ ስሜታችሁ፤ ወይም መጥፎ ልማዳችሁ ሊሆን ይችላል። ምንም ይሁን ምን፤ በእንቅፋታችሁ ውስጥ ወደፊት መግፋት የምትችሉት እናንተው ናችሁ፤ ማንም ሌላ ሰው ለእናንተ ሊገፋላችሁ አይችልም። ባለፈው ጊዜ ያጋጠሙአችሁን ተግዳሮቶች ለማሸነፍ ሞክራችሁ ይሆናል። ምናልባት እስክትደክሙ፤ እስክትሰላቹ፤ ወይም ተስፋ እስክትቆርጡ ድረስ ሞክራችሁ ሊሆን ይችላል። ይህም ከእግዚአብሔር ትኩስ ኀይልን እንድትቀበሉ አስፈላጊ የሚሆንበትና በተጨማሪ ለአንድ ጊዜ ወደፊት የምትገፉበት ትክክለኛው ወቅት ነው።

በቀጣይነት ወይም በቋሚነት በእግዚአብሔር ላይ የማንደገፍ ከሆነ የምንደክምና እንዲያውም በውሳኔያችን የምናወላውል እንሆናለን። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን በምንጠባበቅበት ጊዜ ኀይላችንን እንደ ንስር እንደምናድስ ይናገራል (ኢሳይያስ 40÷31 ይመ)። እግዚአብሔርን መጠባበቅ ማለት መደረጊ የሚያስፈልገውን ነገር ያደርጋል ብሎ

መጠባበቅ፣ በእርሱ ላይ መደገፍና መተማመን ነው። እኛ ወደፊት ለመግፋት የግል ውሳኔ ማድረግ አለብን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲረዳን በእርሱ ላይ ካልተደገፍን በስተቀር በማንኛውም ነገር ከቶ ስኬትን ለማግኘት አንችልም።

መግፋት ለሚለው ቃል ከምጠቀምባቸው ትርጉሞች አንዱ፤ "በአንድ ነገር ላይ የማያቋርጥ ጎይል ወይም ጫና ማሳረፍ" የሚል ነው። ብዙ ጊዜ "የሚገፋችሁን ጫና በመቃወም እርሱን መግፋት አለባችሁ!" እላለሁ። አንድ ነገር የሚገፋችሁ ከሆነ፣ እናንተ ከነገሩ በበለጠ ጎይል ለመግፋት ቆርጣችሁ መነሣት አለባችሁ፤ ምክንያቱም ይህ ጥረት ከሌለ እውነተኛ ረብ ያለው፣ ወይም ልታገኙት የሚገባ ረብ ያለው ነገር በሕይወት ውስጥ ሊገኝ አይችልም። አንዳንድ ጊዜ፣ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎችን ገፍታችሁ ማለፍ ይኖርባችኋል። ለምሳሌ፣ ሕልማችሁ በስተማችሁ በአንድ አካባቢ የንግድ ሥራ ለመክፈት ነው እንበል፤ ከዚያም የዘጉ ቦርድ እናንተ ሕንፃ ለመገንባት ያቀረባችሁትን ጥያቄ በተደጋጋሚ ውድቅ ያደርግባችኋል። ወይም ሕልማችሁ ኮሌጅ ለመግባት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ለነፃ የትምህርት ዕድል ያቀረባችሁት ጥያቄ በሙሉ ውድቅ ይደረግባችኋል።

እኔ በሕፃንነቱ ወሲባዊ፣ አእምሮአዊና ስሜታዊ ጥቃት ደርሶብኛል። በዚህ ምክንያት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን እንደ ጨረስሁ ወዲያውኑ ከቤቱ ወጥቼ ራሴን ለመርዳት መጀመር ያስፈልገኝ ነበር። ስለዚህ ወደ ኮሌጅ ለመግባት አልቻልሁም ነበር። የሁለተኛ ደረጃ አስተማሪዎቼ የጽሑፍ ችሎታ እንዳለኝ ስለተገነዘቡ ወደ ኮሌጅ እንድገባ በብርቱ አሳሰቡኝ፤ ነገር ግን ይህን ለማድረግ አልቻልሁም።

ይሁን እንጂ፣ ይህ እግዚአብሔርን ሊያቆመው አልቻለም! እኔ ለማንያ ያህል መጽሐፎችን ጽፌአለሁ፤ ነገር ግን ይህ እንዴት እንደሚደረግ ለመማር ከቶ ወደ ትምህርት ቤት አልሄድኩም። ደግሞም በመጻፌ በርከት ያሉ የክብር ዲግሪዎችንና ሁለት የራሴን ዲግሪዎች አግኝቼአለሁ። "በተለመደው" ሁኔታ ወደ ኮሌጅ ለመግባት አልቻልሁም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እርሱ የፈለገውን ነገር እንድሠራ

ለመርዳት ሌላ መንገድ ነበረው። እኛ እጅ መስጠትን እምቢ በምንልበት ጊዜ እርሱ የሚያደርገውን ነገር በማስበበት ጊዜ እደነቃለሁ። ከእርሱ ጋር፣ ሁሉ ነገር ይቻላል!

በዚህ ክፍል ውስጥ የገለጽኋቸው ሁኔታዎችና ተግዳሮቶች እውነተኛ ናቸው፤ እነርሱም መፍትሄ ሊያገኙ የሚገባቸው ናቸው። ነገር ግን እኔ የምጨነቀው ስለ ራሳቸው ስለ እንቅፋቶቹ ሳይሆን፣ በይበልጥ የምጨነቀው እናንተ ለእንቅፋቶቹ ስለምትሰጡት ምላሽ ነው፤ ምክንያቱም እናንተ አስተሳሰባችሁንና ዝንባሌአችሁን ካስተካከላችሁና እጅ መስጠትን እምቢ ካላችሁ በመጨረሻው የሚያስፈልጋችሁን መሻሻል ስለምታገኙ ነው። እናንተ የፈለጋችሁትን ነገር ያንኑ በትክክል ታገኛላችሁ የሚል ተስፋ ልሰጣችሁ አልችልም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የጠየቃችሁትን ነገር የማይሰጣችሁ ከሆነ እንግዲያው ከዚያ የተሻለ ነገር ይሰጣችኋል። የእርሱ መንገድ ከመንገዳችን በላይ ነው፤ አሳቡም ከአሳባችን ከእኛ አሳብ በላይ ነው። ስለ ሕይወታችሁ በምታስቡበትና የእድገትን ዋጋ ለመክፈል ዐዲስ ውሳኔ በምታደርጉበት ጊዜ፣ አልፋችኋቸው ወደፊት መሄድ የሚገባችሁን አንዳንድ ነገሮች በአእምሮአችሁ ያዙ፤

* ውድቀት
* ፍርሃት
* ብስጭት
* መገፋት
* ክደት
* ምቀኝነት
* መደናገጥ
* መዘግየት
* ጥቃት
* በራስ ማዘን
* መሰናክሎች
* የሰዎች ግላዊ አመለካከት
* ተስፋ መቁረጥ
* ድካምና መዝለፍለፍ

* መደበት
* ቁጣ
* በደለኝነት
* ሃፍረት
* ጉዳት

በእርግጥ፣ ገፍታችሁ ልታልፉአቸው የሚገባችሁ ሌሎች ጎይሎችና ስሜቶች አሉ፤ ነገር ግን እነዚህ እንቅፋቶች ሲገጥሙአችሁ እንቅፋቶች መሆናቸውን አውቃችሁ ልታሸንፉአቸው የሚገባችሁ መሆኑን እንድትገነዘቡ ይህ ዝርዝር ይረዳችኋል። እንቅፋቶቹ በሕይወታችሁ ሲገጥሙአችሁ ልብ አድርጉ፤ ወደ ውስጥ ግቡ፤ ወደፊት ግፉ።

ፍሬውን ፈልጉ።

አብዛኞቻችን እንደምንስማማበት እርግጠኛ የሆንኩበት ቃል በዕብራውያን 12÷11 ተጽፏል፤ "ቅጣት ሁሉ በወቅቱ የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፤ በኋላ ግን ለለመዱት ሰዎች የጽድቅና የሰላም ፍሬ [ጽድቅ የሚገኝበት የፍሬ መከር] ያስገኝላቸዋል" ይላል።

በመቀጣት ደስ የሚላቸውን ብዙ ሰዎች አላውቅም። ራሳችንን ማሠልጠን (መቈጣጠር) ልናደርገው የሚገባን ነገር ነው፤ ምክንያቱም ለጥቅማችን እንደሆነና ልናደርገውም እንደሚገባ ስለምናውቅ ነው፤ ነገር ግን "አስደሳች" ብለን የምንጠራው ነገር አይደለም። ምንም እንኳ ከባድ ቢሆንም፤ ቅጣት መልካም ብድራት አለው። እኛ ጤናማ አመጋገብ ቢኖረንና የሰውነት ልምምድ በማድረግ ራሳችንን ብናሠለጥን፤ ጥንካሬን እናገኝና ለሰውነታችን ተገቢውን የክብደት መጠን ይዘን ለመቆየት እንችላለን። የገንዘብ ወጪአችን ከገቢአችን ያነሰ እንዲሆን ራሳችንን ብናሠለጥን፤ ጥሩ የቁጠባ ሂሳብ ይኖረንና ከዕዳ ጫና ነፃ እንሆናለን። ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ለማድረግ፤ ለመጸለይና ቃሉን ለማጥናት ራሳችንን ብናሠለጥን፤ ከእርሱ ጋር የመቀራረብን ብድራት እናገኛለን።

በርከት ላሉ ዓመታት በቤቱ ውስጥ በታማኝነት ትረዳኝ ስለነበረች ስለ አንዲት ሴት አስባለሁ። እርሷም "የአንቺን ልብሶች ለመልበስ አነስ ብል ኖሮ አንዴት ጥሩ ነበር!" ትለኝ ነበር። ብዙ ጊዜ ለሰዎች ልብስን እንደምሰጥ ታውቅ ነበር፤ ነገር ግን በዚያን ጊዜ የእኔ ልብሶች ለእርሷ ጠባብ (አነስተኞች) ነበሩ። ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ "አይ፤ የአንቺን ልብሶች ለመልበስ ብችል እንዴት ጥሩ ነበር!" ትለኝ ነበር።

በመጨረሻ አንድ ቀን ውሳኔ አደረገችና እንዲህ አለች፦ "የአንቺን ልብሶች አለብሳለሁ። አንቺ ልብሶችን ለሰዎች ስትሰጪ እኔ መጀመሪያ አሰለፋለሁ፤ ምክንያቱም እኔ እዚሁ በአንቺ ቤት ስለሆንኩ ነው!" አለች።

ይህች ሴት ዝም ብላ በመቀመጥ ትንሽ መሆንን አልተመኘችም፤ ወይም እንደ ፈለገች መብላትን አልቀጠለችም። የአመጋገብ ልምዷን ለወጠችና ከበፊቱ ይልቅ ጤናማ የሆነ የኑሮ ዘይቤ አዳበረች፤ ከዚያም ለእርሷ ተገቢ ያልሆኑ ምግቦችን የመተውን ሥርዐት እየጠበቀች ወደፊት ቀጠለች። እርሷም እያደር እያነሰች፤ እያነሰች፤ እያነሰች፤ እያነሰችና እያነሰች መሄዷን ተመለከትሁ። በሚቀጥለው ዓመት ሃያ ሶስት ኪሎ ግራም ክብደት ቀነሰችና የእኔን ልብሶች ለመልበስ ቻለች። በመጨረሻም እርሷ ብዙ ልብሶችን ከኔ አገኘች፤ ምክንያቱም እርሷ የተናገረችው ልክ ነበር። ልብሶቹን ለመስጠት ወደ ሌላ ስፍራ በመኪና ጭነን ከመውሰድ ይልቅ በዚያው በቤቱ ውስጥ ላለችው ለእርሷ መስጠት ቀላል ነበር። በዐሥራ ሁለት ወራት ውስጥ ሃያ ሶስት ኪሎ ግራም ክብደት መቀነስ ሥነ ሥርዐትን (ሥልጠናን) የሚጠይቅ ነበር፤ ደግሞም ተግባሩ ቀላል ወይም አስደሳች ነገር አልነበረም። ነገር ግን የእርሷ ሥነ-ሥርዐት መልካም ብድራትን አገኘና በሕይወቷ ፍላጐቷን የመፈጸም ደስታን አስገኘላት።

እንደገና ትኩረታችሁን ወደ ዕብራውያን 12÷11 እንድታደርጉ ልጋብዛችሁ፤ "ቅጣት ሁሉ በወቅቱ ... ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፤ በኋላ ግን ..."። እኛ የምንኖረው ለጊዜው ነው፤ ወይም እኛ ያለን የአሁኑ ብቻ ነው የሚለውን ውሸት መቀበል የለብንም። እኛ

የወደፊቱንም ማሰብ አለብን፤ ስለዚህ አንድ ዐይናችንን "በወደፊቱ" "በሚመጡት ጊዜያት" ላይ አድርገን መኖር ያስፈልገናል። ለአሁኑ የምናስበውን ያህል፣ ወይም ከዚያ በላይ፣ ለወደፊቱ ማሰብን መጀመር አለብን።

በሰኔ ወር የመዋኛ ልብሳችሁን ለመልበስ እንድትችሉ ቀጠን ለማለት ከፈለጋችሁ ክረምት ከመግባቱ በፊት ጤናማ አመጋገብና የሰውነት ልምምድ መጀመር ያስፈልጋችኋል። በሚቀጥለው ዓመት አዲስ መኪና እንዲኖራችሁ ከፈለጋችሁ አሁኑኑ ከዕዳ ነፃ ለመሆን መታገል ያስፈልጋችኋል። በጥሩ፣ በንጹህና ሥርዐት ባለው ቤት የመኖር ሕልም ካላችሁ ዕቃዎቹን ሁሉ አውጥታችሁ ማጽዳት ያስፈልጋችኋል!

በሥነ-ሥርዐት ውስጥ በምትሆኑበት ጊዜ ሥነ-ሥርዐት ለሥጋችሁ አስደሳች ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን ለነፍሳችሁ ከፍተኛ የእርካታ ስሜትን ይሰጣችኋል- ይህም እርካታ መልካም ምርጫ ማድረጋችሁን ከመገንዘብ የሚመጣ ነው። አሁን የሥነ-ሥርዐትን ዋጋ ከከፈላችሁ፣ በኋላ ላይ በመልካም ብድራት ትደሰታላችሁ። አሁን ትክክል የሆነውን ነገር ለማድረግ ዋጋ ካልከፈላችሁ፣ በኋላ ላይ ሥነ-ሥርዐት የሌለውን ሕይወት የመኖርን ውጤት ታገኛላችሁ። ወይ አሁን ትከፍላላችሁ፣ ወይም በኋላ ትከፍላላችሁ፤ ነገር ግን በአንድ ወቅት፣ ያደረጋችሁትን ምርጫ ውጤት ታጭዳላችሁ። ዝም ብለን ሕይወታችን የተሰየ ቢሆን ኖሮ እያልን መመኘት በቂ አይደለም፤ ስንፍናን፣ የሥጋ ምኞትንና መጥፎ ዝንባሌን አልፈን በኋላ ላይ መልካም ፍሬ በሚያስገኝልን ሥነ-ሥርዐት ጉዳይ እጅ መስጠትን እምቢ ማለት ያስፈልጋችኋል።

ቀጣይነት ይኑራችሁ

በክብደቱ ላይ አራት ተኩል ኪሎ ግራም የጨመርሁበትንና እርሱን ለመቀነስ የተቻለኝን ሁሉ ለማድረግ የሞከርሁበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። ልብሶቼ ሁሉ ጠበቡኝ፣ በጣም ተቸገርሁ፤ ስለዚህ በፍጥነት ክብደቴን ለመቀነስ ፈለግሁ። ለጥቂት ቀናት ምንም ቅባት

ያለው ምግብ አልበላሁም። አመጋገቡም አልሠራ ሲለኝ ፕሮቲን ብቻ ተመገብሁ። በፕሮቲኑም ብቻ ሳይሳካልኝ ሲቀር ከጥቂት ቀናት በኋላ በቀን ዘጠኝ መቶ ካሎሪ (ከምግብ የሚገኘውን የሰውነት ጉልበት መጠን መለኪያ) ብቻ ለመመገብ ወሰንሁ። ምንም ነገር ሳይሠራልኝ ሲቀርና ተጨማሪ ክብደቴን አሁንም መቀነስ ሲያቅተኝ ሌላ ነገር መከርሁና በመጨረሻው የምግብ መዋሃድ እንደተመሰቃቀለና የውስጥ ማዕድኖችም (ሆርሞንስ) ሚዛናቸውን እንደሳቱ ተገነዘብሁ። እኔም ልትገምቱት እንደምትችሉት በጣም ተበሳጨሁ።

አንድ ቀን እግዚአብሔር ቀላል የሆነ ነገር ተናገረኝ፤ ነገር ግን እርሱ ከቶ የማልረሳው ነገር ነበር:- ቁልፉ ቀጣይነት ነው አለኝ። ከዚያ ቀን ጀምሮ እነዚያ ቃላት እውነት መሆናቸውን ተረዳሁ። በሕይወታችን በማንኛውም አቅጣጫ እድገትን ለማግኘት ከፈለግን፣ ለተወሰነ ጊዜ ትክክለኛውን ነገር እያደረግን መቀየት ያስፈልገናል። ቀጣይነት ማለትም ይኸው ነው።

የእኔን አራት ተኩል ኪሎ ግራም ተጨማሪ ክብደት በተመለከተ፤ የወረት አመጋገብ አላስፈለገኝም፤ በመደበኛ ሁኔታ እንደ ሕይወት ዘይቤ አድርጌ ጤናማ የሆነና መጠኑን የጠበቀ ምግብ መመገብ ነበረብኝ። ይህንን አውቄ ነበር፤ ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሐረግ ትዝ እስኪለኝ ድረስ ትግሌን ቀጠልሁ፤ "ከዕለት እንጀራዬ በላይ" የሚል ነበር (ኢዮብ 23÷12)። እግዚአብሔር በዚያ ቃል ተናገረኝ፤ *አስፈላጊ ካልሆነ አትብዙ* አለኝ። ይህ ለእኔ ሠራልኝ። በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ውስጥ ያንን አራት ተኩል ኪሎ ግራም ቀነስሁት፤ ከዚያም ወዲህ አልጨመርሁትም።

በእኔ ቤት ውስጥ ትሠራ የነበረችው ሴት፤ እንዲሁም እኔ ከክብደት ጋር ያደረግሁት ውጊያ ታሪኮች በግልጽ የሚናገሩት ነጥብ፤ ማንኛችንም ብንሆን አሁን የምንፈልገውን ማንኛውንም ነገርና ወደፊትም የምንፈልገውን ማንኛውንም ነገር ልናገኝ እንደማንችል ነው። ልብ አድርጉ "ቅጣት ሁሉ በወቅቱ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም"።

እስኪ ልጠይቃችሁ፤ አሁን ያላችሁበት ሁኔታ ደስ የማይላችሁ ከሆነ፣ ለመለወጥ ጥረት ታደርጋላችሁን? በሚቀጥለው ዓመት አሁን ባላችሁበት ሁኔታ ለመገኘት ትፈልጋላችሁን? ወይስ አንድ የተለየ ነገር ትፈልጋላችሁ? አንድ የተለየ ነገር ለማግኘት ከፈለጋችሁ፣ የፈለጋችሁትን ነገር በዚያኛው መጨረሻ እንድታገኙ በአሁኑ መጨረሻ ዋጋውን ክፈሉ። የዚህኛውን ዓመት ጥቂቱን ወደሚቀጥለው ዓመት ማባችሁ ለመሸጋገር ልትጠቀመበት ይገባችኋል። ወደፊት በምትንቀሳቀሱበት ጊዜ፣ ከባድ ምርጫዎችን ማድረግ ይኖርባችኋል፤ ደግሞም አንዳንድ አስቸጋሪ መስቀለኛ መንገዶችን ታገኛላችሁ። ወደ እነዚያ ስፍራዎች በምትደርሱበት ጊዜ፣ ወይ በፊት ወደነበራችሁበት ስፍራ ትመለሳላችሁ፤ ወይም ደግሞ ወደፊት ትገፋላችሁ። ወደፊት የምትገፉ ከሆነ፣ የናፈቃችሁትን ድል በኋላ ታገኛላችሁ።

የእኔ ባለቤት በጣም ጤነኛ ነው፤ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ በአካል ከእኔ የተሻለ ስሜት አለው፤ ምክንያቱም እርሱ የበለጠ ጥንካሬና ጎይል ስላለው ነው። ለዴቭ ጤንነትና ጥንካሬ ምክንያት የሆነው ከዐሥራ ስድስት ዓመት እድሜው ጀምሮ በየሦስት ቀኑ ለአካላዊ ደህንነቱ የራሱን ጥረት ሲያደርግ ቆይቶአል። የእርሱ ቆዳ ከእርሱ በሦላሳ ዓመት ያነሰ ሰውን ቆዳ ይመስላል።

አንድ ጊዜ ወደ እርሱ እየተመለከትሁ የተጨማደደ፣ የጐደጐደ ወይም ያበጠ ስፍራ ባይኖርብኝ ኖሮ እያልሁ የተመኘሁበትን ወቅት አስታውሳለሁ፤ ነገር ግን መመኘት ከቶ ሊረዳኝ አልቻለም። በዴቭ መቅናትም ሊረዳኝ አልቻለም። እኔ ራሴ ልምምድ ማድረግ ነበረብኝ! በትጋትና በቀጣይነት ክትትል ካደረግሁ በኋላ፣ አሁን የበፊቱን ያህል የጐደጐደ ወይም ያበጠ ቆዳ የለኝም። ዋጋውን ከፈልሁና የምፈልገውን አገኘሁ!

በሕይወቱ አብዛኛውን ጊዜ፣ ልምምድ ለማድረግ በምሞክርበት ጊዜ ራሴን የምጐዳ ይመስል ነበር፤ ስለዚህ ያ ልምምዱን ላለማድረግ ሰበብ ሆነልኝ። ክብደት ለማንሣት ሞክርሁና ክርኔን ጐዳሁት። ቁጭ ብድግ ማለት ስሞክር ጀርባዬን ጐዳሁት። አሁን የምሠራው በትክክል እንዬት ክብደት ማንሣትና ልምምድን ማድረግ እንዳለብኝ ካስተማረኝ

አሠልጣኝ ጋር ነው። አሁን በሳምንት ሦስት ቀን እሠራለሁ፤ ደግሞም አሁን ራሴን አልጐዳም።

ዴቭ መልካም ስሜት እንዲኖረው ለረጅም ጊዜ ዋጋ ሲከፍል ቆይቶአል። እርሱ ከዓመታት በፊት ስለጀመረ፣ እኔ ያለፍሁበት ጉዳት አላገኘውም። እኔ አሁን ዋጋ እየከፈልሁ ነው፤ ደግሞም እኔ ምንም እንኳ ከዴቭ ወደ ኋላ የቀረሁ ብሆንም ልፋቱ ከንቱ አይደለም። አሁን ከሠላሳ ዓመት በፊት ይሰማኝ ከነበረው ስሜት የተሻለ ይሰማኛል፤ ደግሞም ልምምድ ማድረግንና ራሴን መንከባከብን ስቀጥል ቀስ በቀስ እያደር የተሻለ ስሜት እንደሚኖረኝ አጠብቃለሁ።

እኔ የተጠቀምሁበት ሌላ ሰበብ ሥራ ይበዛብኛል የሚለው ነው። ነገር ግን አንድን ነገር ለማድረግ በእውነት ከፈለግን፣ እርሱን ለማድረግ መንገድ እንደምናገኝ በመጨረሻ ተገንዝቤአለሁ። ጤናማ ለመሆን ሥራ የሚበዛብን ከሆነ፣ እንግዲያው ሕይወታችን ሚዛናዊ አይደለም ማለት ነው፤ ስለዚህ አንዳንድ ለውጦች ማድረግ ያስፈልገናል። አገልጋይ እንደመሆኔ መጠን ሰዎችን የመርዳት ሥራ ይበዛብኛል፤ ይህንንም ለማድረግ መስዋዕት ማድረግ እንዳለብኝ ተስማኝ። ነገር ግን ራሴን ለመጠበቅ ጊዜ ካልወሰድሁ፣ ሌላ ማንንም ሰው ለመርዳት እንደማልችል ተገነዘብሁ። ራሳችሁን ከምትንከባከቧቸው ሰዎች ዝርዝር መጨረሻ የምታደርጉ ከሆነ፣ ይህ መንፈሳዊነት አይደለም፤ እንደ እውነቱ ከሆነ እርሱ ሞኝነት ነው።

በከፍተኛ ደረጃ መሻሻል በሚያስፈልገው ግንኙነት ላይ አንድ ነገር ኢንቬስት ለማድረግ ትፈልጋላችሁን? ዝም ብላችሁ ሌላው ሰው እንዲለወጥ የምትፈለጉ ከሆነ፣ የምትፈልጉት ለውጥ ላይመጣ ይችላል። ለእርቁ የመጀመሪያውን እርምጃ መውሰድ ያለባችሁ እናንተ ልትሆኑ ትችላላችሁ። የእኔ የትዳር ግንኙነት የእኔን ፍላጐት የማያሟላ መሆኑ የተሰማኝን ጊዜ አስታውሳለሁ። ዴቭ እኔን ለማስደሰት ሊያደርግ የሚገባውን ነገር ሁሉ አስብ ነበር፤ ነገር ግን ምንም የተለወጠ ነገር አልነበረም። እንዲያውም ስለዚህ ጉዳይ ጸለይሁበት፤ ምንም ነገር አልተለወጠም። ነገር ግን አንድ ቀን እግዚአብሔር ለልቤ ተናገረኝ፣ እኔ ዴቭን ብዙ ጊዜ በማመስገን

ብጀምር ለውጥ ለማየት እንደምችል ገለጸልኝ። ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ አስቸጋሪ ነበር፤ ምክንያቱም ዲቭ ለእኔ አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ አለበት ብዬ ስለአሰብሁ ነው፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ታዘዝሁና አስደናቂ ለውጦችን አየሁ። ዲቭም ለእኔ እንዲያደርግልኝ የፈለግኋቸውን ነገሮች ለማድረግ ብዙ ጊዜ አልፈጀም። እኔ በመጀመሪያ እርምጃ መውሰድ ነበረብኝ፤ ከዚያም በኋላ ውጤቶችን አየሁ።

እናንተም እንዲለወጥ የምትፈልጉት ነገር ምንም ይሁን ምን፣ ወይ አሁን ስቃዩን አልፋችሁ ወደ ፊት በመግፋት ትክክለኛውን ነገር ታደርጋላችሁ ወይም ደግሞ ከሠላሳ ዓመት በኋላ አሁን ባላችሁበት ስፍራ ትቀራላችሁ ወይም ምናልባት ከዚህ በባሰ ሁኔታ ትገኛላችሁ። እግዚአብሔር መልካም አምላክ ነው፤ እርሱ ለሕይወታችሁ እጅግ ታላቅ እቅድ አለው፤ ነገር ግን እናንተ ለቃሉ የመታዘዝን ዋጋ መክፈል አለባችሁ። ዛሬ ዋጋውን መክፈል እንድትጀምሩና ዐይናችሁን ነቅ በምታጭዱት የረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ እንድታደርጉ አደፋፍራችኋለሁ።

ከቶ አትቀመጡ

ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ችላ ብለን የምናልፈውን ጥቅስ ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ፤ እርሱም ኦሪት ዘፍጥረት 11÷31 ነው፤ "ታራ ልጁን አብራምን፣ ሐራን የወለደውን የልጅ ልጁን ሎጥን፣ እንዲሁም የአብራምን ሚስት ምራቱን ሣራን ይዞ ወደ ከነዓን ለመሄድ በከለዳውያን ምድር ከምትገኘው ከዑር አብረው ወጡ፤ *ነገር ግን ካራን በደረሱ ጊዜ በዚያ ተቀመጡ*" ይላል (አጽንኦቱ የኔ ነው)። እናንተም ስለ አብራም፣ ስለ ሣራና ስለ ሎጥ ታውቁ ይሆናል፤ ነገር ግን ታራ ስለተባለው ስለዚህ ሰው ሰምታችሁ አታውቁም ይሆናል።

እኔ የአብራም አባት፣ ታራ፣ እግዚአብሔር በሰጠው እድል አልተጠቀመበትም ብዬ አምናለሁ። እግዚአብሔር፣ ታራን ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን ዘልቆ እንዲሄድ ፈልጕት እንደነበረ አምናለሁ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አጽንኦት የተሰጣቸው ቃላት ተመልከቱ፤ "ነገር ግን ካራን በደረሱ ጊዜ በዚያ ተቀመጡ"

ይላል። በሌላ አነጋገር፣ ታራ በአጭሩ ቀረ። ከዑር እስከ ከነዓን ድረስ እንዲሄድ ተፈልጕ ነበር፤ ነገር ግን ካራን በደረሰ ጊዜ እዚያው ቀረ። እርሱና ቤተሰቡ ከአንድ ስፍራ ጉዞአቸውን ጀመሩ፤ ወደ ሌላ ስፍራ አመሩና ወደ ግባቸው ሳይደርሱ ጉዞአቸው አስቸጋሪ ስለሆነ በዚያ ተቀመጡ። እግዚአብሔር ካቀደላቸው ነገር በጣም ባነሰ ሁኔታ አርፈው ተቀመጡ፤ ምክንያቱም በችግር ውስጥ አልፈው ወደፊት መግፋት ስላልፈለጉ ነው።

እኔ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሚያደርገው ከአብራም አባት ጋር ሊሆን ይችል ነበር ብዬ አምናለሁ። እግዚአብሔር አንዲሄድ ነገረው፤ እርሱ ግን ቆመ፤ በዚያው ተቀመጠ። አብራም እጅግ አስደናቂ በረከትን ተቀበለ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ይህንን ለአባቱም አቅርቦለት ነበር ብዬ አምናለሁ። አባቱ ይህን ሊቀበል ወደሚችልበት ስፍራ ከመድረሱ በፊት ሁሉንም ነገር ተወ።

ዛሬ እናንተ እግዚአብሔር ካቀደላችሁ መልካም ነገር ባነሰ ሁኔታ አርፋችሁ እንዳትቀመጡ አበረታታችኋለሁ። ሌላው ሰው እንዴት አንድ ነገር ለማግኘት ቻለ ብላችሁ አትደነቁ፤ እናንተም ተመሳሳይ እድል እንደነበራችሁና ነገር ግን ችላ ብላችሁ እንዳለፋችሁት ተረዱ።

ዘፍጥረት 11 ውስጥ ቀጥላችሁ ብታነቡ "ታራ 205 ዓመት ኖሮ በካራን ሞተ" ይላል (ቁጥር 32)። በተቀመጠበት ስፍራ ሞተ። እኔም ብዙ ሰዎች በአንድ ስፍራ ይቀመጡና በዚያው ይሞታሉ ብዬ አስባለሁ። በአካል ላይሞቱ ይችላሉ፤ ነገር ግን ሕልማቸው ይሞታል፤ ራዕያቸው ይሞታል፤ የጋለ ፍላጕታቸው ይሞታል፤ ቅንዓታቸው ይሞታል። ለሕይወት ያላቸው ጉጉት ይሞታል። ለምን? ምክንያቱም እጅ ስለሰጡና እግዚአብሔር ወደ አቀደላቸው መልካም ነገር ገፍተው ስላልሄዱ ነው። የሚገጥማቸውን መከራ አልፈለጉትም፤ ነገር ግን ከዚያ ወደ ከፋ ነገር ውስጥ ገቡ - ሥቃዩም የብስጭትና ግብን የማጣት ነው።

በሕይወት ጉዞ ውስጥ በምትሆኑበት ጊዜ የተለያየ ዐይነት መከራና ችግር ይገጥማችኋል። የትኛውን ዐይነት መከራ እንደምትፈልጉ መምረጥ ይኖርባችኋል - ወደፊት የመግፋትን መከራ፣ ወይስ እጅ የመስጠትን መከራ? እኔ ግን ወደፊት ባለመግፋታችሁ ምክንያት እግዚአብሔርን ማጣታችሁን በውስጣችሁ ከምትገነዘቡበት ካልተሟላና ካልረካ ሕይወት የከፋ መከራ የለም ብዬ አምናለሁ። እናንተ እንደዚህ አትሁኑ። አሁኑኑ ከእርሱ ጋር እስከ መጨረሻው ለመሄድና የተግዳሮት ወቅቶችን አልፋችሁ ወደፊት ለመግፋት ወስኑ።

በዘፍጥረት 12 ውስጥ የቀረውን ታሪክ እናነባለን፤ "እግዚአብሔር አብራምን [በካራን] እንዲህ አለው፤ [ለራስህ ጥቅም] አገርህን፣ ወገንህንና የአባትህን ቤት ትተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ" (ቁ.1)። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር አብራምን እጅግ አስቸጋሪ የሆነ ነገር ይጠይቀዋል፤ ነገር ግን ደግሞ ብድራትን እንደሚቀበል ተስፋ ይሰጠዋል።

እኔም በዛሬው ቋንቋ እግዚአብሔር ለአብራም እንዲህ የሚለው ይመስለኛል፤ "እኔ የምጠይቅህ ነገር ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ። ከቤተሰብህ ጋር ትስስር እንዳለህ አውቃለሁ። ብቸኛ እንደምትሆንም አውቃለሁ። ከለመዱት ከማንኛውም ነገር ተለይቶ ጓዝን መሄድ አስቸጋሪ እንደሆነ አውቃለሁ። የብቸኝነት እንደምታሳልፍ አውቃለሁ። ሰዎች እንደማይረዱልህ አውቃለሁ። እነርሱ ስለ አንተ መጥፎ እንደሚናገሩ፣ እንደሚፈርዱብህና እንደሚተቹህ አውቃለሁ። ስለዚህ እኔ ለአንተ የማደርግልህን ልንገርህ፦ 'ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤ ደግሞም [ብዙ በሆነ ሞገስ] እባርክሃለሁ፤ ስምህን ገናና አደርገዋለሁ [መልካም ነገር በማካፈል ለሌሎች በረከት ትሆናለህ' " (ቁ.2)። ሰዎች መጥተው እ ቢባርኩት፣ በመባረካቸው ብቻ እነርሱ ራሳቸው እንደሚባረኩ በመስጠት እግዚአብሔር አብራምን እስከዚህ ድረስ ባረከው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ከባድ ትእዛዝ የሰጠበትን ብዙ ስፍራ እናገኛለን፤ ነገር ግን እርሱ ሁልጊዜ የመልካም ብድራት ተስፋን ይዞ የሚመጣ ነው እግዚአብሔር ወሳጅ ሳይሆን ሰጪ ነው። እርሱ በመጨረሻው ለእኛ ጥቅም ካልሆነ በስተቀር ምንም ነገር እንድናደርግ ፈጽሞ አያዘንም። እኔ ላረጋግጥላችሁ፤ እግዚአብሔር እናንተ እንድታደርጉት የሚጠይቃችሁ ማንኛውም ነገር፣ ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን፣ እርሱ የሚጠይቃችሁ ለእናንተ አንድ ታላቅ ነገር ስለ አሰበላችሁ ነው፤ ነገር ግን ያንን ከባድ ስፍራ አልፋችሁ ካልሄዳችሁ በስተቀር አታገኙትም። ዋጋውን ከፈሉ እንጂ ከቶ እጅ አትስጡ። ለድል የሚከፈለው ዋጋ አይበዛበትም። ሰዎች ሕልውናቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ብቻ እንዲከፍሉት የሚጠየቁትን መስዋዕት ሳስበው በጣም ያሳዝነኛል። የአንድ ወጣት ታሪክ በአእምሮዬ ውስጥ አለ። በየካቲት 2003 አሮን ራልስቶን የተባለ ብዙ ተሞክሮ ያለውና የነቃ ሠራተኛ በስባድ የበረዶ ናዳ (መንሸራተት) ተይዞ ለጥቂት ከሞት ተረፈ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ናዳው ራልስቶንን እስከ አንገቱ ድረስ ሲሸፍነው በበረዶው ላይ ይንሸራተት የነበረውን ጓደኛውን ሙሉ በሙሉ ቀበረው። ራልስቶን በከፍተኛ ክህሎቱና ጥንካሬው ራሱንና ጓደኛውን በደህና ሁኔታ ሊያወጣ ቻለ።

> እግዚአብሔር እናንተ እንድታደርጉት የሚጠይቃችሁ ማንኛውም ነገር፣ ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን፣ እርሱ የሚጠይቃችሁ ለእናንተ አንድ ታላቅ ነገር ስለ አሰበላችሁ ነው።

ነገር ግን በዚያ ዓመት ይህን የመሰለ ከፍተኛ የማዳን ተግባር ለራልስቶን የመጀመሪያው ተግባር አልነበረም። ከሦስት ወራት በኋላ በኡታህ ብሔራዊ መናፈሻ ብቻውን በእግሩ ሲሄድ ራልስቶን በሕይወትና በሞት መካከል ወደቀ፤ ይህም ሁኔታ እርሱ በሕይወት ይኖር ዘንድ የእርሱን አስቸኳይ ውሳኔና ከፍተኛ እርምጃ መውሰድን የሚጠይቅ ነበር።

ራልስቶን ከአስፋልቱ መንገድ የብዙ ማይል እርቀት ባለው በበረሃማው መሬት ሥር የአንድ መቶ ጫማ እርቀት ባለው ጉድጓድ ውስጥ ገባ፤ አንድ ክንዱም በዓለቻማው ግድግዳ ላይ 370 ኪሎ ግራም

በሚመዝን ቋጥኝ ውስጥ ተቀረቀረ። ምንም እንኳ ከፍተኛ መከራ ቢያደርግ ቋጥኙ ሊንቀሳቀስ አልቻለም። ወዲያውም በእጁና በክንዱ ላይ ያለው ሕመም ሥራሽ ስሜት አልባ ወደ መሆን ደረጃ ደረሰ፡- ይህም ጥሩ ምልክት አልነበረም።

ራልስቶን ምን ማድረግ እንዳለበት እያሰበ ሳለ፣ አንድ አስፈላጊ የሆነ የእግረኛ ተጓዥ ደንብ እንደጣሰ ተገነዘበ፤ የት እንደምትሄድ ሁልጊዜ ለአንድ ሰው ንገር የሚለውን ደንብ ነው። በመሆኑም እርሱ የት እንዳለ ማንም አላወቀም፤ ለተወሰኑ ቀናት ከጉዞው ይመለሳል ብሎ የሚጠብቀው ሰው አልነበረም። ማንም እርሱ መጥፋቱን በጠረጠረ ጊዜ፣ ወዴት መፈለግ እንዳለባቸው ሊያውቁ አልቻሉም። ማንም ሰው እርሱን በሚያገኝበት ጊዜ፣ ሞቶ ሊሆን ይችላል። እርሱ እንደዚህ ሩቅ በሆነ ምድረ በዳ እና ስውር ባለ ስፍራ ስለነበረ አስከሬኑ እንኳ ከቶ ሊገኝ አይችልም ነበር።

በዐለት ውጥመድ ከተያዘ ከዐምስት ቀን በኋላ፣ ራልስቶን ሞት የማይቀርለት መሆኑን ስለ አሰበ፣ ሕይወቱ የማይተርፍ ከሆነ አንድ ሰው ያገኘዋል ብሎ ተስፋ በማድረግ አንዳንድ መልእክቶችን በቪዲዮ ካሜራው ለመቅረጽ ቻለ። አስከሬኑን የሚያገኙ ሰዎች የእርሱን ማንነት ለማወቅ እንዲችሉ በኪሱ በነበረው ሴንጢ ስሙን ጻፈ፤ እንዲሁም የተወለደበትን ወርና ዓመተ ምህረት፣ እ.ኤ.አ ጥቅምት 1975፣ የእግር ጉዞ የጀመረበትን ወር ደግሞ ሚያዝያ 2003 ብሎ ጻፈና እርሱ በተቀረቀረበት ዐለት ድንጋይ ውስጥ አስቀመጠው።

ከዚያም ራልስቶን ሕይወቱን ለማዳን ማድረግ እንዳለበት የተገነዘበውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ተንቀሳቀሰ። ራሱን ከቋጥኙ ለማስለቅ በኪሱ ባለው ሴንጢ ክንዱን ቆረጠ። ከዚያ በኋላ በሚያስገርም ሁኔታ የደም ማምጠጫ መሣሪያን በመጠቀም ለራሱ መሠረታዊ የሆነ የመጀመሪያ እርዳታ ካደረገ በኋላ ስድሳ ዐምስት ጫማ ጥልቀት ካለው ገደል በገመድ በመውጣት ሰባት ማይል በእግሩ ተጓዘ። ከባድ መኪናውን ወደ አቆመበት ስፍራ እየቀረበ ነበር፤ ነገር ግን ወደ እርሱ ለመድረስ የስምንት መቶ ጫማ ከፍታ መውጣት ነበረበት። ራልስቶን አሁንም ደመ እየፈሰሰ አልቆበት እየተንቀጠቀጠ

ወደ መኪናው ለመድረስ ራሱን እየገፋ ሄደ። ወደዚያም በተጠጋ ጊዜ፣ የነፍስ አድን ቡድኖች እርሱን ለመፈለግ ተሰብስበው አየ።

ከዚያ በመጀመሪያ በአቅራቢያው ባለ ሆስፒታል ሕክምና ተደረገለት፤ ቀጥሎም ከተቆረጠው ክንዱ የተረፈው ክፍል ቀዶ ጥገና እንዲደረግለት ወደ ሌላ የሕክምና ድርጅት ተላከ።

እናንተ እንደ ራልስቶን ያለ ከባድ ሁኔታ እንደማያጋጥማችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ነገር ግን የማይቻል በሚመስል ሁኔታ ውስጥ ስለ ሕይወት ያሳየውን ድፍረት፣ የጎይል መላትና ታማኝነት እንደምታዳብሩ ተስፋ አደርጋለሁ።

እናንተ አንድ ነገር ማድረግ እንደሚያስፈልጋችሁ እያወቃችሁ "ይህ በጣም ከባድ ነው" ትተበሉ። እግዚአብሔር ልንሸከመው ከምንችለው በላይ ምንም ነገር እንድንሸከም ከቶ አይጠይቀንም፤ ነገር ግን ከእያንዳንዱ ችግር ጋር የመውጫውን መንገድ ያቀርብልናል። "መንገድ የለም" ትበሉ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር መንገድ ስለሆነ (ዮሐንስ 14÷6 ይመ.) ለእኛም መንገድ ያበጅልናል። በሕይወት ለማድረግ የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ! ችሎታው አላችሁ!

የራንግለር (ዲነም) ንጉሥ

የምትወዱትን ጂንስ ሱሪ ስትለብሱ ማን እንደ ፈለሰፈው ጠይቃችሁ ታውቃላችሁን? ምናልባት ጠይቃችሁ አታውቁም ይሆናል፤ ነገር ግን ታሪኩ መነገር ያለበት ነው።

ለዓመታት፣ ሌቪ ስትራውስ በራንግለር (ዲነም) ጨርቅ እጅግ ዝነኛ ስም ሆኖ ቆይቶአል፤ ስትራውስ ግን የዚህ የተወደደው ሱሪ ባለቤት ለመሆን ወይም ሱሪውን በመሸጥ ሀብት ለማግኘት ከቶ አላሰበም። ስትራውስ በአሜሪካ ውስጥ የተሳካ የብልጽግና ሕይወት ለመገንባት ቁርጥ ሀሳብ የነበረው፤ ፈጣን፣ ጠንካራና ብልህ ሠራተኛ ሲሆን የባቫሪያን ስደተኛ ነበር፤ ወደ አሜሪካ የመጣው አባቱ በ1845 በሳምባ ነቀርሳ ከሞተ በኋላ ከጆርመን (በዚያ ጊዜ ስሟ ሌላ ነው) ከእናቱ ጋር ነበር። እርሱ ኒውዮርክ ከመድረሱ በፊት የሌቪ ሀለት ታላላቅ ወንድሞች፣ ጆናስና ሉዊስ፣ በዚያ ከተማ ውስጥ በራሳቸው የደረቅ ሸቀጥ የጅምላ ሽያጭ ኩባንያ ሥራ ተደላድለው ተቀምጠው ይኖሩ ነበር። ሌቪ የወንድሞቹን ፈለግ በመከተል፣ የደረቅ ሸቀጥ የንግድ ሥራን መማር ጀመረ።

ሌቪ በካሊፎርኒያ ውስጥ ስላለው የወርቅ አደን (ፍለጋ) በሰማ ጊዜ፣ ወደ ምዕራብ ለመሄድ ወሰነ። ቤቱን በሳን ፍራንሲስኮ አደረገና በዚያ የራሱን የደረቅ ሸቀጥ ንግድ በመጀመር በኒውዮርክ ላለውም የወንድሞቹ ኩባንያ ወኪል ሆነ። በእርሱ ኩባንያ አማካይነት ደረቅ ሸቀጦችን በማስገባት በካሊፎርኒያና በምዕራብ አሜሪካ ባሉ አዳጊ ከተሞች ይሸጥ ጀመር።

ሌቪ በ1872 በኔቫዳ ካለ ከአንድ ደንበኛ ደብዳቤ ባገኘ ጊዜ፣ አድል በሩን አንኳኺችለት። ጃኮብ ዴቪስ የተባለ፣ ልብስ ሰፊ፣ ለሠራተኞች ሱሪ መስፋት የጀመረ መሆኑን ለሌቪ በደብዳቤው ውስጥ ገለጸለት። ሱሪው ጫና በሚበዛባቸው ስፍራዎች፣ ለምሳሌ በእያንዳንዱ ኪስ ማዕዘን ላይና በቀበቶ መደገፊያዎቹ ሥር የብረት ቁልፍ ያለበት

ነበር። ዴቪስ የመብት ባለቤትነቱን ለብቻው ለመውሰድ ስላልቻለ አስፈላጊ ለሆነው የወረቀት ሥራ ክፍያ ለመፈጸም የሌቪን እርዳታ ጠየቀና ሁለቱም የመብት ባለቤትነቱን እንዲወስዱ ሀሳብ አቀረበ። በግንቦት 20፣ 1873 እነርሱ "የወገብ ቁታ" ብለው በጠሩት፣ አሁን "ስማያዊ ጂንስ" በሚባለው የልብስ ሥራ የመብት ባለቤትነታቸውን ተቀበሉ።

ብዙ ሳይቆይ ሌቪ በሳን ፍራንሲስኮው ፋብሪካ በወገቡ ላይ የብረት ቁልፍ ያለውን ቱታ የጅምላ ምርት በበላይነት ለመቆጣጠር እንዲችል ጃኮብ ከእርሱ ጋር አብሮት እንዲሄድ ጠየቀው። በመጀመሪያ ልብስ ሰፊዎች ሱሪዎቹን በቤታቸው ይሰፉ ነበር፤ ነገር ግን በ1880ዎቹ ዓመታት ፈላጊ እየበዛ ሄደ፤ ስለዚህ ሌቪ ተወዳጅ ለሆነው ሱሪ ማምረቻ የሚሆን የፋብሪካ ቦታ ተከራየ። እስከ ዛሬ ድረስ በገበያ ላይ የሚገኙት የመጀመሪያዎቹ 501® ጂንሶች የተመረቱት በዚህ ጊዜ ነበር።

በዓመታት ውስጥ፣ የሌቪ የንግድ ሥራ እያደገ መሄዱን ቀጠለ፤ እርሱም ፈጣንና ጠንካራ ሠራተኛ የንግድ ሰው መሆኑ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ ሰውን የሚወድና ትሁት አሠሪ በመሆን የታወቀ ነበር። ደግሞም ለአካባቢው በጐ አድራጐት ድርጅቶች ብዙ ገንዘብ ያበረከተ ለጋስ የሆነ በጐ አድራጊ ነበር፤ ከዚያም በ1897 በርክሌይ በሚገኘው የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ለሃያ ስምንት የኮሌጅ ተማሪዎች የመማሪያ ገንዘብ ክፍያን ቻለ።

እናንተም በጽናት ከቀጠላችሁ፣ ይቻላል ብላችሁ ከቶ ወደማታስቡበት ግብ እንደምትደርሱ መገንዘብ ይገባችኋል። ይህንንም በፈጸማችሁ ጊዜ፣ እንደ ሌቪ ስትራውስ ርህሩህና ለጋስ ሁኑ፤ የልፋታችሁንም ስኬትና መልካም ብድራት ለሌሎች ማካፈልን አትርሱ።

ምዕራፍ 6

የአሸናፊነት መንፈስ

"ችግሮች ለሰዎች ምንነታቸውን ያሳያሉ። አንዳች ችግር በመጣ ጊዜ እግዚአብሔር አንተ አሸናፊ ትሆን ዘንድ ከጠንካራ ባለጋራ ፊት ለፊት እንዳስቀመጠህ አስታውስ፤ ይህም ያለ ልፋት አይገኝም።"

እፒክቴተስ።

በ1867፣ ጆን ሮብሊንግ የተባለ የፈጠራ ችሎታ ያለው መሐንዲስ የኒውዮርክ ከተማን ከብሩክሊን ጋር የሚያገናኝ በጣም አስደናቂ ድልድይ የመገንባት አሳብ አደረበት። ይሁን እንጂ፣ በመላው ዓለም ያሉ የድልድይ ግንባታ ባለሙያዎች ሀሳቡ የማይቻል መሆኑን በማሰብ ሮብሊንግ ይህን አሳብ እንዲተው መከሩት። ድልድዩ ከቶ ሊሠራ አይችልም። ተግባራዊ አይሆንም። ከዚያ በፊትም ተሠርቶ አያውቅም አሉ።

ሮብሊንግ ስለዚህ ድልድይ ጉዳይ በአእምሮው ውስጥ የነበረውን ራእይ ችላ ሊለው አልቻለም። ስለ ድልድዩ ሁልጊዜ እያሰበ ሊሠራ እንደሚችል በልቡ ያውቅ ነበር። ሕልሙን ለሌላ ሰው ማካፈል እንዳለበት ብቻ ተሰማው። ከብዙ ውይይትና ማግባባት በኋላ አዳጊ መሐንዲስ የነበረውን ወንድ ልጁን ዋሽንግተንን፣ ድልድዩ ሊሠራ እንደሚችል ለማሳመን ቻለ።

አባትና ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ አብረው በመሥራት፣ ሥራው እንዴት ሊጠናቀቅ እንደሚችልና እንቅፋቶቹም እንደሚወገዱ አንዳንድ አሳቦችን አዳበሩ። በታላቅ ጉጉትና መነሣሣት፣ እንዲሁም በፈታቸው

ታላቅና አስቸጋሪ ተግዳሮት እንደሚኖር በመተማመን፣ ሠራተኞቻቸውን ቀጠሩና ያለሙትን ድልድይ መገንባት ጀመሩ።

ውጥኑ በደህና ሁኔታ ተጀምሮ ነበር፣ ነገር ግን ጥቂት ወራት ብቻ እንደተካሄደ በሥራው አካባቢ አሳዛኝ አደጋ ተፈጠረና የጆን ሮብሊንግን ሕይወት አጠፋ። ከሦስት ዓመት በኋላ ልጁ ዋሽንግተን ተጉዳና እንዳይራመድ፣ እንዳይናገር፣ ወይም እንዳይንቀሳቀስ እንኳ የሚያደርግ ትልቅ ጉዳት ደረሰበት።

"እኛ ነግረናቸው ነበር።"
"እብዶችና የእብደት ሕልማቸው።"
"የማይጨበጥ ሕልምን መከተል ሞኝነት ነው።" ተባለ።

እያንዳንዱ ሰው አሉታዊ አስተያየት ነበረው፣ እንዲሁም ድልድዩ እንዴት ሊሠራ እንደሚችል የሚያውቀው የሮብሊንግ ቤተሰብ ስለሆነ ውጥኑ መሠረዝ አለበት የሚል ስሜት ተሰማቸው። ዋሽንግተን ምንም እንኳ የአካል ጉዳተኛ ቢሆንም፣ በማይታመን ሁኔታ ከቶ ተስፋ ያልቆረጠ ስለነበረ፣ እንደዚያም ሆኖ ድልድዩን ሠርቶ ለመጨረስ የሚቃጠል ምኞት ነበረው። ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳት ቢኖርበትም፣ አእምሮው አሁንም እንደ በፊቱ ንቁ ነበር።

ዋሽንግተን አንዳንድ ጓደኞቹን ለማነቃቃትና የእርሱን ጉጉት ለእነርሱ ለማስተላለፍ ሞከረ፣ ነገር ግን እነርሱ ሥራውን በጣም ፈርተውት ነበር። እርሱ በሆስፒታል አልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ የፀሐይ ብርሃን በመስኮቱ ውስጥ ሲገባ እንዲሁም ለስለስ ያለ ነፋስ መጋረጃዎቹን ሲከፍታቸው ለማዩንና በውጪ የነበሩትን የዛፎች ጫፍ ለአንድ አፍታ ለማየት ቻለ።

ከቶ እጅ እንዳይሰጥ የሚገልጽ መልክት የመጣለት መስሎ ታየው። በድንገትም አንድ አሳብ መጣለት። እርሱ ማድረግ የነበረበት አንድ ጣቱን ብቻ ማንቀሳቀስና በእርሱም እንደሚገባው መጠቀም ነበር። ያችንም አንዲት ጣት በመጠቀም ቀስ በቀስ ከሚሰቱ ጋር የመገናኛ ምልክትን አዳበረ።

መሐንዲሶቹን እንደገና እንድትጠራለት ለማመልከት፣ የሚስቱን ክንድ በጣቱ ነካ አደረገ። ከዚያም ይሀንኑ ክንዷን የመንካትን ዘዴ መሐንዲሶቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመንገር ተጠቀመበት። ነገሩ ሞኝነት ይመስላል፤ ነገር ግን ውጥኑ እንደገና በሥራ ላይ ሆነ።

በመጨረሻ ድልድዩ ተሠርቶ እስኪያልቅ ድረስ ዋሽንግተን ለዐሥራ አንድ ዓመታት የሚስቱን ክንድ በመንካት መመሪያዎቹን ያስተላልፍ ነበር። ዛሬ የብሩክሊን አስደናቂ ድልድይ የአንድ ሰው የማይደክም መንፈስና በሁኔታዎች የአለመሸነፍ ቆራጥነት ምስክር በመሆን በሙሉ ክብሩ ቆሞ ይታያል። ደግሞም ለመሐንዲሶቹና ለቡድን ሥራቸው፤ እንዲሁም በግማሹ ዓለም እንደ አብድ በተቆጠረው ሰው ላይ እነርሱ ላላቸው እምነት ምስክር ነው። ደግሞም፤ ለዐሥራ አንድ ዓመታት የባሏን መልእክት በትእግሥት እየመዘገበች መሐንዲሶቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለነገረቻቸው ለዋሽንግተን ሚስት ተጨባጭ የሆነ የመታሰቢያ ሐውልት ነው።

የድል አድራጊ መንፈስ

ዋሽንግተን ሮብሊንግ እኔ "የድል አድራጊ መንፈስ" ብዬ የምጠራው ነገር ነበረው፤ እናንተም የድል አድራጊ መንፈስ ወደምታገኙበት ነጥብ እንድትደርሱ አደፋፍራችኋለሁ። አሁን ከምታዩት በተለየ ሁኔታ ራሳችሁን እንድታዩ፣ ችግር በመጣ ጊዜ ሁሉ ወደ ኋላ የመሸሽ ወይም የመሸነፍ ስሜት ሳይሆን ችግሮችን የማሸነፍ ስሜት እንዲኖራችሁ ልረዳችሁና ላነቃቃችሁ እፈልጋለሁ። መከራ ሊያጋጥማችሁ ደፋሮች እንድትሆኑና ራሳችሁንም በዚሁ ዐይነት እንድታዩ መከራውንም በድፍረት፣ በልበ ሙሉነት፣ በጥበብና በእምነት እንድትጋፈጡት እፈልጋለሁ።

አያችሁ፤ መከራ አማራጭ የለውም፤ መከራን ለማሸነፍ አሸናፊ መሆንን ይጠይቃል። ኢየሱስ ራሱ፣ "በዓለም ሳላችሁ መከራና ችግር፣ ሀዘንና ብስጭት አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ [ድፍረት ይኑራችሁ፣ ልበ ሙሉዎች፣ እርግጠኞችና የማትፈሩ] ሁኑ! እኔ

ዓለምን አሸንፌዋለሁ። [እናንተን ለመጉዳት ያለውን ኀይል ወስጄበት እርሱን ስለ እናንተ አሸንፌዋለሁ]" አለ። (ዮሐንስ 16÷33)።

ጳውሎስም ይሀንን ተረድቶ፣ በሮሜ 8÷35-37 እንዲህ ብሎአል፦ "ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማነው? ችግር ነው ወይስ ስቃይ፣ ወይስ ስደት ወይስ ረሃብ፣ ወይስ ራቁትነት፣ ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ? ይህም ስለ እናንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር እንጋፈጣለን እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደተጻፈ ነው። ምንም አይለየንም፣ በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን" አለ። ከአሸናፊዎች መብለጥ ማለት ምን ማለት ነው? ገና መከራ ሳይመጣ፣ በእናንተ ላይ ውጊያ ገና ሳይጀመር፣ እናንተ እጅ መስጠትን እምቢ የምትሉ ከሆነ በመጨረሻው ታሸንፋላችሁ ማለት እንደሆነ አምናለሁ።

ደግሞም ሮሜ 8÷31 ተመልከቱ፤ "ታዲያ ለዚህ [ሁሉ] ምን እንመልሳለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ሊቃወመን ይችላል" [እግዚአብሔር ከእኛ ጐን ከሆነ ማን ጠላት ሊሆንብን ይችላል?] "ይላል። እኔ ላረጋግጥላችሁ፤ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ከሆነ አሸናፊ ከመሆን በስተቀር ሌላ ምንም ዐይነት አስተሳሰብ ለማስተናገድ ምክንያት የላችሁም። እርሱ ከጐናችሁ ነው፤ ስለዚህ የድል አድራጊ መንፈስን ይሰጣችኋል።

ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት እንዳላችሁ ካልተሰማችሁ፣ እርሱ ከእናንተ ጋር መሆኑ ላይሰማችሁ ይችል ይሆናል። እርሱ ከእናንተ ጋር ነው፤ ግን እናንተ ይሀንን ማመን አለባችሁ ነጠላታችሁን ይቅር ማለት ብቻ ሳይሆን በሕይወት ዘመናችሁ ሙሉ እንደሚረዳችሁ ተስፋ ቃልን በርሱ ልትጥሉበት ይገባችኋል። በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ያለውን ጸሎት ተመልከቱ። ኢየሱስ ክርስቶስን በልባችሁ በምትቀበሉበት ጊዜ፣ የድል አድራጊ መንፈስንም ደግሞ ትቀበላላችሁ።

በሕይወታችሁ የገጠማችሁ ነገር ምንም ይሁን ምን፣ የድል አድራጊ መንፈስ ካላችሁና እናንተ በክርስቶስ ሟን እንደሆናችሁ ካወቃችሁ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ከእናንተ ጐን መሆኑን በእውነት

ካመናችሁ በሚያጋጥማችሁ በማንኛውም ችግር መፍራትና መሸነፍ አይኖርባችሁም። የዕዳ ተራራ ለመናድ፣ ትምህርታችሁን ለመጨረስ፣ ሕመምን ለመዋጋት፣ የሚያስፈራራንንና የሚያንገላታንን ማንኑነት ለመተው፣ የራሳችሁን ሥራ ለመጀመር፣ ወደ አገልግሎት ለመሄድ፣ ወይም በቀላሉ ቤታችሁን ለማጽዳት ብትሞክሩ፣ እግዚአብሔር ከጐናችሁ ከሆነ ልታደርጉት ትችላላችሁ። እናንተ የሚያስፈልጋችሁ የድል አድራጊ መንፈስን ማዳበር ብቻ ነው።

ቀደም ሲል የጻፍሁትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ልብ አድርጉ፦ "ቅጣት ሁሉ በወቅቱ የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፤ በኋላ ግን ለለመዱት ሰዎች የጽድቅና የሰላም ፍሬ ያስገኝላቸዋል" (ዕብራውያን 12÷11)። መከራ ባጋጠማችሁ ጊዜ "ይህንን ለመቀበል አልችልም" ከቶ አትበሉ። ይልቁንስ የድል አድራጊ መንፈስ ይኑራችሁና "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው፤ እግዚአብሔር ከጐኔ ነው፤ ስለሆነም ኀይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ" በሉ።

ዲያብሎስን ተቃወሙት

ብዙ ክርስቲያኖች እምነታቸው ከጠላት ጥቃትና ማስፈራራት ነፃ እንደሚያደርጋቸው የሚያምኑ ይመስላሉ፤ ስለዚህ እርሱ ሊያስቸግራቸው ሲጀምር ይደነቃሉ። ይህ እውነት አይደለም፤ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንደ ተማርነው እኛ በመከራ ውስጥ እናልፋለን። ሁልጊዜ ሳይሆን፤ አንዳንድ ጊዜ፣ መከራዎቻችን ከጠላት አሠራር የሚመጡ ናቸው። እኛ "መጥፎ ዕድል"፤ "አስቸጋሪ ሁኔታ" ወይም "ከባድ ቀን" ብለን የምንጠራው ምናልባት እንደ እውነቱ ከሆነ ከዲያብሎስ አሠራር ሊሆን ይችላል። እነዚህ መከራዎች ሲያጋጥሙን፣ ምን እናደርጋለን?

በመጀመሪያ እኛ በሰይጣን ላይ ሥልጣን እንዳለን ማስታወስ ያስፈልገናል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን በጽናት መቃወም እንዳለብን ይነግረናል። ያዕቆብ 4÷7 "እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፤ ዲያብሎስን ተቃወሙት [እርሱን በመቃወም ጸንታችሁ ቁሙ] ከእናንተም ይሸሻል" ይላል። እኛ በመጀመሪያ ራሳችንን ለእግዚአብሔር

ካላስገዛን በስተቀር ሰይጣንን በእውነት ለመቃወም ኀይል እንደሌለን መረዳት ይገባናል። ይህ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እደግመዋለሁ፤ በመጀመሪያ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ካላስገዛን በስተቀር በሰይጣን ላይ ኀይልን ልንለማመድ አንችልም፤ ይህም በቀላሉ ለእርሱ መታዘዝ ያስፈልገናል ማለት ነው። ዲያብሎስን ለመቃወም ሥልጣንና ችሎታ የሚሰጠን፣ ለጌታ የምናደርገው የመሉ ልብ መታዘዝና መገዛት ብቻ ነው።

ዲያብሎስን መቃወም ማለት መከራዎቻችን ወይም ችግሮቻችን እንዲወገዱ እንፈልጋለን ማለት ሳይሆን በማንኛውም ሁኔታና ጊዜ ጽኑ ለመሆንና የጽድቅ ባሕርይ ለማንፀባረቅ ቁርጠኞች መሆን አለብን ማለት ነው። "በእናንተ ውስጥ ያለው ... በዓለም ካለው ይበልጣል" (1ዮሐንስ 4÷4)፤ የእግዚአብሔር ኀይል በእናንተ ውስጥ የሚሠራ ከሆነ፣ ጠላትን አልፋችሁ መሄድ ብቻ ሳይሆን ውጊያው በመፋፋም ላይ እያለ እግዚአብሔርን በማገልገል ልትቀጥሉ ትችላላችሁ።

ልብ አድርጉ፤ ያዕቆብ 4÷7 ጠላትን "ተቃወሙት" ይላል። ጠላት ለመሰዊያው ጥሪ ምላሽ በመስጠታችን ብቻ ወይም የክርስትና ምልክት ያለበትን ጌጣጌጥ በማድረጋችን አይሸሽም። ደግሞም በየአሁዱ ወደ ቤተክርስቲያን በመሄዳችን፣ ወይም የክርስቲያን መጻሕፍትና ሲዲዎች የሞሉበት ቤተ-መጻሕፍት ቢኖረን አይሸሽም። እኛ በውሳኔያችን ጽኑ ካልሆንንና እጅ ላለመስጠትም ቁርጠኞች ካልሆንን ጠላትን ልናሸንፈው አንችልም።

በጥንካሬ ጀምሩ፣ በደህና ፈጽሙ

በሕይወታችን የምንሠራው እያንዳንዱ ነገር መጀመሪያና መጨረሻ አለው። አብዛኛውን ጊዜ እኛ በአንድ መልካም አጋጣሚ፣ በአንድ ግንኙነት፣ ወይም በአንድ እርምጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ደስ እንሰኛለን፤ ደግሞም የሥራ ውጤታችንን ስናከብርና በምኞታችን መሚላት ስንረካ እንደሰታለን። ነገር ግን በመጀመሪያውና በመጨረሻው መካከል ማንኛውም ሁኔታ "መካከለኛ" ነገር አለበት፤ መካከለኛው ታላላቅ ተግዳሮቶችን፣ መሰናክሎችን፣ የመንገድ መቆሚያዎችን፣

እንቅፋቶችን፣ መዞሪያዎችንና ፈተናዎችን የምንጋፈጥበት ስፍራ ነው። በቀላሉ በስሜቶቻቸው የሚመሩ ሰዎች የጀመሩትን ሳይጨርሱ ይቀራሉ። ሥራው የሚያጓጓ ሳይሆን ሲቀርና በፊታቸው የሚያዩት ከባድ ሥራ ብቻ ሲሆን ይሸነፋሉ። እግዚአብሔር የጀመርነውን የምንጨርስ ሰዎች እንድንሆን ይፈልጋል፤ ደግሞም እኛ ከፈቀድንለት እርሱ ይረዳናል።

እናንተ በአሁኑ ጊዜ በብዙ ነገሮች መካከል ልትሆኑ ትችላላችሁ። ምናልባት አሁን ከዕዳ በመውጣት መካከል ልትሆኑ ትችላላችሁ። ከአንዱ በስተቀር ሁሉንም ዕዳችሁን ከፍላችሁ ይሆናል፤ ከዚያም እኔ አሁን ደህና ነኝ፤ ስለዚህ ሣሬ ወደ ገበያ ለመሄድ አስባለሁ፤ ምክንያቱም ብዙ የሸቀጫ ቅናሽ አንዳለ አንብቤአለሁ ብላችሁ ማሰብ ትጀምራላችሁ። አሁን "ደህና መሆን" በቂ አይደለም፤ ምክንያቱም ይህ የመጀመሪያው ግባችሁ ስላልነበረ ነው። ራሳችሁን ከዚህ ረዘም ላለ ጊዜ አሠልጥኑት፤ ያችን የመጨረሻዋን የዕዳ ሂሳብ ስትከፍሉና ከዕዳ ሙሉ በሙሉ ነፃ ስትሆኑ ይህን በማድረጋችሁ ትደሰታላችሁ። አንድ የመገናኛ ጊዜ እንዲኖራችሁ ወይም የስሜታችሁን ውጥረት ለማቃለል ከፈለጋችሁ፤ የወጪ ሂሳብ የማይጠይቃችሁን አንድ ነገር ፈልጉ። በመካከል ሆናችሁ ምንም ነገር ብታገኙ፤ እርሱ እስከ ሚጠናቀቅ ድረስ ለማየት ወስኑ።

በመጀመሪያችንና በመጨረሻችን መካከል ሳለን በመካከል የሚያጋጥመንን ነይለኛ ሁኔታዎች ለማሸነፍ የሚያስፈልገንን ድፍረትና ቁርጠኝነት ማዳበር ያስፈልገናል። ጠላት እግዚአብሔር ካቀደልን መልካም ነገር ባነሰ ሁኔታ ረክተን እንድንቀመጥና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ማንኛውንም ነገር ሳንቀበለውና ሳንደሰትበት ከዚያ ወዲህ ባጭር ሊያስቀረን ይፈልጋል። ዲያብሎስ እድገትን ስለሚጠላ እጅ እንድንሰጥ ይገፋፋናል። በሌላ በኩል፤ እግዚአብሔር ለእኛ ከሁሉ የበለጠውን ነገር ይፈልጋል፤ እርሱ በፊታችን ያለውን ሩጫ እንድንፈጽም፤ እንዲያውም በደስታ እንድንፈጽም ይፈልጋል (ዕብ. 12÷1 ይመ)። እናንተም ሩጫውን ለመፈጸም ዋጋውን ለመክፈል ፈቃደኞች መሆናችሁን ራሳችሁን ጠይቁ።

በሕይወታቸው ውስጥ መልካም ፍጻሜ የሚኖራቸው ሰዎች ጠንካራ ባሕርይ ያላቸው ሰዎች ናቸው። እነርሱ "የሚዘልቅ ጎይል" አላቸው። ኢየሱስ ሁኔታዎች ከባድ በሆነበት ጊዜ አልሸሸም፤ እርሱ ምሳሌያችን ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በቀላሉ ተብትቦ የሚይዘንን ኃጢአት አስወግደን የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንድንመለከት ይነግረናል (ዕብራውያን 12÷2 ይመ.)። እርግጥ ነው፤ ዋሽንግተን ሮበሊንግ ፈጻሚ ነበር። ሌላው ታላቅ ፈጻሚ ሐዋርያው ጳውሎስ ነበር። በሐዋርያት ሥራ 20÷24 መሠረት ጳውሎስን ያጋጠሙት ማንኛቸውም እንቅፋቶች አላነቃነቁትም፤ ወይም በእርሱ ላይ ምንም ዐይነት አሉታዊ ውጤት አልነበራቸውም። ደግሞም ጳውሎስ በዚሁ ጥቅስ፣ ሩጫውን በደስታ ለመፈጸም እንደሚፈልግ ተናግሮአል። ይህ ማለት እርሱን ያጋጠመው ነገር አስቸጋሪ አልነበረም ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ሊያስቆመው (ሊገታው) አልቻለም ማለት ነው።

እኔ እንደማስበው አብዛኞቻችን እግዚአብሔር ያቀደልንን እያንዳንዱን ነገር ለማድረግና ለመሆን፣ እንዲሁም በሂደቱ ለመደሰት እንፈልጋለን። እግዚአብሔር እንድንሮጥ የጠራንን ሩጫ ስንፈጽም ታላቅ ደስታ ይገኛል። በጉዞው ተደሰቱና ዐይኖቻችሁን በብድራቱ ላይ አድርጉ። ኢየሱስ በፊቱ ያለውን ሽልማት በሚያገኝበት ጊዜ ስለሚኖረው ደስታ ሲል የመስቀሉን መከራ ታገሠ።

ጳውሎስ ከፍተኛ አገልግሎት አበረከተና በሕይወቱ ብዙ ነገሮችን ፈጸመ። በምድር ላይ የነበረውን ጉዞ ለመፈጸም በተቃረበበት ጊዜ እንዲህ ሲል ጻፈ፤ "መልካሙን (ተገቢ የሆነውን፣ ክብር ያለበትን፣ ከፍተኛ የሆነውን) ገድል ተጋድያለሁ። ሩጫውን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖትንም ጠብቄአለሁ (አጥብቄ ይዣለሁ)" (2ጢሞ. 4÷7)። በመሠረቱ እርሱ በዚህ ጥቅስ የሚለው፤ "በብዙ ነገር ውስጥ አልፌአለሁ። ነገር ግን አሁንም እዚህ አለሁ። ጠላት ሊያባርረኝ ፈልጉ ነበር፤ ነገር ግን አልተሳካለትም!" ነው።

እኛ ሊኖረን የሚችለው እጅግ ታላቁ ምስክርነት በሚቀጥሉት በሦስት ቃላት የተጠቃለለ ይመስለኛል፤ *"አሁንም እዚህ አለሁ"* የሚል

ነው። እነዚህን ቃላት በምንናገርበት ጊዜ "አልሸሸሁም። እጅ አልሰጠሁም። እኔ አሁንም እዚህ አለሁ ማለታችን ነው።"

ወደ ግባችሁ ስትሄዱ "በመካከል" መሆናችሁ ከተሰማችሁ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ታሪኮች እንደገና አንብቡ። አስደናቂ ነገሮችን የፈጸሙትን ሰዎች ሕይወት ስትመለከቱ ትነቃቃላችሁ፤ ምክንያቱም እነርሱ በመካከለኛው ውስጥ አልፈው የፍጻሜውን መስመር ስለተሻገሩ ነው።

በችግሮች ምክንያት መንገዱን አትሳቱ

ጳውሎስ በ1ተሰሎንቄ 3÷3-5 እንዲህ ይላል፦

> *ማንም ከእናንተ በዚህ ፈተና [ቀደም ብዬ በጠቀሰሁት] እንዳይናወጥ ነው። እኛም ለዚህ ነገር እንደተመደብን [የማይታለፍና የታወቀ እንደሆነ] እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ። በእርግጥ ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ [ታውቃላችሁ] መከራ እንደሚደርስብን በየጊዜው እንነግራችሁ ነበር። እንደምታውቁትም [ከዚያ ወዲህ] እንዲሁ ደግሞ ሆኖአል። ስለዚህ [መዘግየቱን] ምንም መታገሥ ባልቻልሁ ጊዜ ስለ እምነታችሁ [ውጥረቱንና ጫናውን እንዴት እንደተቋቋማችሁት] ለማወቅ ላክሁ፤ ይህንንም ያደረግሁት ምናልባት ፈታኙ ፈትኖአችሁ ድካማችን ሁሉ ከንቱ ሆኖአል ብዬ ስለፈራሁ ነው።*

በዚህ ምንባብ፣ ጳውሎስ የሚለው፣ "በሚያጋጥሙአችሁ መከራዎች፣ ችግሮችና ጭንቀቶች ምክንያት ትሸሹና ትሸነፋላችሁ ብዬ ፈርቼ ነበር" ነው። በመሠረቱ እርሱ የተሰሎንቄን ሰዎች እንዲህ በማለት እያበረታታ ነበር፤ "ችግሮች በመንገዳችሁ ላይ ቢደቀኑ አትደነቁ፤ እንዲያነቃንቁአችሁ አትፍቀዱላቸው፤ እንዲረብሹአችሁ አትፍቀዱላቸው። ነገር ግን 'ይህም ያልፋል' በሉ። ይህ የሕይወት አንዱ ክፍል ነው፣ ስለዚህ በጫናው ምክንያት አትሸመድመዱ" ማለቱ ነበር።

ዴቭና እኔ አንድ ችግር በተጋፈጥን ጊዜ፣ እርሱ ከሚናገራቸው ነገሮች አንዱ "እኔ አልተደነቅሁም!" የሚል ነው። እርሱ የሚለው ችግሮች እንዲያስደንቁን ካልፈቀድንላቸው በስተቀር አይጫኑንም፤ ወይም አያስተክዙንም ነው። በማዕበሉ ውስጥ ፀንተን መቆምን መማር አለብን፤ ይህ ከሆነ ወደ ተፈለገው ግብ በሰላም እንደርሳለን።

እኛ ተነሥተን ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ለመሥራት በምንሞክርበት ጊዜ ጠላት ይህን ይቃወማል። ይህ ሁልጊዜ እውነት ነው፤ ደግሞም የማይቀር ነው። ጳውሎስ በእርግጥ ይህን ተለማምዶት ነበር፤ ስለዚህ በ1 ቆሮንቶስ 16÷9 ላይ፤ "ምክንያቱም ታላቅ የሥራ በር ተከፍቶልኛል፤ ብዙ ተቃዋሚዎችም አሉብኝ" ይላል።

በዓመታት ውስጥ ብዙ ሰዎች በጆይስ ማየር አገልግሎት ውስጥ ለመሥራት መጥተዋል። አንዳንዶቹ ከሌሎች ግዛቶች መጥተው በሴንት ሉዊስ ለመቀመጥ የመኖሪያ ቤት የማግኘትን፣ የመንቀሳቀስን፣ ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት የማግኘትንና በአዲስ ከተማ ተደላድሎ የመቀመጥን ችግሮች መቃቃም ነበረባቸው። ከእነዚህ አንዳንዶቹ ተቀጥረው በሚሠሩበት በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ምን ያህል "ብዙ ባለጋራዎች" እንደሚገጥሙአቸው ሳስብ በጣም ይገርመኛል። ጠላት በተደጋጋሚ እነዚህን ችግሮች በመጠቀም እንዲህ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፤ *ምናልባት ምርጫዬ ትክክል አይደለም ይሆናል። ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ መስሎኝ ነበር፣ ነገር ግን ተሳስቼ ይሆናል። ምናልባት ቤተሰቤን ይዤ ነገሮች ቀላል ወደ ሆኑበት ወደ ቤቴ ብመለስ ሳይሻል አይቀርም* ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል።

ብዙ ጊዜ፣ ዴቭና እኔ ከእነዚህ ሰዎች ጋር መነጋገር ያስፈልገን ነበር፤ "ራሳችሁን ለዐዲሱ ሁኔታ በምታስተካክሉበት ጊዜ ችግሮች አጋጠሙአችሁ ማለት እግዚአብሔር አልተናገራችሁም ማለት አይደለም። እናንተ የሚያስፈልጋችሁ ጸንታችሁ መቆም ነው። ወደ ልባችሁ ተመለሱ። በሁኔታዎቻችሁ ላይ አታተኩሩ። በልባችሁ ውስጥ ያለውን ተመልከቱ" እንላቸዋለን።

እነርሱም ይህ ለሕይወታቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እንደሚያምኑ በሚነግሩን ጊዜ፣ ዴቭና እኔ እንዲህ በማለት እናደፋፍራቸዋለን፤ "ስለዚህ ለመቆየት ወስኑ። ሌላ ግምት እየገመታችሁ፣ ሁለት አሳብ አይኑራችሁ። በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ወደፊት ለመራመድ ወስኑ እንጂ ወደኋላ መመለስን አታስቡ። እግዚአብሔር ወደዚህ እንደመራችሁ ካመናችሁ፣ ምንም ይሁን ምን- ለመቆየት ባላችሁ ውሳኔ ጽኑ" እንላቸዋለን።

ለጠላት፣ "ተመልከት፣ ዲያብሎስ፤ እኔ በልቤ ውስጥ ያለውን አውቃለሁ፤ እግዚአብሔር እንዳደርገው የነገረኝን አውቃለሁ፤ ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን፣ ወይም ምንም ያህል ጊዜ ቢወስድ እዚሁ ቆይቼ እግዚአብሔር ለእኔ ያለውን እጠብቃለሁ" በምንልበት ጊዜ ጠላት በመከራዎችና በችግሮች ሊቆጣጠረን አይችልም። ይህም በእኛ ውስጥ ዐዲስ የእምነትና የጥንካሬ ደረጃ ይገነባና የድል አድራጊነት መንፈስን ያሳያል።

ጳውሎስ ችግሮች የማይቀሩ ናቸው ብሎአል። እግዚአብሔርን በጽናት በምትከተሉበትና በምታድጉበት ጊዜ እነዚህ ችግሮች ይገጥሙአችኋል። ችግሮቹን ለማሸነፍ ቆራጥ ሁኑ እንጂ ከመንገዳችሁ እንዲያስቱአችሁ አትፍቀዱላቸው። እኔም ይህን ለማድረግ እንደምትችሉ አውቃለሁ። እናንተ የበኩላችሁን ማድረግ ይኖርባችኋል፤ ይህ ሥራን ይጠይቃል፤ ነገር ግን ልታደርጉት ትችላላችሁ!

ለችግሮቻችሁ መፍትሔ ስጡ

የድል አድራጊነት መንፈስ ያለው ሰው የሚያጋጥሙንን መከራዎች መጋፈጥና ለእነርሱ መፍትሔ መስጠት እንጂ፣ ከእነርሱ መሸሽ አይገባውም። እኛ በምንም ዐይነት ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች ለመሸሽና ለማምለጥ በመሞከር ልንኖር አንችልም። ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች በሸሸን ቁጥር፣ ዞሮ ዞሮ በሕይወታችን ወደ ኋላ ላይ ሁኔታዎቹን ወይም ተመሳሳይ ሁኔታ እንደምናገኛቸው እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

አስኪ ስለ ሙሴ አስቡ። እርሱ ከግብፅ ሸሽና በምድረ በዳ አርባ ዓመት ተቀመጠ፤ በዚያም እግዚአብሔር ለታላቅ መሪነት አዘጋጀው። እግዚአብሔርም በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ በተገለጠለት ጊዜ በመሠረቱ "እሺ አሁን ወደ ግብፅ እንድትመለስ እፈልጋለሁ" አለው (ዘፀአት 3÷2-10 ይመ)። አም፣ እግዚአብሔር ሙሴን ለመሸሽ ወደ ሞከረበት ስፍራ መልሶ ላከው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ታሪኮች የተሞላ ነው። ከመከራ መሸሽ ለማንም ሰው ምንም ዐይነት መልካም ነገር ሊያደርግ እንደማይችል ይህ በቂ ማረጋገጫ ነው። ከአንድ ዐይነት የችግር ሁኔታ ብትሸሹ ሁልጊዜ ሌላ ይጠብቃችኋል። አያችሁ፣ እግዚአብሔር ከመከራ የምታገኙት ክህሎት፣ ጥንካሬና ሥልጠና እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃል፤ ስለዚህ ምንም እንኳ ከአንድ የችግር ሁኔታ ለመውጣት ችሎታ ቢኖራችሁ ወደ ሌላ ችግር ይወስዳችኋል።

ለምሳሌ ብዙም ከማትወዱአቸው ከአንዳንድ ሰዎች ኩታ ገጠም ጐረቤት ሆናችሁ ትኖራላችሁ እንበል። እነርሱን በጣም ከመጥላታችሁ የተነሣ ከእነርሱ ለመሸሽ ስፍራውን ለመልቀቅ ትወስናላችሁ። ከዚያም ወደ ሌላ አካባቢ ስትሄዱ በሁለቱም ጐን ያሉት ጐረቤቶቻችሁ እናንተ በፊት ከሸሻችኋቸው ሰዎች ተመሳሳይ ባሕርይ ያላቸው ናቸው እንበል። እናንተም ይህን ለመገመት አስቸጋሪ ሊሆንባችሁ ይችላል፤ ነገር ግን እነርሱን ከአጠገባችሁ ያስቀመጣቸው እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል። እርሱ ይህን የሚያደርገው ለምንድነው? ምክንያቱም ምናልባት በእናንተ ውስጥ አንድ መስተካከል ያለበት ነገር ሊኖር ይችላል፤ ይህም የሚገለጠው በዚያ ዐይነት ሰው አካባቢ ስትሆኑ ብቻ ነው።

ማንነታቸው ከእኔ አባት ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ሰዎች ጋር እጅግ አስቸጋሪ ጊዜ ገጥሞኝ ነበር። እርሱ በእኔ ላይ ጉዳት ስላደረሰብኝ እንደ እርሱ ያለ ንግግር ከሚናገሩ ሰዎች፣ እንደ እርሱ ያለ ድርጊት ከሚያደርጉ፣ ወይም በሆነ መንገድ እርሱን ከሚያስታውሱኝ ሰዎች አካባቢ መሆን አልፈልግም ነበር።

ነገር ግን በጊዜ ብዛት እግዚአብሔር አባቴን በሚያስታውሰኝ ሰዎች የተከበብሁ እንድሆን የሚፈልግ መሆኑን ተረዳሁ። አባቴን የሚያስታውሰኝ አንድ ሰው ባገኘሁ ቁጥር፣ ጥርጥርና ፍርሃት ይሰማኝ ነበር፣ ከዚያም ወደ ዱሮው የአስተሳሰብ ባሕርይ ሸርተት እል ነበር።

የእኔን ምላሾች አልወዳቸውም ነበር፤ ወይም ከየት እንደሚመጡ ለተወሰነ ጊዜ አላውቅም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር እኔን እንዲለውጠኝና እውነቱን እንዲያሳየኝ ወደ እርሱ እጮህ ነበር። አሁን እግዚአብሔር የእኔ ድክመቶች በሚገለጡባቸው ሁኔታዎች ውስጥ እያስቀመጠኝ እንደነበረ እገነዘባለሁ፤ አሁን "እሺ፣ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ከዚህ ነፃ ልታደርገኝ እንደምትፈልግ ተረድቼአለሁ!" ለማለት እችላለሁ። እርሱ እኔ እንዳድግና ይበልጥ እንድጠነክር፣ ይበልጥ በሳል ክርስቲያን እንድሆን ለማድረግ እየሞከረ ነበር። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ከተሳሳቱ ነገሮች እንዲታደገን እንጠይቀዋለን። ከችግሮቻችን እንዲታደገን እንፈልጋለን፤ ነገር ግን እርሱ ለሕይወታችን ያለውን ዕላማ ከሚያሰናክሉት፣ በልባችን ውስጥ ካሉት ነገሮች እንዲታደገን ልንጠይቀው ያስፈልገናል።

እግዚአብሔር እርሱ የሚያምንብንና የሚጠቀምብን ሰዎች እንድንሆን ችግሮችን ይጠቀምባቸዋል። ችግር በሚያጋጥመን ጊዜ የድል አድራጊ መንፈስ ሊኖረን ይገባል። ዳዊት ንጉሥ ከመሆኑ በፊት ከጉልያድ ጋር መጋጠም ነበረበት። እኛ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ ከእነርሱ ለመሸሽ ወይም ለማምለጥ መሞከር የለብንም። በዚህ ፈንታ፣ እንዲህ ማለት ይገባናል፤ "እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህ በውስጡ ማለፍ ያለብኝ ነገር ከሆነ በድል አድራጊነት አልፍበታለሁ። በእርሱ ውስጥ በአሸናፊነት ዝንባሌ ለማለፍ እፈልጋለሁ። በዚህ አማካይነት አንተ በሕይወቴ ለመፈጸም የምትፈልገው ነገር ካለ እንድታደርገው እፈልጋለሁ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሆይ፣ አንድ ነገር እጠይቅሃለሁ፦ ይኸውም በውስጡ በማልፍበት ጊዜ ሁሉ ስሜቶቼን አልፌ ወደፊት እንድሄድና የጽድቅ ባሕርይ እንዳሳይ እንድትረዳኝ ነው" እንበል። ከችግር መሸሽ ከቶ የእኛ

> እግዚአብሔር እርሱ የሚያምንብንና የሚጠቀምብን ሰዎች እንድንሆን ችግሮችን ይጠቀምባቸዋል።

ግብ መሆን አያስፈልገውም፤ የእኛ ግብ በክርስቶስ አስተሳሰብና ባሕርይ ችግሩን ማሸነፍ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ጠላቶቻችንን እንድንባርካቸውና እንድንጸልይላቸው እንጂ እንድንሸሻቸው አያስተምረንም (ማቴዎስ 5÷44 ይመ)

እርሱ ክፉውን በመልካም እንድናሸንፍ ይነግረናል (ሮሜ 12÷21 ይመ)። በሁኔታዎቻችሁ ምንም ነገር ቢነሣ ትክክል ነው ብላችሁ ያመናችሁበትን ነገር አድርጉ፤ ከዚያም በኋላ ታሸንፋላችሁ!

ለእግዚአብሔር አድርጉት

ይህን ምዕራፍ አንብባችሁ ስትጨርሱ ለእናንተ የምመኘው ግብ ከዚህ እንደሚከተለው ነው፤ ከዚህ በኋላ አንድ ተግዳሮት በሚያጋጥማችሁ ጊዜ በውስጡ ስታልፉ የአስተሳሰብ ዝንባሌአችሁን፣ ስሜቶቻችሁን፣ አንደበታችሁንና አእምሮአችሁን የጽድቅን መንገድ እንዲከተሉ እንድታሠለጥኑአቸው ነው። ይህ ከባድ ነው። ሥጋችሁ በእናንተ ላይ ሲያምፅ ይሰማችኋል። ነገር ግን እንዲህ በሉ፤ "እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔ ይህን የማደርገው ለአንተ ነው። በራሴ ላደርገው አልችልም፤ እንዲሁም ለራሴ ላደርገው አልፈልግም። ይህን ለማድረግ የምፈልገው ለአንተ በመታዘዝ ነው።" ኢየሱስ እጅ አልሰጠም። እርሱ ለእኛ ሲል ሁሉንም መንገድ ተጓዘ፤ እኛም ለእርሱ ስንል ይህንኑ ለማድረግ እንችላለን!

ከዓመታት በፊት አንድ አሁድ አስታውሳለሁ፤ መጋቢዬ ጥቂት ጊዜ እንድንወስድና ሌሎችን ሰላም እንድንል፣ እንዲያውም እቀፍ አድርገን እንደምንወዳቸው እንድንገልጽላቸው ምዕመናኑን አደፋፈረ። እኔም ከተቀመጥሁበት ወንበር ወደፊት ስመለከት በከፍተኛ ደረጃ የጐዳችኝን አንዲት ሴት አየሁ። ከዚያም ወደ እርሷ ሄጀ እቀፍ በማድረግ ፍቅሬን እንድገልጽላት የእግዚአብሔር መንፈስ በኀይል እንደሚያሳስበኝ ተሰማኝ። ይህ በእኔ በኩል ትልቅ ትህትናን (መማረክን) የሚጠይቅ ነበር፤ ምክንያቱም እኔ ይቅርታ እንዳደርግላት እርሷ መጠየቅ እንደነበረባት ስለተሰማኝ ነው። ነገር ግን እርሷ እኔን እንደጐዳችኝ ምንም አታውቅምኳ ነበር! እኔም ሙሉ በሙሉ ከልቤ

መሆኑን ላረጋግጥ አልችልም፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር መታዘዜን አውቃለሁ።

ከብዙ ወራት በኋላ፣ እኔ በጣም የምወደውን አንድ ንብረት ለዚያችው ሴት እንድሰጣት እግዚአብሔር መራኝ። እኔም፣ "እግዚአብሔር ሆይ፤ እርሱን አሁን ለሰው ብሰጠው ግድ የለኝም፤ በእውነቱ ከሆነ፣ ይህን ለራሴ ባስቀምጠው እወዳለሁ፤ ነገር ግን አንተ ለሰው እንድሰጠው የምታዘኝ ከሆነ፣ ቢያንስ ቢያንስ ስትይዘው እኔን ደስ እንዲለኝ ለምወዳት ሴት እንድሰጠው ፍቀድልኝ!" የሚል ምላሽ ሰጠሁት።

እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፡- *ጆይስ፣ ይህንን ለእርሷ ከሰጠሻት፣ አንቺ በጣም የምትወጂውን ንብረት ብዙ ለጉዳሽና ለማይገባው ሰው ለመስጠት የምትችይ ከሆነ፣ የጠላትን ጎይል ትሰብሪያለሽ። እርሱም አንቺን ለማጥፋት ያለውን እቅድ ታጠፊዋለሽ አለኝ።*

የመታዘዝን እርምጃ የምንወስደውና የችግር ወቅቶችን የምናሸንፈው ይህን እንድናደርግ ስለተሰማን፣ ወይም መታዘዝ ጥሩ አሳብ መሆኑን ስላሰብን አይደለም። ይልቁንስ ይህን የምናደርገው እግዚአብሔርን ስለምንወድ፣ እርሱም እንደሚወደን ስለምናውቅ፣ ልንታዘዘለት ስለምንፈልግና የእርሱም መንገዶች ለእኛ መልካም መሆናቸውን ስለምናውቅ ነው።

አሁን ያጋጠሙአችሁ፣ ወይም በሚመጡት ቀናት ውስጥ የሚያጋጥሙአችሁ መከራዎች ምንም ይሁኑ ምን፣ እንድትጋፈጡአቸው፣ እንድትቀበሏቸውና እንድትቋቋሙአቸው አደፋፍራችኋለሁ። እንደ አሸናፊ ተጋፈጡአቸው። ልብ አድርጉ፣ መከራዎች ለእናንተ በጐነት የሚያገለግሉ ናቸው፤ እግዚአብሔርም እናንተን ለማጠንከር ይጠቀምባቸዋል። በድል አድራጊነት አስተሳሰብ ተቀበሏቸው፤ ከዚያም በኋላ አስቀድሞ አይታችሁት የማታውቁትን ታላቅ ብስለት፣ ጥበብና ችሎታ ታገኛላችሁ።

ችግሮች፣ ስቃዮች፣ መከራዎችና ስደቶች በራሳቸው መልካም ነገር አይደሉም። እነርሱ የሚመጡት ከጠላት ነው፤ ነገር ግን ሰይጣን ለጉዳት ያሰበውን እያንዳንዱን ነገር እግዚአብሔር አንድ መልካም ነገር ለማድረግ ይጠቀምበታል። ሁኔታው መልካም ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር መልካም ነው፤ እኛም እርሱን መውደዳችንንና ማመናችንን ስንቀጥል ከመከራው ውስጥ መልካም ነገርን ያወጣል (ሮሜ 8÷28 ይመ)። ይህንን ማመን በአስቸጋሪ ወቅቶች ወደፊት እንድንገፋ ጥንካሬንና ድፍረትን ይሰጠናል። እኛ ተስፋ ሊኖረን ይገባል። በሕይወታችን የጌታን መልካምነት እንደምናይ ማመን አለብን (መዝሙር 27÷13 ይመ)

ወደ ሙሉ እምቅ ጎይላችሁ ድረሱ

ወደ እምቅ ጎይላችሁ መድረስ ችግሮችን ከምታስተናግዱበት ሁኔታ ጋር የተያያዘ መሆኑን በሙሉ ልቤ እኔ አምናለሁ። ዊንስተን ቸርችል፣ "የተሸነፉ ችግሮች የተገኙ እድሎች ናቸው" አለ። እኔም በሙሉ ልቤ እስማማበታለሁ። ችግሮችና ተግዳሮቶች እንዲያበሳጩአችሁ፣ እንዲያስፈራሩአችሁ፣ ወይም ተስፋ እንዲያስቆርጡአችሁ ከፈቀዳችሁላቸው ከዮ ልታሸንፉአቸው አትችሉም። ነገር ግን እነርሱን ፊት ለፊት ከተጋፈጣችኋቸውና የሚያጋጥሙአችሁን ችግሮች አልፋችሁ ወደፊት ከገፋችሁ፣ እንዲሁም በእነርሱ ውስጥ ሳላችሁ እጅ መስጠትን እምቢ ካላችሁና በድል አድራጊነት መንፈስ ወደፊት ከገፋችሁ፣ የተፈጠራችሁለትን እያንዳንዱን ነገር ለመሆን ክህሎትንና ቁርጠኝነትን እያዳበራችሁ እግዚአብሔር ለእናንተ ያቀደውን ማንኛውንም ነገር ትለማመዳላችሁ።

ከጥጥ እርሻ ወደ ድሮጅት

ወ/ሮ (ማዳም) ሲ.ጄ.ወከር፣ በአሜሪካ ውስጥ የመጀመሪያዋ አፍሮ አሜሪካዊት (አፍሪካ፣ አሜሪካዊት) ባለ ሚሊዮን ገንዘብ (ሚሊዮነር) ሴት ነበረች በ1867 የተወለደችው በሉዚያና የጥጥ እርሻ ጣቢያ ላይ ሲሆን ሣራ ብሪድላቭ ትባል ነበር። ወላጆቿም የቀድሞ ባሪያዎች ሲሆኑ እርሷ ገና የሰባት ዓመት ልጅ ሳለች ሁለቱም ተለዋት ሞቱ። እርሷና እህቷ በሕይወት ሊኖሩ የቻሉት በሉዚያናና በሚሲሲፒ እርሻዎች ውስጥ አስቸጋሪና አድካሚ የሆነውን የጥጥ ለቀማ ሥራ ለመሥራት ፈቃደኞች በመሆናቸው ነበር።

እርሷም በዐሥራ አራት ዓመቷ አንድ ሰው አገባችና ባሷ ከስድስት ዓመት በኋላ አንዲት ሴት ልጅ እንደወለዱ ሞተ። ከዚያም ሣራ ልጇን ይዛ አራት ወንድሞቿ የተሰካላቸው ፀጉር አስተካካዮች ሆነው ወደ ሚኖሩበት ወደ ሴይንት ሉዊስ ሚዚውሪ መጣችና በቀን 1.50 ዶላር እየተከፈላት በአጣቢነት ሥራ ተቀጠረች።

በ1890ዎቹ ውስጥ፣ ሣራ አብዛኛውን ፀጉርዋን እንድታጣ ያደረጋት ያልተለመደ የፀጉር መመለጥ ችግር ደረሰባት። ፀጉሯ ተመልሶ እንዲያድግ የተቻላትን ሁሉ ለማድረግ ሞከረች፣ ነገር ግን ምንም ውጤት አልተገኘም።

ሣራ ለአንድ የፀጉር ምርቶች ኩባንያ የሽያጭ ወኪልነት ሥራ አገኘችና ወደ ዴንቨር ኮሎራዶ መጣች፣ በዚያም ቻርሌስ ጆሴፍ ወከር የሚባል ሰው አገባችና "ወ/ሮ (ማዳም) ሲ.ጄ.ወከር" በመባል ታወቀች።

ሣራ አሁንም በፀጉር መመለጥ ችግር ላይ ነበረች፣ ነገር ግን በመጨረሻ ባልተለመደ ሁኔታ መፍትሔ አገኘች። እርሷም አንድ ሽማግሌ ሰውዬ ፀጉሯ ተመልሶ እንዲያድግ መደባለቅና መቀመም የሚያስፈልጓትን ቅመሞች ሲነግራት በሕልሟ አየች። በሚቀጥለው ቀን ቅመሞቹን ደባለቀችና መድኃኒቱን ስትሞክረው የተሳካ ሆነ!

ወ/ሮ ሲ.ጄ ወከር እርሷ ወደ ገበያ የምትወስደውና የምትሸጠው ምርት እንዳላት በፍጥነት ተገነዘበች፣ ስለዚህ የራሷን የንግድ ሥራ ክፈተችና "ወ/ሮ ወከር አስደናቂ የፀጉር ማላደጊያ" በሚል ስያሜ ማምረትና ማሠራጨት ጀመረች።

ወ/ሮ ወከር ንግዷ ጠንካራ ጅማሬ እንዲያገኝ በአሜሪካ ውስጥ በግሏ ስትንቀሳቀስ ለብዙ ማይልስ በእግሯ ትሄድ ነበር፣ በዚህም ጊዜ በየሰዉ በር እየሄደች ስለ ምርቷ ትናገርና አድማጮችም ተሰብስበው ስታገኝ መግለጫ ትሰጥ ነበር። በትጋትና በቁርጠኝነት፣ ለምርቷ ሽያጭና ገበያ ውጤታማነት ስልቶችን ማሳደግና ማስተካከሏን ቀጠለች።

በ1908፣ ወ/ሮ ወከር አዳጊ ለሆነው የንግድ ሥራዋ እንዲረዳት "የወከር የፀጉር ማለስለሻ" በሚል ስያሜ አንድን ቡድን የምታሠለጥንበት ትምህርት ቤት ለመክፈት ወደ ፒትስበርግ ፔንሲልቫኒያ ሄደች። ከሁለት ዓመት በኋላ፣ በእርሷ ጊዜ የፋብሪካ ከተማ በነበረው በኢንዲያናፖሊስ መኖሪያ ቤት መሠረተችና ለምርቶቿ ማምረቻና ማከፋፈያ አንድ ፋብሪካ አቋቋመች። በኢንዲያናፖሊስ ላለች፣ የመጀመሪያው ዓመት ከማለቁ በፊት ለአካባቢው የአፍሪካ አሜሪካውያን የ ዋይ ኤም ሲ ኤ ድርጅት ለመገንባት ወ/ሮ ወከር አንድ ሺ ዶላር አበረከተች፣ ይህም አስቀድሞ ጥጥ በመልቀም ራሷን ታስተዳድር ለነበረች ሴት ከፍተኛ ውጤት ነበር፣ ነገር ግን ይህ ሊገኝ የቻለው እርሷ ጠንክራ በመሥራቷና እጅ መስጠትን እምቢ በማለቷ ነበር።

ወ/ሮ ወከር በ1916፣ ከኢንዲያናፖሊስ ወደ ኒውዮርክ ሄደች፣ ይሁን እንጂ በኢንዲያናፖሊስ የነበራት ፋብሪካ በግንባር ቀደምትነት ባሠለጠነቻት ሴት መሪነት ሥራውን እንደ ቀጠለ ነበር። በፀጉሯ መመለጥ በገጠማት ችግር እጅ መስጠትን እምቢ ማለቷ፣ ወ/ሮ ወከር ጥጥ ከመልቀም ሥራ ወጥታ በቁንጅና ኢንዱስትሪ ግንባር ቀደምት ለመሆንና በአሜሪካ ውስጥ የሚሊዮን ገንዘብ ባለቤት (ሚሊዮነር) ለመሆን የመጀመሪያዋ አፍሪካ አሜሪካዊት ሴት ሆነች። የእርሷ ታሪክ እናንተ ተግዳሮት በገጠማችሁ ጊዜ፣ እጅ በመስጠት ፈንታ ወደ እምቅ ኃይላችሁ እስክትደርሱ ድረስ የፈጠራ ችሎታ ባለቤቶች እንድትሆኑ፣ ጠንክራችሁ እንድትሠሩና እንድትጸኑ አንዲያነቃቃችሁ ይሁን።

ምዕራፍ 7

አስፈላጊያችሁ በሆነው ነገር ላይ ኩቶ እጅ አትስጡ

"ዓሳ አጥማጆች ባሕሩ አደገኛና ማዕበሉም አስፈሪ መሆኑን ያውቃሉ፤ ነገር ግን እነዚህ አደጋዎች በባሕሩ ዳር ቆሞ ለመቅረት በቂ ምክንያቶች ሆነው አላገኙአቸውም"

ቪንሴንት ቫን ጉፍ

ለእናንተ አስፈላጊ ነገራችሁ ምንድን ነው? ስለ እርሱ ቆም ብላችሁ በምታስቡበት ጊዜ፣ በርግጥ የምትጨነቁለት ነገር ምንድን ነው? ሥራችሁ ነው? ወይስ፣ ዝናችሁ፣ ጤንነታችሁ፣ ቤተሰባችሁ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁ ግንኙነት፣ ንብረቶቻችሁ፣ ውጥናችሁ ወይስ የቆማችሁለት ዐላማ?

ለተለያዩ ሰዎች አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ ነገሮች የተለያዩ ናቸው። በብሉይ ኪዳን ዘመን፣ ነህምያ ለተባለው ሰው እጅግ አስፈላጊ የሆነው ነገር የኢየሩሳሌምን ከተማ የፈረሰ ቅጥር እንደገና መሥራት ነበር። ይህ ለእርሱ በጣም አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ በመሄድ ሥራውን በበላይነት ለመቈጣጠር እንዲችል እንዲፈቅድለት፣ አለቃውን የፋርስን ንጉሥ ፈቃድ ጠየቀ፤ ንጉሡም ፈቀደለት።

ታሪኩን በምታነቡበት ጊዜ እንደምትገነዘቡት፣ ነህምያ የድል አድራጊነት መንፈስ ነበረው። ለእርሱ በጣም አስፈላጊ የነበረው ይህ እቅድ የእግዚአብሔር ነበረ፣ እቅዱን እንዲፈጽመው እግዚአብሔር ጠርቶት ነበረ፣ ሆኖም እቅዱን ለመፈጸም በሚሞክርበት ጊዜ የተቃውሞ፣ የማሽሟጠጥና የማስፈራራት ማዕበል ገጠመው። በተመሳሳይ መንገድ፣

ለእናንተ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ለማድረግ በምትሞክሩበት ጊዜ የተለያየ ዐይነት ማዕበል ይገጥማችኋል። ማዕበሎቹን እንዴት እንደምታስተናግዱና በአሸናፊነት እንደምትወጡ የነህምያ ታሪክ ያስተምራችኋል።

ተገን ይኑራችሁ

ከተፈጥሮ ማዕበል በሰላም ለመጠበቅ ከሁሉ የተሻለው መንገድ ተገን/መጠለያ/ ማግኘት ነው። ተገን ከሌላችሁ በስተቀር ነፋሱ ወዲያና ወዲህ ያንገላታችኋል፣ ዝናቡም በግልጽ ለማየት እንዳትችሉ ያደርጋችኋል። ከዚህም በላይ፣ በመብረቅ ልትመቱ ትችላላችሁ። ተገን ካላገኛችሁ በስተቀር፣ ማዕበሉ በቁጥጥሩ ሥር ያደርጋችኋል። ነገር ግን በተገን ውስጥ ከሆናችሁ ማዕበሉን በሰላም ታሳልፉትና ካለፈም በኋላ ለመሥራት የምትፈልጉትን ነገር እንድትሠሩ መልካም አቋም ይኖራችኋል።

መዝሙር 91÷1 የሕይወት መንፈሳዊ ማዕበሎች መመሪያ ይሰጠናል፦ "በልዑል መጠጊያ የሚኖር [የእርሱን ኀይል ማንም ጠላት ሊቋቋመው በማይችል] ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ሥር ያድራል" ይላል። ማዕበል ሕይወታችሁን በሚመታው ጊዜ በመጀመሪያ መሮጥ ያለባችሁ ወደ ልዑል መጠጊያ ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ሀልዎት (መገኘት) ነው። ቃሉን አንብቡ፤ ጸልዩ፤ እርሱን አምልኩት፤ የመከራ ነፋሳት ሲነፍሱ በእርሱ እንደምትተማመኑ ንገሩት። እነዚህን ማንም ጠላት ሊቋቋማቸው የማይችላቸው መንፈሳዊ ሥርዐቶች ናቸው። እነዚህን ሥርዐቶች ተግባራዊ በምታደርጉበት ጊዜ በራሳችሁ ዙሪያ የመከላከያ መንፈሳዊ ቅጥሮችን ትገነባላችሁ። ልምምዶቹ የሕይወትን ማዕበል አያስወግዱም፤ ነገር ግን መከላከያ በመሆን በማዕበሎቹ ውስጥ ጠንክራችሁ ለመቆም እንድትችሉ ያደርጓችኋል።

ብዙዎቹ የሕይወት ማዕበሎች በቀጥታ ከጠላት የሚመጡ ናቸው። ጠላት ሕይወትን፣ ሕልምን፣ ትዳርን፣ ቤተሰብን፣ የንግድ ሥራን፣ ትምህርት ቤትን፣ ወይም መልከአ ምድራዊ አካባቢን የሚያጠፋ ሁኔታዎችን በማቀነባበር ዋና ነው። እርሱ በሕይወታችሁ

ዙሪያ የመከላከያ ቅጥር እንድትገነቡ አይፈልግም። በተሳካ ሁኔታ ጥቃት ለመሠንዘር እንዲመቸው ቅጥሮቹ ሁሉ እንዲፈርሱ ይፈልጋል።

ቅጥር ጠላትን በውጪ ያስቀረዋል

ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች በሕዝቡ ላይ ችግር እንደሚፈጥሩባቸው ተመለከተ፣ ምክንያቱም ጠላቶቹ እንዳይገቡ ለመከላከል ከተማዋ ቅጥር ስላልነበራት ነው። ነህምያ በመጀመሪያ የኢየሩሳሌምን ሰዎች በተገናኛቸው ጊዜ እንዲህ አለ፤ "ያለንበትን ክፉ ሁኔታ (ጉስቁልና) ይኸው ታያላችሁ፤ ኢየሩሳሌም ፈርሳለች፣ በሮቿም በእሳት ጋይተዋል፣ አሁንም ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና እንሥራ፣ ከእንግዲህስ መሣለቂያ አንሆንም አልኋቸው። እንዲሁም መልካሚቱ የአምላኬ እጅ በእኔ ላይ እንደነበረችና ንጉሡም ምን እንዳለኝ ነገርኋቸው። እነርሱም 'እንደገና መሥራቱን እንጀምር!' ካሉ በኋላ ይህን መልካም ሥራ ጀመሩ" (ነህምያ 2÷17-18)

ሕይወታችሁ እንደተበላሸና ጠላትም ይህን ብልሽት አይቶ እንደሚዋጋችሁ ከተገነዘባችሁ የዚህ ታሪክ ተመሳሳይ መርሕ ለእናንተም ይጠቅማል። እናንተ ቅጥሮቻችሁን አልጠበቃችሁም፣ መከላከያ የላችሁም፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር እርዳታ ትክክለኛውን ዐይነት ሕይወት ለመገንባት ትችላላችሁ፣ ከጠላት ትጠበቁ ዘንድ በዙሪያችሁ የመከላከያ ቅጥሮች መገንባት ልትጀምሩ ትችላላችሁ። ጠላት ወደ እናንተ ሊመጣ ይችላል፣ ነገር ግን እቅዱ አይሳካለትም።

የሕይወት ማዕበሎች ለረጅም ጊዜ በታትነውና ሰነጣጥቀው አስቀምጠዋችሁ ከሆነና የመከላከያ ቅጥር ለመገንባት የተዘጋጃችሁ ከሆነ፣ እኔ ስለ እናንተ ደስ ብሎኛል። ነገር ግን ይህንን ያለ ተቃውሞ እናደርገዋለን ብላችሁ አትጠብቁ። ይህ የሕይወት ተጨባጭ ሁኔታ ነው። እናንተ ወደፊት በተራመዳችሁና ትክክለኛውን ነገር ባደረጋችሁ ቁጥር ጠላት ይበሳጫል። ነገር ግን እናንተ ስለ ተቃውሞው መጨነቅ አያስፈልጋችሁም፣ ምክንያቱም ማንኛውንም ጦርነት ለማሸነፍ በቂ ኀይል ስላላችሁ ነው። እግዚአብሔር ለእናንተ፣ በእናንተ ውስጥ፣

ከእናንተ ጋርና በእናንተ ዙሪያ ነው። ደግሞም እርሱ የራሳችሁን ጦርነት እንድታሸንፉ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም የራሳቸውን ጦርነት እንዲያሸንፉ ለመርዳት በእናንተ አማካይነት ይሠራል።

ማዕበል እየተዘጋጀ ነው

አይሁዶቹ "ለመልካሙ ሥራ እጆቻቸውን እንደ አበረቱ" ወዲያውኑ ተቃውሞ ተነሣ። (ጠላቶች) የግንባታው ሥራ እየተካሄደ መሆኑን በሰሙ ጊዜ ነህምያንና አይሁዶቹን ማሸማቀጥ ጀመሩ። በተለይ ሦስት ሰዎች፦ ሰንበላጥ፣ ጦብያና ጌሳም- በእነርሱ ላይ ያፌዙባቸውና ይቀልዱባቸው ጀመር። "አፈሙብን፣ አንቋሸሹንም፣ እንዲሁም የምታደርጉት ይህ ምንድን ነው? ... አሉ" (ነህምያ 2÷19)።

እኔ ተመሳሳይ የሆነ ተሞክሮን አስታውሳለሁ። እኔ የእግዚአብሔርን ጥሪ በተቀበልሁበት ጊዜ ሰዎች ምን ዐይነት ምላሽ እንደሰጡ ቀደም ሲል ገልጬ ነበር። ብዙ ሰዎች እየሳቁ "ምን እያደረግሽ ይመስልሻል?" አሉኝ። ይህ ለእኔ እጅግ አስቸጋሪ ጊዜ ነበር፣ ነገር ግን በተቃውሞው ማዕበል ውስጥ በጽናት ለመቆም የተቻለኝን ሁሉ አደረግሁ። ቃሉን በማጥናት፣ በመጸለይና በእርሱ ሀልዎት ውስጥ ጊዜን በማሳለፍ በተቻለኝ መጠን ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ለማድረግ የምችለውን ሁሉ አደረግሁ። የአስተሳሰብ ዝንባሌዬን፣ ትዳሬንና ከልጆቼ ጋር ያለኝን ግንኙነት ለማሻሻል ጥረት አደረግሁ። ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ሲረዱኝና ሲስቁብኝ ሳለሁ እንኳ የእርሱን ፍቅርና ቸርነት ለማወቅ በመሞከር ችግሮቹን ለማሸነፍና ጤናማ የሆነ የራሴን ማንነት ለመገንባት ከእግዚአብሔር ጋር መሥራትን ቀጠልሁ። ይህንን ሳደርግ የመከላከያ ቅጥር እየሠራሁ ነበር። በተቻለኝ መጠን በትጋት በቅጥሬ ላይ ጡቦችን እያስቀመጥሁ ነበር፣ ጠላት ግን እኔን መዋጋቱን እንደ ቀጠለ ነበር።

በተቻላችሁ መጠን ትክክለኛውን ነገር በማድረግ ላይ ሳላችሁ፣ ማዕበሉ በይበልጥ እየከፋ መሄዱ ተሰምቶአችሁ ያውቃል? ለእኔ በተለይ በጣም አስቸጋሪ የነበረበትን የተለየ አንድ ሁኔታ አስታውሳለሁ። ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ጓደኛዬ እንደሆነች ያሰብኳት

ሴት ወደ እኔ መጣችና፤ "ጆይስ እግዚአብሔር በመላ አገሪቱ ውስጥ በሴቶች ከሚካሄዱት አገልግሎቶች አንዱን እግዚአብሔር ለእንቺ መስጠቱን እንደምታምኚ አንድ ሰው ነገረኝ፤ አንቺ እንደዚህ ብለሻል?" አለኝ።

እኔም፣ "አዎ፣ እግዚአብሔር ይህንን እንደተናገረኝ በእርግጥ አምናለሁ" የሚል ምላሽ ሰጠሁት።

ይህች ሴት ሾክክ አለችና፣ "እሺ እንግዲህ እውነቱን ልንገርሽ፣ አንዳንዶቻችን ስለ አገልግሎቱ ስንነጋገር ነበር፣ እናም ይህ በእንቺ ተክለ ሰውነት የማይቻል ነገር እንደሆነ አስበናል" አለችኝ።

እንደዚህ ያሉትን አስተያየቶች መስማት ማለት ያለ መከላከያ በአስከፊ ማዕበል ውስጥ እንደ መሆን ማለት ነው። ሰንበላጥ፣ ጡቢያና ጌላም ወደ ነህምያ መጥተው እየሳቁ "ይህ የምታደርጉት ነገር ምንድን ነው? ይህን ልትሠሩ አትችሉም" ባሉት ጊዜ ነህምያ ይሰማው የነበረው ዐይነት ስሜት ተሰማኝ።

ነህምያ ግን ጸንቶ ቆመ፣ የድል አድራጊነትም የአሸናፊ መንፈስ በማሳየት "የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፣ እኛ ባሪያዎቹ እንደገና ሥራውን እንጀምራለን፣ እናንተ ግን በኢየሩሳሌም ድርሻ ወይም ይገባናል የምትሉት ወይም የታሪክ መታሰቢያ የላችሁም" አላቸው (ነህምያ 2 ÷ 20)።

ጠላት እናንተን በመቃወም ሲመጣ፣ እናንተም "አንተ በዚህ መብት የለህም። ከእኔ ጋር ምንም ድርሻ የለህም፣ እግዚአብሔር ለእኔ ሕይወት ያለውን ፈቃድም ልታደናቅፍ አትችልም!" ማለት ይገባችኋል። እናንተ ሕይወታችሁን ለኢየሱስ ክርስቶስ ከሰጣችሁ፣ የእርሱ ገንዘብ ናችሁ እንጂ የዲያብሎስ አይደላችሁም። ማድረግ ያለባችሁ ይህንን ሐቅ ለጠላት ማስታወስና መቃወም ብቻ ነው። እናንተ ድምፃችሁን ከፍ ማድረግ ወይም ትርኢታዊ መሆን አይጠበቅባችሁም፣ ነገር ግን በክርስቶስ ያላችሁን ሥልጣን በመጠቀም፣ "መንገድ የለም፣ ዲያብሎስ፣ አንተ ልታስቆመኝ አትችልም፣ እኔ በዚህ

አልሸነፍም፣ ምንም ነገር ብትወረውርብኝ አልሸሽም!" ማለት ያስፈልጋችኋል።

እኔም አልሸሸም አልሁ፣ ሴትዮዋና ጓደኞቿ እንደማይሳካልኝ አስበው የነገሩኝ ነገር በመጨረሻው ለእኔ ሲሠራ ተገኘ። እርሱ እንድናደርገው የነገረንን ነገር ማድረጋችንን ብንቀጥል እግዚአብሔር ሁልጊዜ ለእኛ ይቆማል። አንድ ሰው አይሳካልህም ስላላችሁ ብቻ ከቶ እጅ አትስጡ።

> አንድ ሰው አይሳካልህም ስላላችሁ ብቻ ከቶ እጅ አትስጡ።

የሕይወት ማዕበል ውስጥ ጠላትን ለመቃወም እኛ በርግጥ ቁርጠኞች መሆን አለብን። አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ እንሸነፋለን። ትንሽ የተሰፋ መቁረጥ ስሜት ያድርብናል፣ ወይም የሕይወት "ሰንበላጦች" ስሜታችንን ይጐዱታል፣ ከዚያም በጫናው ምክንያት እንዝለፈለፋለን። እናንተ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ለአሸናፊዎች እንደምትበልጡ ከቶ አትርሱ (ሮሜ 8÷37 ይመ)።

እድገትን የሚወደው ሁሉም ሰው አይደለም

ሰንበላጥ የታወቀ (አዲጋች) ጠላት ነበር፣ እርሱ በቀላሉ እጅ አልሰጠም። ተቃውሞው እያለ የከተማዋ ቅጥር ግንባታ እንደ ቀጠለ በሰማ ጊዜ፣ "ተቆጣ፣ እጅግም ተበሳጨ፣ በአይሁድም ላይ ተሣለቀ" (ነህምያ 4÷1)። እነርሱ በይበልጥ በሠሩ መጠን፣ የእርሱም ቁጣ ተባባሰ።

ምናልባት ሌሎች ሲያድጉ፣ ራሳቸውን ሲያሻሽሉ፣ ወይም አንድ ዐዲስና የተለየ ነገር ሲሠሩ የሚቆጡ ሰዎችን እናንተም ታውቁ ይሆናል። ሰዎች ስለ እናንተ እድገት የሚቆጡት ለምንድን ነው? ምክንያቱም እነርሱ ራሳቸው ለማደግ የማይፈልጉ ከሆነ፣ እናንተም እንድታድጉ ስለማይፈልጉ ነው። እነርሱ ሕይወታቸውን ለማሻሻል ወይም ሕልማቸውን እውን ለማድረግ ያለመፈለጋቸውን ሐቅ ከመቀበል ይልቅ፣ በእናንተ ላይ መፍረድና መተቸት ነይቀናቸዋል። ለወደፊት ኑሮአቸው ከመሥራትና ግባቸውን ለመፈጸም ጥረት ከማድረግ ይልቅ፣

ይቆጡና እናንተ አንድ ችግር ያለባችሁ ለማስመሰል ይሞክራሉ። በዚህም ሁኔታ፣ እነርሱ ራሳቸው አንድ ችግር ሊኖርባቸው የሚችል መሆኑን ማሰብ ይሳናቸዋል። ይህም "ስህተትን በሌላው ላይ ማላከክ" (ብሌም ሺፍቲንግ) ይባላል፤ ይህንንም የሚያደርጉ ሰዎች ትክክለኛ ምርጫ ባለማድረጋቸው መነቀፍን ስለማይፈልጉ ትኩረቱን ወደ እናንተ ያዙሩና እናንተን ዋጋ ቢስ ለማድረግ ይሞክራሉ።

ሰንበላጥና ተባባሪዎቹ "እጅግ የተበሳጨት" ነህምያ ሰዎችን የመርዳትን ጥረት ስለመራና የማህበረሰቡን ኑሮ ስላሻሻለ ነበር። እናንተም ራሳችሁንና የአካባቢያችሁን ሰዎች ለመርዳት ጥረት ስታደርጉ፣ ስለጥረታችሁ የሚቆጣ አንድ ሰው ብታገኙ አትደነቁ። በዚያ ማዕበል ውስጥ መቆም ብቻ ይጠበቅባችኋል። ሰላም ይኑራችሁ፤ ከዚያም ልክ ነው ብላችሁ በልባችሁ የምታምኑበትን ነገር አድርጉ።

ምን ዐይነት ብልሽት!

በነህምያ 4÷2 እንደተጻፈው ሰንበላጥ ፋክራውን ቀጠለ፤ "በተባባሪዎቹና በሰማርያ ሠራዊት ፊት፣ እነዚህ ደካማ አይሁዶች ምን እያደረጉ ነው? ቅጥራቸውን መልሰው [በራሳቸው ፈቃድ] ሊሠሩ ነውን? መሥዋዕት [ለአምላካቸው ጉበ] ሊያቀርቡ ነውን? በአንዲት ጀንበር ሠርተው ሊጨርሱ ነውን? እንደዚያ ተቃጥሎ የፍርስራሽ ክምር የሆነውን ድንጋይ ነፍስ ሊዘሩበት ይችላሉን?" አለ።

በመሠረቱ፣ ሰንበላጥ የሚለው፣ "ይህ ብልሽት በጣም ትልቅ ስለሆነ እንደገና ሊሠራ አይችልም!" ነበር። አዎ፣ ቅጥሮቹ በጣም ከመበላሸታቸው የተነሣ ከተሰባበሩ ድንጋዮች በስተቀር ምንም ነገር አልነበራቸውም። ድንጋዮቹም - ቢያንስ ቢያንስ ያለብዙ ጥረት - ቅጥሮቹን ለመገንባት እንዲቻል ዕቃዎች ጥሩ የግንባታ ዕቃዎች አልነበሩም። በሰንበላጥ አስተሳሰብ ቅጥሮቹን መሥራት የተሳሳተ አሳብ ነበር። ድንጋዮቹ በጣም ተበላሽተው ነበር።

ጠላት በእናንተ ላይ ተመሳሳይ ክስ ሊሠነዝርባችሁ ይችላል፤ "እንደገና እጀምራለሁ ስትል ምን ማለትህ ነው? ሕይወትህ እንዴት

እንደተበላሸ ተመልከት!" "አንተ የኮሌጅ ዲግሪ የምታገኝበት መንገድ የለም፤ አእምሮህ እንደዚህ ተበላሽቶ!" "ልጆችህን ወደ ኮሌጅ ለመላክ ገንዘብ የምትቆጥብ ይመስልሃል? የገንዘብ አቅምህ በጣም ስለደከመ ባንክም ሊያስተካክለው አይችልም!" ሊላችሁ ይችላል። ጠላት የሚላችሁ ምንም ይሁን ምን፣ እናንተ ለእግዚአብሔር ትልቅ ብልሽት አለመሆናችሁን እንድታውቁ እፈልጋለሁ፤ ለመስተካከል ከእርሱ አቅም በላይ የሆነ ምንም ነገር የለም።

የተበላሸ ሕይወት ነበረ ቢባል፣ እርሱ የእኔ ነበር። ለመሻሻል መሞከር ዋጋ የለውም ብሎ ለማመን ምክንያት ቢኖር ኖሮ፣ እኔ ነበርክ። ጠላትም ይህን ያውቅ ነበር። ከቶ የተስተካከለ ሕይወት ሊኖረኝ እንደማይችል ሊያሳምነኝ ሞክሮ ነበር። እኔ ከቶ "ልስተካከል" እንደማልችል ነገረኝ፤ ከሥጋ ዘመድ ጋር የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሰለባ ስለሆንኩ ጤናማ የሆነ የራሴ ግንኙነት ሊኖረኝ እንደማይችል ነገረኝ። ወንዶች በደል ስለ አደረሱብኝ ወንዶችን ማመን እንደማልችል፣ ለባሌ ትክክለኛ የሆነ የመዝሙር ግንኙነት ከቶ ሊኖረኝ እንደማይችል፣ በእኔ ውስጥ ታምቆ በቆየው ቁጣ ምክንያት በአካባቢዬ ያለውን ማንኛውንም ነገር ለመቆጣጠር ከመሞከር፣ ወይም በቁጣ ከመገንፈል ልቆጠብ እንደማልችል ነገረኝ። በአስተዳደጌ ምክንያት ጣፋጭ፣ ጥሩና ርህሩህ ልሆን እንደማልችል፣ ሁልጊዜ ሸካራ፣ ጨካኝ፣ ክባድ፣ ባለጌ፣ እና ኋላ ቀር እንደምሆን ነገረኝ። እኔም ለመለወጥና እግዚአብሔር እንድሆን የፈለገው ዐይነት ሴት ለመሆን ከፍተኛ ፍላጐት አደረብኝ፤ ነገር ግን በአእምሮዬና በስሜቶቼ ውስጥ በነበረው ውጊያ በጥንካሬ መቆም ነበረብኝ።

ዲያብሎስ ሐሰተኛ ነው፤ ነገሩ ይኸው ነው (ዮሐንስ 8÷44 ይመ)። ጠላት እውነቱን አይነግራችሁም፤ እርሱ እናንተን ለማጥፋት ሊነግራችሁ የፈለገውን ነገር ይነግራችኋል። አእምሮአችሁንና ስሜቶቻችሁን ያለ ርህራሄ ይዋጋል። ችግሮቻችሁ በጣም ትልቅ እንደሆኑ በማሰብ እጅ ለመስጠት በምትፈተኑበት ጊዜ ልብ አድርጉ፤ ዲያብሎስ ሐሰተኛ ነው፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም!

ዲያብሎስ እድገትን ሁሉ ይጠላል። የተወሰነ ክብደት ለመቀነስ ፈልጋችሁ ለአንድ ሳምንት አመጋገባችሁን ብታስተካክሉና ከዚያ በኋላ ለአንድ ቀን በአመጋገብ ብትሳሳቱ እርሱ ይመጣና እንዲህ ይላችኋል፦ "አየህ? ይህ በጣም ከባድ ነው። ልትዘልቀው አትችልም። አንተ ሁልጊዜ ክብደትህ ከመጠን በላይ ነው፤ የአመጋገብ ልምድህም በውስጥህ ስለ አደገብህ አሁን ለመለወጥ አትችልም!"

ዲያብሎስ የክስ ማዕበል ሲያወርድባችሁ፣ ብድግ በሉና "*ሰማ፣ ሐሰተኛው!* ትንሽ ተሳስቼአለሁ፤ ግን ነገሩ ገና አላለቀም! ግቦቼን እፈጽማለሁ። እግዚአብሔር ያዘዘኝን አደርጋለሁ። እርሱም ዋጋ ያለው ነገር ነው፤ አንተ ልታስቆመኝ አትችልም!" በሉት። የእምነትን ገድል ተጋደሉ። እናንተ የእግዚአብሔር የጦር ሠራዊት ወታደሮች ናችሁ፤ እርሱም በእናንተ ወገን ነው።

ሁላችንም አንዳንድ ነገሮችን በትክክል ማድረግን ስንማር ልንሳሳት እንችላለን፤ ነገር ግን በየቀኑ ዐዲስ ጅማሬ ለማድረግ እንችላለን። ሁሉም ሕጻናት በእግራቸው መሄድን ሲማሩ ይወድቃሉ። ሲያደናቅፋቸው በወለሉ ላይ ተኝተው አይቀሩም፣ ሲያለቅሱም አይኖሩም። ይነሣሉ፣ አቧራውን ያራግፋሉ፣ እንደገናም ይሞክራሉ! ምንም ያህል ብዙ ጊዜ ቢወድቁ፣ እጅ አይሰጡም።

ጸልዩ!

በነህምያ 4÷4፣ እኛ በማዕበል ውስጥ ፀንተን ለመቆም በምንሞክርበት ጊዜ ማስታወስ ያለብንን በጣም አስፈላጊ ሦስት ቃላት እናገኛለን፤ "እናም ነህምያ ጸለየ።" በእርሱ ላይ ለተሠነዘረው ጥቃት ማለትም ለሳቁ፣ ለቁጣው፣ ለማንፍልንቱ፣ ለፍርዱ፣ ለትችቱ፣ የግቡ ፍጻሜ የማይቻል ነው ተብሎ ስለመነገሩ ምን ምላሽ ሰጠ? ጸለየ!

እስኪ ልጠይቃችሁ፣ እናንተ በፈራችሁ፣ ወይም ማስፈራራያ በደረሳችሁ ጊዜ ሁሉ ብትጸልዩ ምን ይሆናል? በተናደዳችሁ፣ ወይም አንድ ሰው ስሜታችሁን በጉዳው ጊዜ ሁሉ ብትጸልዩ ምን ይሆናል? አንድ ዐይነት ፍርድ ወይም ትችት በእናንተ ላይ በተሠነዘረ ጊዜ ሁሉ፣

ብትጸልዩ ምን ይሆናል? ሕይወታችሁ የተለየ ይሆናል? እነዚያን ማዕበሎች በተሻለ ሁኔታ መቋቋም ትችላላችሁ? አዎን ትችላላችሁ።

ከነህምያ ጸሎት በጣም አስፈላጊ የሆነ ትምህርት ልንማር እንችላለን፤ "አምላካችን ሆይ፣ ተንቀናልና ስማን። ስድባቸውን በራሳቸው ላይ አውርድባቸው፤ በምርኮ ምድር እንዲበዘበዙ አሳልፈህ ስጣቸው አለ (ነህምያ 4÷4)። ነህምያ በራሱ ጠላቶቹን ፍለጋ እንዳልሄደ ልብ አድርጉ፤ እርሱ እግዚአብሔር እንዲገናኛቸው ጠየቀ። የእርሱ አስተሳሰብ፣ "እኔ የማደርገው የእንተን ፈቃድ ነው! አንተ ይህን ቅጥር እንድሠራ ስለነገርከኝ እርሱን እየሠራሁ ነው። ስለዚህ ከጠላቶቼ ጠብቀኝ!" ነው።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር አንድ ነገር እንድናደርግ ወይም አንድ ሥራ እንድንፈጽም ይነግረንና እኛም መሥራት እንጀምራለን። ነገር ግን ጠላት በእኛ ላይ ይነሣል፤ እኛም ለመዋጋት ወደ እርሱ ዘወር ስንል ከእግዚአብሔር ዘወር እንላለን። ጠላትም በድንገት የእኛን ትኩረት ወደ ራሱ ይስበዋል። እግዚአብሔር ጣልቃ እንዲገባ ወደ እርሱ በመጸለይ ፈንታ ጠላትን በመዋጋት ጊዜያችንን እናጠፋለን።

ነህምያ ጠላቶቹ ትኩረቱን እንዳይቆጣጠሩት የሚያደርግ በቂ እውቀት ነበረው። ጠላቶች መኖራቸውን አውቆአል፤ ነገር ግን እርሱ ዐይኖቹን በእግዚአብሔርና እርሱ ባዘዘው ሥራ ላይ አደረገ። ወደ እግዚአብሔር ጸለየና የሚዋጉትን ጠላቶች አንድ ነገር እንዲያደርግለት ጠየቀ።

አብዛኞቻችን እ.ኤ.አ መስከረም 11፣2001 የሆነውን ነገር ከቶ አንረሳውም። በቅርብ ጊዜ በዓለም የንግድ ማዕከል በሁለተኛው ሕንፃ(ግንብ) ውስጥ ይኖር የነበረውንና ሕይወቱ በተአምር የተረፈውን ስታንሌ ፕሬይምናዝ የተባለውን የባንክ ባለቤት ታሪክ አነበብኩ። ስታንሌ ታሪኩን እንዲህ በማለት ያስታውሰዋል፤ "በአንድ ልዩ ምክንያት፣ የዚያን ዕለት ማለዳ ጥቂት ጊዜዬን በጸሎት ለጌታ ሰጠሁት። እኔም 'ጌታ ሆይ፣ እኔንና የምወዳቸውን ሁሉ በክብር ደምህ

ሽፍንን'። እናም ምንም እንኳ የተናገርሁትን በሙሉ ልቤ ያመንሁት ቢሆንም፣ ደግሜ፣ ደግሜ፣ ደግሜ አልሁት።"

ስታንሌ በሰማንያ አንደኛው ፎቅ ላይ ወዳለው ቢሮው እንደ ደረሰ፣ ወዲያውኑ በመስኮት ሲመለከት ቁጥር አንድ ግንብ በእሳት ተያይዞ አየ። እርሱና አንድ የሥራ ባልደረባው ሕንጻውን ለመልቀቅ ወሰኑ፣ ነገር ግን አንድ የደህንነት ጠባቂ ቁጥር ሁለት ግንብ በደህና ሁኔታ መሆኑን ሲነግረው ወደ ቢሮው ተመለሰ።

ስታንሌ ወደ ቢሮው እንደተመለሰ ወዲያውኑ አንድ ሰው ስልክ ደወለለትና ዜና እያዳመጠ እንደሆነ ጠየቀው። እርሱም ሁሉም ነገር ደህና ነው በማለት ምላሽ ሰጠ። ከዚያም አንድ የአሜሪካ አየር መንገድ ጄት አውሮፕላን በቀጥታ ወደ እርሱ ሲመጣ አየ። እርሱም ለማድረግ ያሰበው በጠረጴዛው ሥር ገብቶ፣ በእጎቱ ማህፀን ውስጥ እንዳለ ሽል፣ መጠቅለልና አውሮፕላኑ ከእርሱ በሃያ ጫማ እርቀት ሲከሰከስና ሲፈነዳ ሲያይ መጸለይ ብቻ ነበር። እርሱም አንድ ጊዜ እዚያ ከደረሰ በኋላ፣ እርሱ እንደተናገረው "ያለ አንዳች ጥርጥር ጌታ እንደሚጠብቀው" አወቀ።

ስታንሌ የአውሮርላኑ አንድ ክንፍ ወደ እርሱ ቢሮ በሚወስደው በር ላይ በእሳት ተያይዞ አየ። በተአምራዊ ሁኔታ ምንም ስላልተጐዳ ከሕንጻው መውጣት እንደሚያስፈልገው አወቀ፣ ነገር ግን በፍርስራሹ ስለተጠመደ መንቀሳቀስ አልቻለም።

ስታንሌ በጎይል እየጸለየ፣ "ጌታ ሆይ፣ አንተ ተቆጣጠር፣ ይህ አሁን የአንተ ችግር ነው" እያለ እግዚአብሔር ሕይወቱን እንዲያተርፍለት ጠየቀ። ከዚያም በድንገት ጥንካሬ በአካሉ ውስጥ እንደገባና አሥሬው የያዙትን ፍርስራሾች እያራገፈ እንደሄደ ሲያውቅ "በሕይወት ያለ እጅግ ጠንካራ ሰው" መሆኑን ያስታውሳል። ከዚያም "ጌታ ሆይ፣ ወደምወዳቸውና ወደ ቤቱ መሄድ አለብኝ። ይህ መሆን አለበት። አንተም እኔን መርዳት አለብህ" እያለ በዙሪያው ባለው የፍርስራሽ ክምር እየወጣና የእሳቱን ነበልባል እየሸሸ ሄደ።

ስታንሌ ተቆርጦና ተቀጥቅጦ በቢሮው አጠገብ ባለው አደገኛ ፍርስራሽ ላይ እየተደናቀፈ ሲራመድ መውጫዎቹ ሁሉ እንደተዘጉ ተመለከተ። እርሱም በአንድ ግድግዳ ላይ ተይዞ ነበር። ከዚያም ተንበረከከና እንደገና መጸለይ ጀመረ፣ ቀጥሎም ከግድግዳው በሌላኛው በኩል አንድ ሰው አየና "ኢየሱስን ታውቀዋለህ?" ብሎ ጠየቀው። ሰውዬውም አዎን ባለ ጊዜ፣ ሁለቱም ጸለዩና በግድግዳው ውስጥ ለማለፍ እንዲችሉ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ጠየቁት። ይህንንም አደረጉና ስታንሌ በአንድ ትንሽ ቀዳዳ ውስጥ አልፎ ሄደና በመውደቅ ላይ ወዳለው ሕንጻ ደረጃ ሊደርስ ቻለ።

እርሱና ዐዲሱ ጓደኛው ደረጃውን ሲወርዱ በእያንዳንዱ ፎቅ መሰል ላይ ሲደርሱ እርዳታ የሚፈልግ አንድ ሰው እንዳለ ይመልከቱ ነበር። ወደ መሬት እንደደረሱም፣ ያዩአቸው "ሩጡ! ሩጡ!" እያሉ የሚጮኹ የእሳት አደጋ ሠራተኞችን ብቻ ነበር።

ሰዎቹ ለመሮጥ ፈልገው ነበር፣ ነገር ግን በእሳት ተከብበው ነበር። በእሳቱ ውስጥ ሮጠው ካላለፉ በስተቀር ተቃጥለው ይሞታሉ። በሕንጻው ውስጥ ባለው የውሃ መርጫ መሣሪያ ራሳቸውን በውሃ እየረጩ በመጨረሻ በነበልባሉ ውስጥ እየበረሩ በማለፍ ሊተርፉ ቻሉ።

ስታንሌ ለሕይወት በሚያሰጋ ሁኔታ ውስጥ ለመትረፍ ቆርጦ ነበር፣ ነገር ግን ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ሊፈጽመው አልቻለም። የሰው ቁርጠኝነት እጅ ላለመስጠት በጣም ትልቅ ነገር ቢሆንም፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍን መርሳት የለብንም፣ በራሳችን ብርታት ብቻ ነገሮችን ለመፈጸም ፈጽሞ ሳንሞክር ለሚያስፈልገን መሻሻል በእዚአብሔር ላይ እየተደገፍን፣ ነገር ግን የራሳችንን ድርሻ ማበርከት ያስፈልገናል።

እኔም ይህን እንድታውቁ እፈልጋለሁ፣ በርግጥ ጠላት የእናንተ ችግር አይደለም፣ ጠላት የእግዚአብሔር ችግር ነው። ትኩረታችሁን እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ሥራና እድል ላይ አንስታችሁ በጠላት ላይ በምታተኩሩበት ጊዜ ጊዜያችሁን ታጠፋላችሁ። ሰይጣን አሳባችሁን ከበታተነው፣ በመጨረሻው እንጀሚያሸንፋችሁ ያውቃል። እግዚአብሔር

የእናንተ ተከላካይ ነው፤ እርሱ የእናንተን ጦርነት ለመዋጋት ቃል ገብቶአል። ስለዚህ ጠላት በሕይወታችሁ ላይ ማዕበል ሊያስነሣ ሲጀምር እንደ ነህምያ ሁኑ፤ ጸልዩ።

የመሥራት ልብና አእምሮ

ነህምያ በምዕራፍ 4 ውስጥ ጥሩ መግለጫ ሰጥቶአል፤ "ሕዝቡ ከልቡ ስለሚሠራ፤ ቅጥሩን እኩሌታው ድረስ መልሰን ሠራነው" አለ (ቁጥር 6)። ምንም እንኳ ጠላቶቻቸው ያለ ማሰለስ ወደ እነርሱ የመጡባቸው ቢሆንም የነህምያ ሰዎች ለመሥራት ቆርጠው ነበር። ጠላቶቻቸው ግትር ቢሆኑባቸውም እንኳ፤ ከመሥራት አላቋረጡም!

እናንተም ቆራጦች ከሆናችሁ ጠላት ወደ ኋላ ሊገትታችሁ አይችልም! ከጠላት የበለጠ ቁርጠኞች መሆን ያስፈልጋችኋል፤ ነገር ግን ይህን ለማድረግ የምትችሉት እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ስለሆነ ነው። ጠላት በጽናት ሊቃወማችሁ ይችላል፤ ነገር ግን እናንተ እጅ መስጠትን እምቢ ካላችሁ የመከላከያ ቅጥር ለመሥራትና ወደ ሕይወታችሁ ግብ ለመድረስ ትችላላችሁ።

የቅጥሩ ግንባታ ወደ ላይ ማደግ ብቻ ሳይሆን በቅጥሩ ላይ የነበሩት ቀዳዳዎችና ስንጥቆችም ተደፈኑ። ይህም የነህምያን ጠላቶች በርግጥ አናደዳቸው።

ይህን መጽሐፍ በምታነቡበት ጊዜ ከምታገኙአቸው ጥቅሞች አንዱ በሕይወታችሁ ያሉት "ስንጥቆች" መደፈናቸው ነው! ከቶ እጅ የማትሰጡ ሰዎች መሆንን በምትማሩበት ጊዜ፤ በእናንተ ውስጥ ደካማ የሆኑት ስፍራዎች ይጠነክራሉ። ይህም ጠላትን በጣም፤ በጣም እንዲቆጣ ያደርገዋል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ ባለው ዐላማ ወደፊት እንድትራመዱ ስለማይፈልግ ነው።

አንዳንድ ሰዎች የጠላትን ቁጣ በሚያስቡበት ጊዜ ይፈራሉ፤ ነገር ግን ምንም መፍራት አያስፈልግም። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ነው፤ እርሱም ሁልጊዜ በድል ይመራችኋል (2ቆሮንቶስ 2÷14 ይመ)።

የተቆጣን ጠላት ለማሸነፍ ነህምያ እንዳደረገው እናንተም እግዚአብሔርን ፈልጉ፤ ከቃሉ ጋር ቆዩ፤ እርሱን አምልኩትና ጸልዩ። በራሳችሁ ኀይል ዲያብሎስን ለማሸነፍ መሞከርን አታስቡት! ጸልዩ - እግዚአብሔር እንድታደርጉት እንደነገራችሁ የምታውቁትን ነገር ማድረጋችሁን ቀጥሉ! ጸልዩ - እናም እንዲሁም ዲያብሎስ እንድታደርጉት የማይፈልገውን ነገር ማድረጋችሁን ቀጥሉ።

ነህምያ መጸለዩን ከቶ አላቆመም። ስለ እርሱ ጸሎት ቀደም ሲል ጽፌአለሁ። ነገር ግን በነህምያ 4÷9 እንደገና ሲጸልይ እናየዋለን፤ "እኛ ግን ወደ እግዚአብሔር ጸለይን፤ ዛቻቸውንም ለመቋቋም ቀንና ሌሊት የሚጠብቁ ዘቦችን መደብን" ይላል። በሌላ አነጋገር፤ ያለ ማቋረጥ ጸለዩ ማለት ነው።

ችግር ባጋጠማችሁ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ እንድትጸልዩ እኔ አደፋፍራችኋለሁ። እግዚአብሔር የሚያስፈልጋችሁ በአደጋ ጊዜ ብቻ አይደለም፤ እርሱ ሁልጊዜ ያስፈልጋችኋል። የጸሎትን ሕይወት አዳብሩ፤ ምክንያቱም በራሳችሁና በምትወዱአቸው ዙሪያ የመከላከያ ቅጥር ለመሥራት የምትችሉት በዚህ ስለሆነ ነው። ስለ ጸሎት በይበልጥ ለማወቅ፤ *የቀላል ጸሎት ኀይል* (ዘ ፓወር ኦፍ ሲምፕል ፕሬየር) የተሰኘውን መጽሐፌን እንድታነቡ እጋብዛችኋለሁ።

ተዋጉ፤ አትፍሩ

ነህምያ ጠንካራና ጥበበኛ መሪ መሆኑን አሁን መናገር ትችላላችሁ። እርሱ እግዚአብሔርን መፈለግና በእርሱ ላይ መደገፍ ብቻ ሳይሆን፤ በተጨማሪም ጥሩ ውሳኔዎችን መወሰንና ሕዝቡ በልበ ሙሉነት ፀንተው እንዲቆዩ ማድረግን ያውቅ ነበር። ነህምያ 4÷13-14 እንዲህ ይላል፦

> *ስለዚህ ከቅጥሩ በስተኋላ በሚገኙ ግልጽ ቦታዎች ላይ ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ሰይፋቸውን፤ ጦራቸውንና ቀስታቸውን እንደያዙ በየቤተሰባቸው በመመደብ ቦታቸውን እንዲይዙ አደረግሁ።ʼ ነገሩን በጥሞና*

ከተመለከትሁ በኋላ መኪንንቱን፣ ሹማምቱንና የቀረውን ሕዝብ ‘ሽተፍሩአቸው፤ ታላቁንና የተፈራውን እግዚአብሔርን አስቡ። ስለ ወንድሞቻችሁ፣ ስለ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ፣ ስለ ሚስቶቻችሁና ስለ ቤት ንብረታችሁ ተዋጉ’ አልኋቸው።

እኔም ዛሬ የነህምያን ቃሎች ለእናንተ ለማስተጋባት እፈልጋለሁ፤ ለቤታችሁ ተዋጉ! ለልጆቻችሁ ተዋጉ! ከበደልና ከኩነኔ ነፃ ሆኖ ለመኖር ላላችሁ መብት ተዋጉ! በሕግ ለመታሠር ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ለመኖር ላላችሁ መብት ተዋጉ። ለመደሰት መብታችሁ ተዋጉ! እግዚአብሔር በልባችሁ ውስጥ ላስቀመጣቸው ሕልሞች ተዋጉ! ለእናንተ አስፈላጊ ለሆነው ነገር ተዋጉ! እግዚአብሔር ለእናንተ ካሰበው ከማንኛውም ነገር በታች ረክታችሁ አትቀመጡ። ጠላት ይቃወማችኋል፤ ነገር ግን እርሱን አትፍሩት። ይልቁንስ፣ እግዚአብሔርን አስቡና ከእርሱ ድፍረትን አግኙ።

> እግዚአብሔር ለእናንተ ካሰበው ከማንኛውም ነገር በታች ረክታችሁ አትቀመጡ።

ከዚህ በኋላ ነህምያ የተወሰነ ድልን አገኘ፤ "አድማቸውን እንዳወቀንባቸውና እግዚአብሔርም ዕቅዳቸውን ከንቱ እንዳደረገባቸው ጠላቶቻችን በሰሙ ጊዜ ሁላችን ወደ ቅጥሩ፣ እያንዳንዳችንም ወደ ሥራችን ተመለስን። ከዚያን ቀን ጀምሮ ከሰዎቹ አኩሌቶቹ ሥራውን ሠሩ፤ የቀሩት ደግሞ ጋሻና ጦር፣ ቀስትና ጥሩር ይዘው ነበር። የጦር አለቆች ከመላው የይሁዳ ሕዝብ በስተኋላ ቆሙ" (ቁጥር 15-16)።

በዚህ ሥፍራ የምንማረው ትልቁ ትምህርት አንድ ትንሽ ፋታ ወይም አንድ የእድገት ደረጃ ባገኘን ጊዜ ጥበቃችንን ማላላት የለብንም የሚለው ነው። እኛ ትንሽ ፋታ ብቻ ሳይሆን፣ ሙሉ በሙሉ ነፃ መሆን እንፈልጋለን። ነህምያ፣ "ሁላችሁም አድምጡ! ጠላቶቻችን ሤራቸውን እንዳወቅንባቸው አውቀዋል። እግዚአብሔር ዐላማቸውን እንዳከሸፈው አውቀዋል! እኛ ሁላችንም አሁን መዝናናት እንችላለን!" ለማለት ይችል ነበር። በዚህ ፈንታ ግን፣ ምንም እንኳ ጠላት ትንሽ ወደ ኋላ ያፈገፈገ መሆኑን ቢረዳም፣ ሠራዊቱን በጠላት ላይ አሰልፎ

መጠበቅ እንዳለበት በጥበብ አስተዋለ። እስከ አሁን የነበረው አዝማሚያ እንዲቀጥል አደረገ፤ "እኛ እግዚአብሔር እንድናደርገው የፈለገውን ነገር ለማድረግ ጥረት እያደረግን ነው። ስለዚህ ችላ ማለት የለብንም፤ መላላት አንችልም፤ ምንም እንኳ ጠላታችን በዚህ ወቅት በመንቀሳቀስ ላይ ባይሆንም፤ እኛ እንደ ተዋጊዎች ማሰባችንን አናቋርጥም" አለ።

የጦር መሣሪያችሁን ያዙ

ነህምያ ሥራ እንዲት መሠራት እንዳለበት ያውቅ ነበር። የእርሱ ስልት ምን እንደነበረ በነህምያ 4÷17-18 ላይ እናነባለን፤ "እነርሱም ቅጥሩን ይገነቡ ነበር፣ ዕቃ የሚሸከሙት በአንድ እጃቸው ሥራቸውን ሲሠሩ፣ በሌላው እጃቸው የጦር መሣሪያቸውን ይዘው ነበር። እያንዳንዱም ግንበኛ ቅጥሩን በሚሠራበት ጊዜ ሰይፉን በወገቡ ላይ ታጥቆ ነበር፤ መለከት የሚነፋው ሰው ግን ከእኔ አይለይም ነበር" ይላል።

በአንድ እጃችን ስንሠራ በሌላው እጃችን የጦር መሣሪያ ከምንይዝባቸው መንገዶች አንዱ በምንሠራበት ጊዜ እግዚአብሔርን ማወደስ ነው። የምትሠሩት ነገር ምንም ይሁን ምን፣ ቤታችሁ፣ ትዳራችሁ፣ የንግድ ሥራችሁ፣ የገንዘብ ዋስትናችሁ፣ የሰውነት ልምምድ፣ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር የተቀራረበ ግንኙነት፣ ሊሆን ይችላል - በሥራ ላይ እንዳላችሁ እግዚአብሔርን ማምለክን መተው የለባችሁም። እግዚአብሔርን ማወደስንና ለትንሿ የእድገት ደረጃ እንኳ እርሱን ማመስገንን አትርሱ። የውዳሴ ቃላት ማባዛት አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን "ጌታ ሆይ፤ እወድሃለሁ፤ አመልክሃለሁ፤ ይህንን ያለ አንተ ላደርገው አልችልም። ዛሬ የአንተ እርዳታ ያስፈልገኛል። የምደርስበትን ግብ ስለሰጠኸኝና እርሱንም ለመፈጸም ስለምትረዳኝ አመሰግንሃለሁ" የሚል የምስጋና ልብና ዝንባሌ ይኑራችሁ።

የነህምያ ሠራተኞች በጉናቸው የያዙት ሰይፍ እኛ ሁልጊዜ መያዝ የሚያስፈልገንን የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚወክል አምናለሁ። የእግዚአብሔር ቃል ለእኛ ሰይፍ ነው፤ እኛም ቃሉን በጠላት ላይ

መሳል አለብን። ሰይፍ በሰገባ ውስጥ ቢቀመጥ ምንም ሊጠቅም እንደማይችል ሁሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስም በመደርደሪያው ላይ ተቀምጦ አቧራ ቢጠጣ ሊጠቅመን አይችልም። እኛ ቃሉቹን በጠላት ላይ ካልተጠቀምንባቸው ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም። በሰይፋችን መጠቀም ማለት የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ፣ ማመንና መናገር ነው።

አንድ ቀን ማለዳ ስትነሱ እጅ የመስጠት ስሜት ቢያድርባችሁ፣ እንዲህ በማለት በሰይፋችሁ ተጠቀሙበት፣ "እኔ እጅ አልሰጥም! እግዚአብሔር ለእኔ የወደፊት እቅድና ተስፋ አለው፣ እኔም የታቀደልኝን ለማግኘት መሥራቱን እቀጥላለሁ!" በሉ (ኤርምያስ 29÷11 ይመ)። እግዚአብሔር የጦር መሣሪያ የሚሰጠን እንድንጠቀምበት ነው። ለማሸነፍ ከፈለጋችሁ መንቀሳቀስ አለባችሁ። ዝም ብሎ መቀመጥና መመኘት ጦርነትን አያሸንፍም።

የታሪኩ ቀሪ ክፍል

የነህምያና የቅጥሩ ጉዳይ ከምን ደረጃ እንደ ደረሰ ለማወቅ እንደምትፈልጉ አውቃለሁ። መላውን ታሪክ ከመጽሐፈ ነህምያ ልታነቡ ትችላላችሁ፣ ነገር ግን እኔ ሥራው የተሳካ ነበር ለማለት እችላለሁ። ቅጥሩ ተሠርቶ እስኪያልቅ ድረስ ነህምያና ሕዝቡ ጠላቶቻቸውን ይዋጉ ነበር። ሕዝቡን በአግባቡ ከማያስተዳድሩ የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር የግድ መፋጠጥ ነበረበት፣ ሰንበላጥም ችግር መፍጠሩን ቀጥሎ ነበር፣ እንዲያውም በማስፈራራት እርሱን ለማስቆም አንድ የመጨረሻ ሙከራ አደረገ።

ቅጥሩ ተሠርቶ ባለቀ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ምን ምላሽ የሰጡ ይመስላችኋል? "ጠላቶቻችን ሁሉ ይህን ሲሰሙ በዙሪያችን ያሉ አሕዛብ ሁሉ ፈሩ፣ በራሳቸው መተማመንም አልቻሉም፣ ምክንያቱም ይህ ሥራ የተከናወነው በአምላካችን ርዳታ መሆኑን ተገንዝበዋል" ይላል (ነህምያ 6÷16)።

ቅጥሩ ተሠርቶ ካለቀ በኋላ እንኳ፣ ጠብያ ለነህምያ የማስፈራራያ ደብዳቤ መላኩን ቀጠለ። ጠላት አልሄደም፣ ነገር ግን ነህምያን ሥራውን ከመፈጸም አላገደውም። ነህምያ በጠላቶቹ የውጊያ ማዕበል ውስጥ እንቶ መቆምን፣ ለእርሱ አስፈላጊ በሆነው ነገር መከራከርንና በድል አድራጊነት መውጣትን ተማረ። ይህም እግዚአብሔር ለእናንተ የሚፈልገው ትክክለኛ ነገር ነው።

የፔኒ ሀቀኛነት

ጆምስ ካሽ ፔኒ የተባለ፣ የአንድ የሚዙሪ ምስኪን ቄስ ልጅ፣ ቀላልና ዘመን የለሽ በሆኑት በጨዋነት፣ በሀቀኛነት፣ በአክብሮትና ጠንክሮ በመሥራት እሴቶች ላይ በመመሥረት በአሜሪካ ውስጥ እጅግ ስኬታማ ከሆኑት የችርቻሮ ሽያጭ ንግዶች መካከል አንዱን የመሠረተ ሰው ነው።

የፔኒ አባት ክቅስና ሥራው በተጨማሪ ገበሬ ነበር፣ ፔኒም በሐሚልተን፣ ሚዙሪ አጠገብ ባለው የቤተሰቡ እርሻ ውስጥ መሥራትን ተማረ። አባትዮውም ልጆቹ የገንዘብን ጥቅም እንዲረዱ ለማድረግ ይፈልግ ነበር፣ ስለሆነም አባቱ ፔኒን ክስምንት ዓመት እድሜው ጀምሮ የራሱን ልብሶች እንዲገዛ አደረገው።

በ1893 ፔኒ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ጨረሰና የሕግ ባለሙያ ለመሆን ተስፋ ያደርግ ነበር። በዚህ ፈንታ ግን፣ በአካባቢው በሚገኘው ጄ.ኤም ሃሌ እና ወንድሞቹ በተሰኘው የደረቅ ሽቀጦች መደብር ውስጥ አሻሻጭ ሆነ። ወዲያውም ፔኒ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ክቡር በሆነው እሴት ሊኖር እንደሚችል ተገነዘበ። ሌሎች ፀሐፊዎች ከእርሱ ራቅ ያለ የንግድ ሥራን ጀመሩ፣ እርሱም በይበልጥ ልበ ሙሉ መሆንን፣ የሽያጭ ክህሎቱን ማጠናከርንና እርሱ ባለ መብት ለሆነባቸው የሽያጭ አድሎች በጽናት መቆምን ተማረ።

በዚህ ግላዊና መ.ያዊ እድገት መካከል በነበረበት ጊዜ፣ የፔኒ ጤንነት ማሽቆልቆል ጀመረ። ዶክተሩም የሳምባ ነቀርሳ ይይዘዋል ብሎ ስለፈራ ሚዙሪን ለቅቆ ወደ ሞቃት አካባቢ ሄዶ እንዲቀመጥ ግፊት አደረገበት። ከዚያም ወደ ዴንቨር ኮሎራዶ ሄደና ከሚስተር ሃሌ በተማረው የደረቅ ሽቀጦች የንግድ ሥራ ተቀጠረ።

ወዲያውኑም ብልህና ደፋር የነበረው ፔኒ የራሱን ንግድ ለመጀመር በቂ ገንዘብ አገኘና የሉካንዳ ሱቅ ከፈተ። ይህም በኪሣራ ውስጥ ጣለው፣ ነገር ግን ፔኒ የከሠረው መጥፎ ሠራተኛ ስለሆነ አይደለም፣ የከሠረው በእውነተኛነቱ ምክንያት ነበር። ፔኒ ሁሉንም ደንበኞች በቸርነትና በአክብሮት ማስተናገድን ያምንበት ነበር፣ ስለዚህ ለአንድ ትልቅ

ደንበኛው የተለየ መስተንግዶ ማድረግን እምቢ ባለ ጊዜ፣ ያ ደንበኛ ያለውን የተጽእኖ ኃይል በመጠቀም ፔኒ ሥራውን እንዲለቅ አስገደደው።

የሉካንዳ ሱቁ ከተዘጋ በኋላ፣ ፔኒ የጉልደን ሩል (ወርቃማው ሕግ) የደረቅ ሽቀጦች መደብር ለመሥራት ሄደ። በዚያም ስኬትን አገኘና በመጨረሻ በኩባንያው ውስጥ ሽሪክ ሆነ። ፔኒ በጉልደን ሩል ውስጥ እየሠራ በዋዮሚንግ በሚኖርበት ጊዜ፣ በርታ አልቫ ሄስን ወደዳትና አገባት።

በጨዋነት፣ በሀቀኛነትና በአክብሮት ፍልስፍና ላይ በመመሥረቱ የፔኒ ንግድ እያደገ ሄደ፣ ወዲያውም የራሱን የጉልደን ሩል (ወርቃማው ሕግ) መደብር ከፈተ። ከዚያም ለሠራተኞች ክፍል ቤተሰቦች ጥራት ያላቸውን ሽቀጦች በመጠነኛ ዋጋ በማቅረቡ፣ የላቀ አገልግሎት በመስጠት ዝናን አተረፈ። እርሱም ዳቤ መስጠትን ከለከለና ደንበኞቹ ለሚገዙአቸው ዕቃዎች በጥሬ ገንዘብ እንዲከፍሉ አደረገ።

የጉልደን ሩል ባለቤቶች ይዞታቸውን ለፔኒ ሸጡለትና እርሱም ስሙን ጄ.ሲ.ፔኒ ኩባንያ በማለት ለወጠው። ፔኒ በ1914፣ የኩባንያውን ዋና መሥሪያ ቤት ወደ ኒውዮርክ አዞረና በ1918 የመጀመሪያውን የጄ.ሲ.ፔኒ ይፋዊ መደብር በሚዙሪ ከፈተ።

ፔኒ የችርቻሮ ንግዱን በሚያስፋፋበት ጊዜ ብዙ የግል አደጋዎች አጋጥመውት ነበር። በ1910 ሚስቱ በርታ በሳምባ ምች ስለሞተችበት፣ ሁለት ወንዶች ልጆቹን ብቻውን ማሳደግ ግድ ሆነበት። የእርሷ ሞት፣ ዓለም በራሱ ላይ እንደተደፋበት የሚቆጥረው መሆኑን ጸፈ። በ1919 ፔኒ እንደገና አገባ። ሚስቱ ሜሪ አንድ ወንድ ልጅ ከወለደችለት በኋላ በ1923 ሞተችና ብቻውን ቀረ። በ1926 እንደገና አገባ። እርሱና ሚስቱ ካሮሊን ሁለት ሴቶች ልጆች ወለዱና ፔኒ እስኪሞት ድረስ በትዳር አብረው ኖሩ።

ጄ.ሲ.ፔኒ በመልካምና ጽድቅ ባለበት መርሕ ላይ ተመሥርቶ እያደገ የሚሄድ ንግድን አቋቋመ። በሀቀኛነቱ ላይ ከቶ እጅ አልሰጠም። እናንተም በሕይወታችሁ የምታከናውኑት ነገር ምንም ይሁን ምን፣ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያለውን መርሕ አጥብቃችሁ ያዙ፣ ከዚያም ሁልጊዜ ስኬታማ ትሆናላችሁ።

ምዕራፍ 8

የስኬት ቁልፎች

"የእኛ ታላቅ ድክመት ያለው እጅ በመስጠት ላይ ነው።
ሁልጊዜ ለስኬት እርግጠኛ የሆነው መንገድ
በተጨማሪ አንድ ጊዜ መሞከር ነው።"
ቶማስ ኤዲሰን።

እናንተ በምታደርጉት በማንኛውም መስክ ውስጥ አራት የስኬት ቁልፎች አሉ፡- ታማኝነት፣ ቁርጠኝነት፣ ጌታን መጠበቅና ለመዝናናትና ለመታደስ ጊዜ መውሰድ ናቸው። እነዚህ ባሕርያትና ልምዶች የተለመዱ የሕይወታችሁ አካል በሚሆኑበት ጊዜ፣ እጅ እንዳትሰጡ ያደርጉአችሁና ወደምትናፍቁት ስኬት ያደርሱአችኋል።

ታማኝነት

"ከቶ እጅ ያለመስጠትን" አሳብ በአንድ ቃል ለማጠቃለል ከፈለጋችሁ፣ ታማኝነት የሚለውን ቃል መጠቀም ትችላላችሁ። ታማኝነት ከሌለ፣ ሰዎች በቀላሉ እጅ ይሰጣሉ፣ ከቶ የጽናት ኀይል አይኖራቸውም። እናንተም ከቶ እጅ የማትሰጡ ሰዎች ለመሆን ከፈለጋችሁ፣ ቁልፉ ታማኝነት ነው።

ሥር ነቀል ታማኝነት።

ንስር እድሜው አንድ ዓመት ሲሆን፣ ጥቂት ነፃነትን ማዳበር ይጀምራል። በዚህ ወቅት ዐይናቹ ብሩህ፣ ጥፍሮቹም ስለታም ይሆናሉ። የራሱን ምግብ ለማግኘት፣ ለመብረርና በጥቂቱም ወደ

ሰማይ ለመውጣት የሚችል ይሆናል። ለሦስት ዓመት ያህል አዳኒ ንስር ሆኖ ይኖራል፤ ከዚያም እያደገና ጥንካሬን እያገኘ፣ ችሎታዎቹንም እያሻሻለ ይሄድና በንስር ሕይወት የተመሠረተ መሆን ይጀምራል።

ንስሩ አራት ዓመት ሲሆነው አውቆ የሚያደርገው ሳይሆን በደመ ነፍሱ - መለወጥ ይጀምራል። በውስጡ ምኞት የማይሰማው፣ እንግዳና አረፍት የለሽ ይሆናል። ምናልባት ንስሩ ምን እየሆነበት እንዳለ ላይገባው ይችላል። በመጨረሻው፣ በዚህ እንግዳ በሆነበት የእድገት ወቅት ለራሱ ደስታ ብቻ ለመኖር እንዳልተፈጠረ መገንዘብ ይጀምራል። ሕይወቱ ከራሱ በላይ የሚተርፍ እንዲሆንለት ይፈልጋል።

በዚህ ወቅት፣ ወንዱ ንስር ሴት ንስር ለማግኘት ይሄዳል። አንዲቱን ባገኘ ጊዜ፣ ሁለቱ የመጓተት ጨዋታ ይጫወታሉ፤ ይህም እንደ መዳራት ያለ ነገር ነው። የእርሱ መወራጨት ለፍቅር ካለው ናፍቆት የተነሣ ነው! አሁን እርሱ የሚያድግበት ጊዜ ነው። ሴቷ ንስር በስምንት ቁጥር መልክ ወደ ሰማይ ትመጥቅና ወንዱ ንስር እንዲያባርራት ታደርገዋለች። አሁን እርሱ የራሱን አቅጣጫ ተከትሎ አይበርም፤ ሌላውን እየተከተለ ነው፤ እርሱም ባልተለመደ አቅጣጫ የሚሄድ ነው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ መሬት ትወርዳለች፤ ከዚያም አንድ የዛፍ ቀምበጥ ታነሣና ወደ ሰማይ ዐሥር ሺህ ጫማ ከወጣች በኋላ ቀምበጡን ትጥለዋለች። እርሱም በግምት በሰዓት ሁለት መቶ ማይል እየበረረ ወደ ታች ይወርድና ቀምበጡን በአየር ላይ ከቀለበው በኋላ ወደ እርሷ መልሶ ይወስደዋል። የእርሷ ምላሽ ምንድን ነው? ችላ ትለዋለች።

በዚህ ወቅት፣ ንስሩ ምንም እንኳ ይህን እንደ ስድብ ቢቆጥረውም ውሳኔ ማድረግ ይኖርበታል፤ "እኔ በርግጥ ይህንን በትእግስት ችዬ ፍጻሜውን ማየት ይኖርብኛልን? ይህ በርግጥ እኔ የምፈልገው ነገር ነውን? ወይስ ይህንን ትቼ ከዚህ ቀለል ባለ ጉዳይ ላይ ጊዜዬን ባሳልፍ ይሻላል? ይላል።

ሴቷ ንስር ይህንን ሂደት በመደጋገም፣ የወንዱን ንስር ሥራ ታክብድበታለች። በበረረች ቁጥር ቀምበጡን ትልቅ ታደርግና ወደ ታች ዝቅ ብላ ትበርራለች። ይህም ቀንበጡ በፍጥነት በምድር ላይ ስለሚያርፍ ወንዱ ንስር እርሷን ለመማረክ ከፈለገ ጠንክሮ መሥራት ይኖርበታል።

ይህ ጨዋታ ለቀናት የሚቀጥል ነው። በመጨረሻ ሴቷ ንስር ከወንዱ ንስር ክብደት የበለጠ የዛፍ ቅርንጫፍ ትወስዳለች። ወንዱ ንስር፣ "ይህ ትክክል አይደለም! እግዚአብሔር ሆይ ይህን ለማድረግ እንደማልችል ታውቃለህ! ምነው እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህ ለእኔ ከባድ እንደሆነ ታውቃለህ!" እንደሚል እገምታለሁ። በዚህ ጊዜ ሴቷ ንስር ከመሬት በላይ ዐምስት መቶ ጫማ ብቻ ትበርና ቅርንጫፉን ትጥለዋለች። እርሱ ከያዘው አብረው ይሄዳሉ። ይህ ካልሆነ እርሷ ትታው ትበርራለች፣ የእርሷ ባል ለመሆን በቂ ጥንካሬ ያለው ሌላ ወንድ ንስር ለማግኘት ወስናለች ማለት ነው።

ለወንዱ ንስር ይህን ሂደት በቀጣይነት ለመከተል፣ ፍጹም ታማኝ መሆን ይጠበቅበታል። እርሱ ይህን የመጨረሻውን የቀምበጥ ፈተና ካለፈ፣ ሁለቱም ንስሮች ከመዳራት ደረጃ ወደ መጨረሻው የታማኝነት ፈተና ይሸጋገራሉ። ሴቷ ንስር ከፍ ብላ ወደ ሰማይ ትበርራለች፣ እርሱም ያባርራታል፣ እርሷም በድንገት ያልተለመደ ድርጊት ታሳያለች። በአየር ላይ ተገልብጣ በጀርባዋ ትተኛና ጥፍሮቿን ወደ ላይ ትዘረጋለች። ወንዱም ወደ እርሷ ይሄድና የራሱን ጥፍሮች ከእርሷ ጥፍሮች ጋር ካቆላለፈ በኋላ ሁለቱም ወደ መሬት ይወድቃሉ። በዚህ ጊዜ እርሱ ውሳኔ አድርጓል። እርሱ በታማኝነት ስለጸና፣ እርሷን ከመተው ሞትን ይመርጣል። አሁን ሁለቱም የፍቅር መዝሙር መዘመር ይጀምራሉ። ለመላው የሕይወት ዘመናቸው ይገናኛሉ። አንዱ ካልሞተ በስተቀር ማንኛቸውም ሌላ ጓደኛ አይኖራቸውም። ሴቷ ከሞተች ወንዱ ልጆቹን ያሳድጋል።

የግንኙነታቸው ወቅት ካለቀና በጎጆአቸው ውስጥ እርሱ የእርሷ፣ እርሷም የእርሱ መሆናቸውን ከተዋወቁ በኋላ እንኳ፣ ለቀሪው የሕይወት ዘመናቸው በሙሉ ወንዱ ንስር ከሴቷ ንስር ጋር መዳራቱን

ይቀጥላል። የመዳራቱ ጊዜ ካለፈ ከረጅም ጊዜ በኋላም፣ ወንዶች ንስሮች የሴት ጓደኞቸውን ላባ ሲያሻሹና የዛፍ ቀምበጥ ወደ ጉጂቸው ሲያመጡላቸው ታይተዋል። ይህንን የምታነቢው ሴት ከሆንሽ፣ በምድር ላይ ያሉ ወንዶች በሙሉ ከንስሩ ጥቂት ነገሮችን ቢማሩ ብለሽ ሳትመኚ አትቀሪም ይሆናል!

በሕይወት ዘመን ሂደት ውስጥ ጽኑና ጠንካራ ሆኖ የሚቆየው የታማኝነት ዐይነት ይህ ነው፤ እናንተም በሕይወታችሁ ውስጥ የምታዳብሩት ታማኝነት ይህ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን በፍጹምነት ላታገኙት ትችላላችሁ፣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ከተራመዳችሁና በሕይወታችሁ ከተባረካችሁ፣ ይህ ዐይነቱ ሥር ነቀል ታማኝነት ያስፈልጋችኋል፤ ይህም ታማኝነት በአስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ፣ ብቸኝነት ወይም መገፋት በሚሰማችሁ ጊዜ፣ ወይም ሁኔታዎች መጥፎ በሚሆኑበት ጊዜ ተከትሎአችሁ የሚሄድ ነው። ኀይለኛው የወንድ ንስር ምንም እንኳ ታማኝነቱ የሕይወት ዋጋ የሚያስከፍለው ቢሆንም፣ በታማኝነት ጸንቶ መቆየቱን አስቡ። ደግሞም ከልባችሁ፣ "በዚህ ሁኔታ ውስጥ ታማኝነቱን ምንም ነገር ሊያነቃንቀው አይችልም። እስከ ፍጻሜው ድረስ ጸንቼ እይዘዋለሁ። *ምንም ቢሆን እጅ አልሰጥም* ማለትን ተማሩ።

እግዚአብሔር፣ ንስር፣ እና እናንተ

የአራት ዓመት እድሜ ያለው ንስር ምኞት እንደማይሰማው ሁሉ፣ እኛም ብዙ ጊዜ በተመሳሳይ ምክንያት ምኞት የማይሰማን ጊዜ ይኖራል፦ ይህ ለእኛም የማደግ ጊዜ ነው። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር እኛን ወደ ዐዲስ ደረጃ ሊወስደን ሲፈልግ የብዥታ መልክ ካለው እርካታ ቢስነትና እረፍት የለሽነት ስሜት ጋር የመታገል ሁኔታ ይገጥመናል። በዚህ ጊዜ እኛ የምንለጠው ምላሽ አሳባችንን ግልጽ ማድረግና ስሜቶቻችንን ፀጥ ማድረግ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም ምንም ዐይነት ከባድ ችግር ስለሌለ ነው። በጥንካሬ የማደግና ይበልጥ በሳል የመሆን ጊዜ ስለ ደረሰ ብቻ ነው፤ እኛም ለዚህ ሂደት ታማኝ መሆን ያስፈልገናል።

ታማኝነት ቀላል ነው? አይደለም፤ ነገር ግን ታማኝነት የሚጠይቀውን ሁሉ ሊያገኝ የሚገባው ነገር ነው። በሕይወቱ ብዙ ጦርነቶችን ተዋግቼአለሁ፤ ነገር ግን አሁን ደስተኛ፣ ሙሉና እርካታ ያለኝ ነኝ። አይደለም፤ እርሱ ቀላል አልነበረም፤ አሞ፤ ብዙ፣ ብዙ ጊዜ እጅ ለመስጠት ፈልጌ ነበር። ነገር ግን ለእግዚአብሔርና እርሱ ለጠራኝ አገልግሎት ታማኝ ሆኛለሁ። ይህም እኔ እጅ ለመስጠት ከቶ አልተፈተንሁም ማለት አይደለም፤ ነገር ግን የታማኝነቴ ጎይል ፈተናውን ለመከላከል ያስችለኛል ማለቴ ነው። እግዚአብሔር እናንተን ወደ ዐዲስ የታማኝነት ደረጃ ሊወስዳችሁ ይፈልጋል። እናንተንም እንደ ንስሩ እርሱ በሕይወታችሁ ላለው ዐላማ ከፍተኛ ታማኝነት እንዲኖራችሁና ራሳችሁን ለእርሱ አሳልፋችሁ እንድትሰጡ ይፈልጋል። ከእርሱ ጋርና ከሕይወትም ጋር የታማኝነት ግንኙነት እንዲኖራችሁ ይፈልጋል። በበኩሌ ከዚህ የበለጠ የሚያረካ፣ የበለጠ ብድራት ያለውና የበለጠ የጀብዱ ተግባር አለ ብዬ አልገምትም። እርሱ ለእናንተ እናንተ ከጠየቃችሁት ወይም ከገመታችሁት በላይ የሆነ ነገር አለው፤ ነገር ግን የእርሱ እቅድ በሕይወታችሁ እውን ሲሆን ለማየት ከፈለጋችሁ፣ በጣም ታማኝ መሆን ያስፈልጋችኋል።

> ታማኝነት ቀላል ነውን አይደለም፤ ነገር ግን እርሱ የሚጠይቀውን ሁሉ ሊያገኝ የሚገባው ነገር ነው።

ቁርጠኝነት

እኛ ክርስቶስን እንደ አዳኛችን ስንቀበል የእግዚአብሔርን መንፈስ እንቀበላለን፤ ዐዲስ "ፍላጐት" እንቀበላለን፤ ይህም ግቦችን ለመፈጸምና የማይቻሉ የሚመስሉ ሕልሞችን ለመከተል የሚያስችለን ቁርጠኝነት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ይህ ፍላጐታችሁ በምድር ላይ ካሉት እጅግ ጠንካራ ጎይሎች አንዱ ነው። ፍላጐት ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ከተመለሰ፣ በሕይወት አስገራሚ ነገሮችን ለመፈጸም ትችላላችሁ። ለማንኛውም ነገር ምንም ዐይነት ሰበብ ማቅረብ እንደማይገባኝ በራሴ ሕይወት አይቼዋለሁ፤ ምክንያቱም ሐቁ፣ እኔ አንድ ነገር ለማድረግ በርግጥ ከፈለግሁ ስለማደርገው ነው!

በዲትሮይት መሐል ከተማ የተወለደው ዝነኛው የሕፃናት የነርቭ ቀዶ ጥገና ሐኪም ቤን ካርሰን መጥፎ ጅማሬ ነበረው። እናቱ ትምህርቷን ከሦስተኛ ክፍል ያቋረጠችና ገና በዐሥራ ሦስት ዓመት እድሜዋ ያገባች ሴት ናት። ቤን ገና ስምንት ዓመት ሲሆነው ወላጆቹ ተፋቱ፤ ከዚህም የተነሣ እናቱ የእርሱንና የወንድሙን የክርቲስን መሠረታዊ ፍላጐት ለማሟላት፣ በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ሦስት ሥራዎችን ትሠራ ነበር። የእርሱ "እጅ ያለ መስጠት" ታሪክ ለእርሱ ቁርጠኝነትና ጽናት ምስክር እንደሆነ ሁሉ ለእርሷም እንዲሁ ነው።

ቤንም ሆነ ወንድሙ ክርቲስ በትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት አልነበራቸውም። ቤን የዐምስተኛ ክፍል ተማሪ በነበረ ጊዜ፣ በክፍል ውስጥ የሚያገኘው ውጤት እጅግ አነስተኛ ስለነበረ ሌሎቹ ተማሪዎች "የአንጀራ እናት ጡጦ" የሚል ስያሜ ሰጥተውት ነበር። በዚህ ጊዜ፣ እርሱ ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ቁጣና ግልፍተኝነት ያሳይ ነበር።

የቤን ችግሮች እናቱን በጣም ያስጨንቃት ነበር። አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባት ይሰማት ነበር። በመጀመሪያ፣ መጸለይ ጀመረች፤ ከዚያም ቤንና ክርቲስ ማወቅ ያለባቸውን ትምህርት እንዲያውቁና በትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት እንዲኖራቸው ለመርዳት የሚያስችላትን ጥበብ ለማግኘት አምርራ ትጸልይ ነበር። ከዚያም በቤት ውስጥ ጥብቅ የሆነ ሥነ-ሥርዐት እንዲጠበቅ አደረገች፤ ልጆቹ ቴሌቪዥን የሚያዩበትን ጊዜ ወሰነች፤ በየቀኑ የቤት ሥራቸውን ሳይሠሩ ወደ ጨዋታ እንዳይሄዱ ከለከለች፤ እንዲሁም በሳምንት ሁለት መጻሕፍትን አንብበው ሪፖርት እንዲያቀርቡ አዘዘች። ቤን ለትምህርት ቤት ሥራው ከሰጠው ከፍተኛ ትኩረትና በከፍተኛ ደረጃ ካዳበረው የማንበብ ልምዱ የተነሣ የውጤት ደረጃውን በጣም ማሻሻሉ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ደግሞ እርሱ እንደ ሌሎቹ መማር የሚችል እንጂ "ዱዳ" እንዳልሆነ ተገነዘበ።

ቤን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንደጨረሰ፣ ጐልቶ የሚታይ ተማሪ ሆነ። እርሱም በክብር ተመረቀና ወደ ዬል ዩኒቨርሲቲ ገባ፤ በዚያም በሥነ ልቡና (ሳይኮሎጂ) ዲግሪውን አገኘና የሥነ አእምሮ ባለሙያ (ሳይኪያትሪስት) ለመሆን ትምህርቱን ለመቀጠል ዐሰበ። ቤን

በሚሺጋን ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ትምህርት ቤት ከገባ በኋላ፣ የሥነ አእምሮ ትምህርትን ትቶ የነርቭ ቀዶ ጥገና ትምህርትን ለመከታተል ወሰነ። ቤን የነርቭ ቀዶ ጥገና የሕክምና ቆይታውን በዓለም ከታወቁት ሆስፒታሎች አንዱ በሆነው በባልቲሞር ሜሪላንድ በሚገኘው በጆንስ ሆፕኪንስ ሆስፒታል ፈጸመ፤ ከዚያም በቀደምት ሠላሳዎቹ ዓመታት እድሜ ላለ የዚያ ሆስፒታል የሕፃናት የነርቭ ቀዶ ጥገና ክፍል ዲሬክተር ሆነ - በጆንስ ሆፕኪንስ ሆስፒታል እንዲህ ያለውን ቦታ ለመያዝ የመጀመሪያው ወጣት ሰው ሆነ። ይህን ጽሑፍ በተመለከተ፣ እርሱ አሁንም በዚህ ቦታ ይገኛል፣ በጆንስ ሆፕኪንስ የሕክምና ትምህርት ቤት የነርቭ ቀዶ ጥገና፣ የእብጠት፣ የፐላስቲክ ቀዶ ጥገናና የሕፃናት ሕክምና ፕሮፌሰር በመሆን ያገለግላል፤ በተጨማሪም ወጣቶች የአእምሮ እምቅ ኀይላቸውን እንዲያሳድጉ በመናገርና በማደፋፈር ሥራ ተይዞ ይገኛል።

እናንተም የማይቻል ወደሚመስል ግብ ለመድረስ ሕልም ካላችሁ፣ በክፍል ውስጥ እጅግ ዝቅተኛ ውጤት ያገኘ የነበረውንና ዛሬ በዓለም ውስጥ እጅግ ብሩህ ከሆኑት የሕክምና ባለሙያዎች አንዱ የሆነውን ቤን ካርሰንን አስታውሱ። ይህም ሊሆን የቻለው እናቱ በእርሱ እጅ መስጠትን እምቢ ስላለችና እርሱም በራሱ እጅ ስላልሰጠ ነው።

እናንተም በትምህርት ቤት፣ ወይም በማንኛውም የሕይወቱ ክፍል የሚታገል ልጅ ወላጆች ከሆናችሁ፣ የቤን ካርሰን ታሪክ ሊያነቃቃችሁ ይገባል። እናቱ በእርሱ ሕይወት ላይ ያመጣችውን ልዩነት አስታውሱና እንደ እርሷ አድርጉ፤ ጸልዩና ልጆቻችሁ ስኬታማ እንዲሆኑ ለመርዳት እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት። ከዚያም እነርሱ የሚያስፈልጋቸውን ሥነ-ሥርዐት እንዲጠብቁ እየረዳችኋቸው እጅ እንዳይሰጡ አድርጓቸው!

ምርኩኛ አድርጉ ከያዛችሁ እሥራት በርግጥ ለመውጣት ከፈለጋችሁ፣ ትወጣላችሁ! ካለፈው ሁኔታችሁ ነፃ ወጥታችሁ ወደፊት ለመራመድ በርግጥ ከፈለጋችሁ፣ ትችላላችሁ። በአሉታዊ አስተሳሰብ ፈንታ አዎንታዊ አስተሳሰብን ለማዳበር በርግጥ ከፈለጋችሁ፣

ትችላላችሁ። ሌላ ማንም አይመጣም በሚል ፍርሃት "የሁለተኛነት ደረጃ" ያለውን ሰው ከማግባት ይልቅ ለመቆየትና ትክክለኛውን ሰው ለማግባት በርግጥ ከፈለጋችሁ፣ ትችላላችሁ!

እናንተ በቂ ቁርጠኝነት ካላችሁ፣ - ምንም ዐይነት የገሃነም ክፉ ኀይል፣ በምድር ላይ ያለ ምንም ዐይነት ሰው ቢሆን - ስኬታማ ከመሆን ማንም ሊያግዳችሁ አይችልም። ለእግዚአብሔር ከታዘዛችሁና እርሱ እንድታደርጉት ያዘዛችሁን ነገር ለማድረግ ከፈለጋችሁ፣ እንዲሁም ዲያብሎስ ሊቃወማችሁ በመጣ ጊዜ ሁሉ፣ እርሱን ለመቅደም ከቀረጣችሁ፣ ወደ ግባችሁ እንዳትደርሱ ማንም ሊያግዳችሁ አይችልም።

ቁርጠኞች ሁኑ

የቁርጠኝነት አንዱ ትርጉም፣ "ሥልጣን ባለው ውሳኔ ወይም መግለጫ ክርክርን ማስቆም" የሚል ነው። ይህ ትርጉም እኔን ያበረታታኛል፤ ምክንያቱም እኔ በአንዳንድ ነገሮች ላይ ቁርጠኝነቴን ለመገንባት ብዙ ጊዜ "መግለጫዎች" ስለምሰጥ ነው። አንዳንድ ጊዜ፣ በቂ ምግብ እንደበላሁ ስረዳ፣ ነገር ግን ሥጋዬ ከዚያ ይበልጥ ለመብላት ሲፈልግ፣ በጠረጴዛው አጠገብ እንደ ተቀመጥሁ፣ "ይህ የመጨረሻው ጉርሻዬ ነው! ይህን ማዕድ ጨርሻለሁ!" በማለት መግለጫ እሰጣለሁ።

እናንተም በአንድ ነገር ላይ ቁርጠኞች ከሆናችሁ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ለራሳችሁ መናገር ትችላላችሁ። አንዳንድ ጊዜ በአንድ ነገር ላይ እጅ የመስጠትን ፈተና ለማሸነፍ ከሁሉ የተሻለው መንገድ ለራሳችሁ "አይ አይሆንም፤ አይቻልም! መነጫነጭህን ተውና በቅጽበት ፀጥ በል!" ማለት ነው። እኔ በዓመታት ውስጥ፣ እጅ የመስጠት ስሜት በተሰማኝ ጊዜና ማንም የሚያበረታታኝ በሌለ ጊዜ ለራሴ "ጆይስ፣ ልትፈጽሚው

አንዳንድ ጊዜ፣ በአንድ ነገር ላይ እጅ የመስጠትን ፈተና ለማሸነፍ ከሁሉ የተሻለው መንገድ ለራሳችሁ "አይ፣ አይሆንም፣ አይቻልም! መነጫነጭህን ተውና በቅጽበት ፀጥ በል!" ማለት ነው።

ትችያለሽ! ከባድ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ልትፈጽሚው ስለምትችዪ አልችልም ብለሽ አታስቢ!" እላለሁ።-

በሕይወቴ ውስጥ በአንድ ወቅት፣ ለ*ዐሥር ዓመታት* በተለያዩ አካላዊ ችግሮች ተሰቃይቼ ነበር። *ለዐሥር ዓመታት!* ብዙ የሕመም ምልክቶች ነበሩብኝ፤ አንዳንዶቹ በደሜ ውስጥ የስኳር ማነስ ሲሆኑ፣ አብዛኞቹ ከከባድ ሥራ የተነሣ በሚመጣ የአእምሮ ጫና ምክንያት ሥር የሰደዱ ነበሩ። ደግሞም ለእኔ ቀላል ባልሆነው "የሕይወት ለውጥ" ውስጥ እያለፍሁ ነበር። በአካሌ ውስጥ ያለው የኬሚካል ማዕድን (ሆርሞን) ለውጥ ከፍተኛ የራስ ምታትን አስከተለብኝ፤ እንዲያውም በ1989 አንድ ጊዜ፣ ከዚህ በፊት እንደጠቀስሁት፣ የጡት ካንሰር ስለያዘኝ ቀዶ ጥገና ያስፈልገኝ ነበር።

በእነዚያ ዐሥር ዓመታት ወቅት ለስብከት በመድረክ ላይ በወጣሁ ጊዜ ሁሉ፣ *መልእክቱን አስክጨርስ ድረስ በዚህ ለመቆም የምችል መሆኔን አላውቅም* ያልሁበትን ጊዜ ቆጥሬ አልጨርሰውም። እግዚአብሔር እንዲፈውሰኝ አምርሬ እጸልይ ነበር። እርሱ ችግሮቼን ሙሉ በሙሉ አላስወገደልኝም፤ ነገር ግን ሕመሞች እያሉ ማድረግ የሚያስፈልገኝን ነገር እንዳደርግ ሁልጊዜ ጥንካሬን ይሰጠኝ ነበር። እኔ የምፈልገው ግን ወደፊት ለመጓዝ ጥንካሬን እንዲሰጠኝ አልነበረም፤ እኔ የምፈልገው ችግሮቹ እንዲወገዱ ነበር! በእነዚያ ዓመታት ውስጥ ጉዞን ለመቀጠል መሞከር ከባድ፣ በርግጥ ከባድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ እጅ ላለመስጠትና ላለመሸነፍ ቆርጬ ነበር። በእነዚያ ዓመታት ውስጥ እምነቱ እንደጠነከረና ለታመሙ ሰዎችም እውነተኛ ርህራሄን እንዳገኘሁ አሁን ተገንዝቤአለሁ።

ከዐሥር ዓመታት በኋላ ለችግሮቹ መፍትሔን ስለሰጠኝ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። እኔ ቶሎ እንዲሆን ፈልጌ ነበር፤ ነገር ግን የእኛ ጊዜዎች በእርሱ እጅ ናቸው። አሁን እኔ ደህና ነኝ፤ ደግሞም የማደርገውን ነገር ማድረጌና መልካም ስሜትን ማግኘቴ አስደናቂ ነገር ነው! ነገር ግን ብዙ ጊዜ "*ሥራዬን መሥራትና* መልካም ስሜትን ማግኘት ይበልጥብኛል፤ ነገር ግን ስማ ዲያብሎስ፤ መልካም ስሜት ቢኖረኝም ባይኖረኝም አደርገዋለሁ" ማለት ነበረብኝ።

በምሰቃይበት ጊዜ፣ የቁርጠኝነትን ቃላት ጮክ ብዬ የግድ መናገር ነበረብኝ፤ "ይህን በማደርግበት ጊዜ ጥሩ ስሜት ቢኖረኝ እወዳለሁ። በዚህ ሁኔታ እርሱን ማድረግ ከባድ ነው፤ ነገር ግን የሚሰማኝ ስሜት ምንም ይሁን፣ እግዚአብሔር ለሕይወቴ ያለውን ጥሪ እፈጽማለሁ። እግዚአብሔር እኔ እንዳደርገው የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር አደርጋለሁ፤ እኔ እንድሆን የሚፈልገውንም ነገር ሁሉ እሆናለሁ!" እላለሁ። ከዕለታት አንድ ቀን ጠዋት መጥፎ ስሜት የተሰማኝን ጊዜ አስታውሳለሁ። ምንም ጎይል አልነበረኝም፤ ነገር ግን ጸለይሁና ለጌታ "ብዙ ጎይል ላይኖረኝ ይችላል፤ ነገር ግን ያለኝን ያህል በቀሪው የሕይወት ዘመኔ አንተን ለማገልገል እጠቀምበታለሁ" አልሁት። እንዲህ ያለ ውሳኔ በምወስንበት ጊዜ ሁሉ፣ ዲያብሎስ እየተሸነፈ እግዚአብሔር ደግሞ እያሸነፈ ነበር።

ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመታዘዝ ቁርጠኛ የሆንኩበት ዋናው ምክንያት - በሰውነቴ መልካም ስሜት ቢኖረኝም ሆነ ባይኖረኝ እግዚአብሔርን ስለምወድ ነበር። ደግሞም እግዚአብሔር እንዳደርገው ከጠራኝ ባነሰ ሁኔታ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ብሞክር ብስጩ እሆን ነበር። ምናልባት እናንተ ቁርጠኞች ለመሆን ሁልጊዜ ጥረት ለማድረግ ላትፈልጉ ትችላላችሁ፤ ነገር ግን ይህን ለመታዘዝ ፈቃደኞች ባለመሆናችሁ ብቻ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ለመሆን እንደማትፈልጉ እርግጠኛ ነኝ።

ክርክሩን አስቁሙ

ልብ አድርጉ፤ *የመቀረጥ (የመወሰን)* ትርጉም ክርክርን የማስቆምን አሳብ የሚያካትት ነው። ይህ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ለአንድ ነገር ታማኝ ለመሆን ከተነሣችሁ በሥጋችሁና በመንፈሳችሁ መካከል ያለውን የማያቋርጥ ክርክር ማስቆም ስለሚኖርባችሁ ነው። እኔ ብዙ ጊዜ *ሥጋ* "ቁማርተኛ" ነው፤ *መንፈስ* ግን "አስቀማጭ" ነው አላለሁ። *መንፈስ* ቅዱስንና የእርሱን አመራር በልባችሁ (በመንፈሳችሁ) ውስጥ በምትከተሉበት ጊዜ፣ ዛሬ ትክክለኛ ምርጫ በማድረግ ለነገ ታስቀምጣላችሁ።

ገላትያ 5÷17፣ "ሥጋ መንፈስ (ቅዱስ) የማይፈልገውን፣ መንፈስም ሥጋ (መልክም ያልሆነ ተፈጥሮ) የማይፈልገውን ይመኛልና፤ እነዚህ እርስ በርሳቸው ስለሚጋጩ ..." ይላል። ይህ ጥቅስ በመሠረቱ፣ በእኛ ውስጥ ሁልጊዜ ጦርነት የሚካሄድ መሆኑን ይነግረናል። ሥጋና መንፈስ ምን ጊዜም አይስማሙም፤ ሁልጊዜ እርስ በርሳቸው ይዋጋሉ።

ይህ በሁላችንም ዘንድ አለ። እኛ ስለ አንድ ነገር ምኞት፣ ግፊት፣ ወይም ስሜት ይኖረናል፤ በልባችንም ውስጥ ይህ ትክክል መሆኑ ይታወቀናል። ነገር ግን አእምሮአችን ይህን በተግባር ላይ እንዳናውል ይከራከረናል። ለምሳሌ እናንተ ለአንድ ችግረኛ ቤተሰብ ገንዘብ ለመስጠት ስሜት ይኖራችኋል እንበል። ልባችሁም ይህን ማድረግ ትክክል እንደሆነ ያምናል፤ እናንተም ይህ ተግባር እግዚአብሔርን እንደሚያስደስተውና እንዲያውም በመንፈስ ቅዱስ የተነሳሳ መሆኑን ታምኑበታላችሁ። ሥጋችሁ ግን፣ "ይህን ገንዘብ መስጠት የለባችሁም። ገንዘቡ እንደሚያስፈልጋችሁ ታውቃላችሁ" ይላል፤ ወይም "ለእነዚያ ሰዎች ምንም ነገር አትስጡ፤ ለእናንተ ምንም ነገር አላደረጉላችሁም" ይላል። ሥጋ በመንፈስ ላይ ይነሣል፤ እናንተም የትኛውን ማዳመጥ እንዳለባችሁ ለማወቅ ትሞክራላችሁ።

ብዙ በረከቶችን የምናጣው መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን በመፍቀድ ፈንታ፣ ሁሉን ነገር ለመረዳት ስለምንሞክር መሆኑን አምንበታለሁ። በሥጋና በመንፈስ መካከል ያለውን ክርክር ማስቆምና ምንም ነገር ቢሆን ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ መቁረጥ አለብን።

ጌታን ስለ መጠበቅ

እግዚአብሔር ሕዝቡን ከንስር ጋር ያወዳድራቸዋል፤ "እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን ኀይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፣ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፣ አይደክሙም" ይላል (ኢሳይያስ 40÷31)። እግዚአብሔር እኛን ከንስር ጋር ያመሳሰለን በሕይወታችን ወዳለው እምቅ ኀይል እንድንደርስ ሊያነቃቃንና እርሱን እንድንጠብቅ፣ እንዲሁም ኀይላችንን ከእርሱ

እንድናገኝ ሊያደፋፍረን ነው። ስኬት በቀላሉ በማይገኝበት ጊዜ፣ የጥረታችን ውጤት በሙሉ ብስጭትና ድካም ብቻ በሚሆንበት ጊዜ፣ ጌታን መጠበቅ ያስፈልገናል።

ለመሆኑ ጌታን መጠበቅ ማለት ምን ማለት ነው? በቀላሉ፣ ከእርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፍ፣ በእርሱ ሀልመት ውስጥ መሆን፣ ቃሉን ማሰላሰል፣ እርሱን ማምለክ፣ እርሱን የሕይወታችን ማዕከል ማድረግ ማለት ነው። መጠበቅ የሚለው ቃል አንዱ ትርጉም፣ "በአንድነት መገመድ ወይም መጐንጐን" ማለት ነው። የአንድን ሰው ፀጉር ጉንጉን በምንመለከትበት ጊዜ አንዱ ክፋይ (ጥቅል) የት እንደሚጨርስና ሌላ ክፋይ (ጥቅል) የት እንደሚጀምር ለማወቅ አስከማንችል ድረስ ፀጉሩ በአንድነት የተሸመነ (የተሠራ) መሆኑን እንገነዘባለን። እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ያለን ሕብረት ይህን እንዲመስል ይፈልጋል፤ ይህም ከእርሱ ጋር በቅርበት የተጠላለፈና በጥብቅ የተሸመነ ከመሆኑ የተነሣ ከእርሱ ጋር አንድ እንሆናለን፤ የእርሱ ባሕርይ ቀጥተኛ ወኪሎች እንሆናለን ማለት ነው። እርሱን በምንጠብቅበት ጊዜ፣ እያደር በይበልጥ እርሱን እየመሰልን እንሄዳለን። መጠበቅ ማለት ዝምታ (አለመሥራት) ማለት አይደለም፤ በመንፈሳዊ ረገድ ተንቀሳቃሽ ማለት ነው። እኛ በምንጠብቅበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር በእኛና በሕይወታችን ታላቅ ነገሮችን እንደሚያደርግ በንቃት መጠባበቅ ያስፈልገናል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለ የተቀራረበ ግንኙነት በውስጠኛው የሰውነታችሁ ክፍል እንድትጠነክሩ ያደርጋችኋል። እርሱ ልባችሁን ያጠነክራል፤ እርሱ ምንም ነገር ቢሆን በሕይወታችሁ በአስቸጋሪ ወቅት በሰላምና በልበ ሙሉነት ያሸጋግራችኋል። በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎች በእናንተ ሕይወት አንዳች ጫና መኖሩን ለማወቅ እስከማይችሉ ድረስ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመታገስ ጥንካሬን ይሰጣችኋል። በምገልጽላችሁ መንገድ እግዚአብሔርን የምትጠባበቁ ከሆነ፣ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ከእርሱ ታገኛላችሁ። እርሱ የእናንተ ምሽግ፣ የእናንተ ኀይል፣ የእናንተ ደስታ፣ የእናንተ ሰላም፣ የእናንተ

> መጠበቅ ማለት ዝምታ (አለመሥራት) ማለት አይደለም፤ በመንፈሳዊ ረገድ ተንቀሳቃሽ ማለት ነው።

ጽድቅ፣ የእናንተ ተስፋ ነው። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በድል ለመኖር የሚያስፈልጋችሁን ማንኛውንም ነገር ይሰጣችኋል።

ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በምንጠብቅበትና ከእርሱ ጋር ጊዜ በምናሳልፍበት ጊዜ፣ እንዲሁም በይበልጥ እርሱን በምንመስልበት ጊዜ ጎይላችንን እንደምናድስ ይናገራል። ማደስ ማለት "እንደገና መመለስ፣ ዐዲስ መሆን፣ ወደ አንድ ነገር መጀመሪያ መመለስ" ማለት ነው። እግዚአብሔርን በምንጠብቅበት ጊዜ ጎይላችን እንደገና ዐዲስ ይሆናል፣ በሕይወት ማዕበል ላይ እንደ ንስር ለመብረር እንችላለን፣ ሳንደክም ለመራመድና ለመሮጥ እንችላለን። ብዙ ያደክመንን ሁኔታ በዐዲስ ጎይልና የጋለ ፍላጐት ልንቀርበው እንችላለን። ስኬትን በምናጣበት ጊዜ እንኳ፣ እንበረታታለን፣ ጎይልን እናገኛለን፣ እጅ ለመስጠትም አንፈልግም።

ንስሮች ለጥንካሬ ምሳሌ የሚሆኑበት አንዱ ምክንያት ጥንካሬአቸው እንዴት እንደሚሠራላቸው ስለሚያውቁ ነው። እነርሱ ጎይላቸውን በከንቱና አላስፈላጊ በሆነ ነገር ላይ አያባክኑም። እነዚህ አስገራሚ ወፎች የግዙፉ ዓለም የአየር ፍሰት እንዲሸከማቸው መፍቀድን እንዴት እንደሚያውቁ ሁሉ፣ "ንስር ክርስቲያኖችም" የመንፈስ ቅዱስን መፍሰስ ይረዳሉ። ንስር ክርስቲያኖች የመንፈሱን እንቅስቃሴ ስለሚያዩ በሕይወታቸው በቀላሉ ያለ ውጥረት፣ ያለ ጥረትና ያለ ከንቱ ጫና በቀላሉ ለመፍሰስ ይችላሉ። ይህም እግዚአብሔርን ከመጠበቅ የሚገኝ ሲሆን በሕይወታቸው በጥንካሬ፣ በጎይልና በብርታት ለመራመድ ያስችላቸዋል።

ብዙ ጊዜ፣ ሰዎች "አንቺና ዴቭ በዚህ እድሜያችሁ አሁን የምታደርጉትን እንዴት ለማድረግ ቻላችሁ?" ብለው ይጠይቁኛል። ሐቁ ግን፣ እኛ ምናልባት በጉባኤያችን ውስጥ ካሉት ከባለ ሠላሳ ዓመት እድሜ ሰዎች የተሻለ ስሜት ያለን መሆኑ ነው። ለዚህ አንዱ ምክንያት የሚሆነው እኛ ሰውነታችንን በጥንቃቄ ስለምንጠብቅ ነው። ጤናማ አመጋገብ አለን፣ የአካል ልምምድ እናደርጋለን፣ ብዙ ውሃ እንጠጣለን፣ እንዲሁም በቂ እንቅልፍ አለን። ከመጠን በላይ የሆነውን ጫና ከሕይወታችን እናስወግዳለን፣ እናም ጌታን መጠበቅ ተምረናል።

ኢየሱስ፣ የደከመ፣ ያለቁና የዛሉ ሰዎች ወደ እርሱ እንዲመጡ ተናግሮአል (ማቴዎስ 11÷28 ይመ.) እርሱም ያሳርፋቸዋል።

ብዙ ጊዜ፣ በጉባኤያችን እኔ በምናገርባቸው ስብሰባዎች መካከል በሆቴል ክፍሌ ውስጥ አልጋዬ ላይ በመጋደም ሰውነቴን አሳርፋለሁ። ደግሞም ይህን ጊዜ ከጌታ ጋር ለመነጋገር እጠቀምበታለሁ። እኔ ብዙ ውብ የሆኑ ቃላት አልናገርም፣ "ጌታ ሆይ እወድሃለሁ፣ አንተ ታስፈልገኛለህ፣ ዛሬ ማታ እርዳኝ። ዛሬ ስለአደረግኸው ነገር አመሰግንሃለሁ" እላለሁ። በእነዚህ ወቅቶች የማሳርፈው አካሌን ብቻ አይደለም፣ በተጨማሪም እግዚአብሔር ረዳቴና ብርታቴ እንደሚሆን ስለምተማመንበት መንፈሳዊ አረፍት ይኖረኛል።

አንዳንድ ጊዜ እደክማለሁ - በአካል ብቻ ሳይሆን በሌሎች መንገዶችም ስለምደክም ከአጭር ጊዜ እረፍት በላይ ያስፈልገኛል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ በተቻለ መጠን ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ለብቻዬ ጊዜ አሳልፋለሁ። ቡናዬን ይዤ ወደ አንድ ቦታ በመሄድ በወንበር ላይ ተቀምጬ ፀጥ እላለሁ። ከእግዚአብሔር ጋር የፀጥታ ጊዜ እንዲኖረኝ አፈልጋለሁ፣ ደግሞም ከእርሱ ጋር የማሳልፈው ይህ ጊዜ ጎይሌን እንደሚያድሰው አውቃለሁ።

ከመታደስ አስፈልጐት ነፃ የሆነ ሰው የለም፣ ሁሉም ሰው የእረፍት፣ የመዝናናትና የመታደስ ጊዜ ያስፈልገዋል። እናንተም በሕይወት ዘመን በምትጓዙበት ጊዜ ትደክማላችሁ። ብስጭት በሚያጋጥማችሁ ጊዜ፣ ትደክማላችሁ። የጊዜ ገደቦችን፣ በጀቶችንና የተመደቡ ድርሻዎችን ለማሟላት ስትሠሩ፣ ትደክማላችሁ። ለፈተና ስታጠኑ፣ ትደክማላችሁ።

ድካም ሲመጣ፣ መጥፎ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። የደከመ ሰዎች ሳያስቡ ይናገራሉ፣ በኋላ የሚጸጸቱበትን አቋራጭ መንገድ ይወስዳሉ፣ እንዲሁም መጠበቅ ስለሚሰለቻቸው ከመልካሙ ባነሰ ነገር ላይ ረክተው ይቀመጣሉ። የደከመ ሰዎች ኃይላቸው እንዲታደስ ካላደረጉ በስተቀር፣ ጥበብ የጐደላቸው ይሆናሉ። ብዙ ሰዎች ደካማ ውሳኔ የሚወስኑት ስለ ደከሙና ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ጊዜ

ስለማይወስዱ፤ እንዲሁም ጎይላቸው እንዲታደስ አርሱን ስለማይጠብቁ መሆኑን አምናለሁ።

ሰዎች በመደበኛነት ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ቢችሉ፣ የተሻለ ምርጫ እንደሚያደርጉ እኔ እርግጠኛ ነኝ። እግዚአብሔርን የሚሹ ከሆነ ከእርሱ ይሰማሉ። እንዲያውም ብዙ ጊዜ እርሱ የሚናገር መሆኑንም ላይገነዘቡት ይችላሉ፤ ነገር ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለባቸውና ምን ማድረግ እንደሌለባቸው የሚያውቁ ሆነው ይገኛሉ።

> እግዚአብሔርን ለመጠበቅ ጊዜ ውሰዱና በክንፍ ትበርሩ ዘንድ ጎይላችሁን እንዲያድሰው ፍቀዱለት።

እግዚአብሔርን ለመጠበቅ ጊዜ መውሰድ ጀምሩና በክንፍ ትበርሩ ዘንድ ጎይላችሁን እንዲያድሰው ፍቀዱለት። ዛሬ ድካም ከተሰማችሁ፣ ወዲያውኑ አረፍት ውሰዱና "ጌታ ሆይ አወድሃለሁ፤ አንተ ታስፈልገኛለህ። ጌታ ሆይ፣ ትንሽ ድካም ተሰምቶኛል፤ አንተ አበርታኝ" በሉት። አሁን የሁለት ሳምንት እረፍት ለመውሰድ አትችሉም ይሆናል፤ ነገር ግን በየቀኑ በርከት ያሉ የዐምስት ደቂቃ እረፍቶችን ለመውሰድ ትችላላችሁ። በርከት ላሉ ቀናት ወጥታችሁ ለመሄድ አትችሉም ይሆናል፤ ነገር ግን ወደ መፀዳጃ ቤት ብትገቡ ወይም በመኪናችሁ ውስጥ ሆናችሁ የአምልኮ መዝሙር ብትሰሙ፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻችሁ ሁኑና "ኢየሱስ ሆይ፣ ትንሽ መታደስ ያስፈልገኛል። እወድሃለሁ። አመልክሃለሁ። አጠንክረኝና አድሰኝ" በሉት። እናንተ ለመጽናትና ስኬትን ለማግኘት ትችሉ ዘንድ እርሱ ሊያጠነክራችሁና ሊያድሳችሁ ይፈልጋል። እግዚአብሔርን መጠበቅ የተወሳሰበ ነገር መሆን የለበትም። ነገር ግን በቅደም ተከተላችሁ ዝርዝር መጀመሪያ ላይ አስቀምጡት። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ጊዜ ባለማሳለፋችሁ ያጣችሁትን ጥራት ያለው ሕይወት እንድታገኙና እንድትደሰቱበት ይፈልጋል።

መታደስ

መዝሙር 103 ÷2-5 እንዲህ ይላል፤

> ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፤ ውለታውንም ሁሉ አትርሺ፤ ኀጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፤ ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ፤ ሕይወትሽን ከጥፋት ጉድጓድ የሚያድን፤ ምህረትንና ርህራሄን የሚያቀዳጅሽ ጉልማሳነትሽም እንደ ንስር ይታደስ ዘንድ ምኞትሽን በበጐ ነገር የሚያረካ እርሱ ነው።

አብዛኞቻችን ጉልማሳነታችን የመታደሱን አሳብ እንወደዋለን። ወጣት ለመምሰልና ባለፈው ጊዜ የነበረንን ጎይል ለማግኘት እንፈልጋለን። ነገር ግን መዝሙረኛው "ጉልማሳነት" በሚልበት ጊዜ "የልብ ወጣትነት" - የደከመ፣ የዛለ፤ አሉታዊ ገጽታ ሳይሆን ለሕይወት ትኩስና የተንቃቃ አቀራረብ ማለቱ እንደሆነ አምናለሁ። ጉልማሳነት ማለት በዓመታት የሚቆጠር እድሜ ማለት አይደለም፤ እርሱ በውስጣችሁ የሚካሄደውን ነገር የሚመለከት ነው። እናንተ በሥጋ ውስጥ ትኖራላችሁ፤ ነገር ግን በውስጣችሁ መንፈስ አለ፤ ስለዚህ መንፈሳችሁን ካጠነከራችሁት፣ እርሱ ሥጋችሁን፣ አእምሮአችሁን፣ ስሜቶቻችሁንና ውሳኔዎቻችሁን በአምንታዊ መንገድ ይለውጣል። ንስር ጉልማሳነትን ስለማደስ አንድ ነገር የሚያስተምረን ባይሆን ኖሮ፣ መዝሙረኛው ጉልማሳነታችን እንደ ንስር የመታደሱን ጉዳይ አይጠቅስም ነበር። እኔ በበኩሌ የንስርን የመታደስ ሂደት በጣም ማራኪና ክቡር ሆኖ አገኘዋለሁ፤ ለእናንተም እንዲሁ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ።

የመታደስ ሂደት

በንስር ሕይወት ውስጥ እንደ በፊቱ ፈጣን የማይሆንበት ጊዜ ይመጣል። የበረራ አነሳሱም ከዓመታት በፊት እንደ ነበረው ፈጣን አይደለም፤ በረራው ዝግ ያለ ነው፤ የበፊቶቹ ስለታም ጥፍሮች ደንዝዘዋል፤ በአፉ (በመንቆሩ) ላይም ካልሲየም የተባሉት ንጥረ ነገሮች ተጋግረውበታል፤ ክንፎቹም ስላለቁ ምርኩውን ለማግኘት ወደ ታች ሠርጉ በሚበርርበት ጊዜ አላስፈላጊ ፉጨት ያሰማሉ። እርሱ አሁንም

ቢሆን ንስር ነው፤ ነገር ግን አብዛኛውን ጥንካሬውንና ጀግንነቱን አጥቶአል።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ ንስሩ በተቻለው መጠን ወደ ፀሐይ በመቅረብ በከፍተኛ ዐለት ላይ ይቀመጥና ላባዎቹን በሙሉ አንድ በአንድ ይነቅላቸዋል፤ አንዳንድ ጊዜ ላባዎቹ እስከ ሰባት ሺህ ይደርሳሉ። እርሱ ለአድገቱ የሚጨነቀውን ያህል ለሕመሙ አይጨነቅም። ከዚያም ራሱን የሚያፀዳበት ቀዝቃዛና ንጹህ ውሃ ያለበት ወንዝ ይፈልጋል። ውሃውም በጊዜ ብዛት በእርሱ ላይ የተከማቸውን ጭቃና አፈር፣ ትላትሎችና ሌሎች ነፍሳት ያጥበለታል። እርሱም ዐዲስ፣ ንጹህና ራቁት በሆነ ጊዜ፣ በፀሐይዋ ፊት ይቆምና መጠበቅ ይጀምራል።

እንደገና ለማደግ የሚያስፈልገው ጊዜ አርባ ቀናት ያህል ይሆናል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ጥፍሮቹንና መንቆሩን በዐለት ላይ በመፈግፈግ ስለታም እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ያንኑ ዐለት በአፉ ላይ የተላከከውን ካልሲየም የተባለ ንጥረ ነገር ለማራገፍ ይጠቀምበታል። በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፉ ሌሎች ንስሮች ምግብ ሊጥሉለት ይችላሉ። እርሱም በአንፃራዊ ሁኔታ ደካማ የሆነ የፀጥታ ጊዜ ያሳልፋል፤ ነገር ግን ጎይሉ ይታደሳል።

ንስሩ ካለፈበት ከዚህ ሂደት አንድ ነገር እንድንማር እግዚአብሔር ይፈልጋል ብዬ አምናለሁ። እኛም ድርቀት፣ ድክመት፣ ሽንፈትና ተስፋ ቢስነት የሚሰማን ጊዜ አለ። ሕይወታችን በጎይለኛ (በመረረ) ምት የሚመታበትና ሕልማችን ሁሉ በዐይናችን ፊት የሚፈረካከስበት፣ የምንወደው ሰው እኛን የሚያቆስልበት፣ የምናምነው ሰው የሚክዳበት፣ ይሠራል ብለን ያሰብነው ነገር ሳይሠራ የሚቀርበት ጊዜ አለ። እነዚህ መሸሸን እንድንፈልግ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ናቸው። በእነዚህ ወቅቶች፣ በርግጥ መታደስ ያስፈልገናል። ለመታደስ ጊዜ ካልወሰድን በስተቀር፣ ለሁኔታዎች ስሜታዊ ምላሽ የመስጠት አደጋ ይገጥመናል፤ ይህም ሁልጊዜ ያለ ጥበብ ምላሽ የመስጠት ችግር ሲሆን ይህም ብዙ ጊዜ መጥፎ ሁኔታዎችን የባሰ መጥፎ እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

እነዚህ ወቅቶች በርግጥ እግዚአብሔርን አጥብቀን እንድንፈልገው የሚያደርጉ ናቸው። በየዕለቱ ጊዜያችንን ከምንሰጥባቸው ጉዳዮቻችን በላይ ጊዜ መመደብ ያስፈልገናል። አንዳንድ ሰዎች ከንስሩ ትምህርት ማግኘትና ለአርባ ቀናት ያህል የጸሎትና የጾም፣ እግዚአብሔርን የመሻት፣ እርሱን የማምለክና ልባቸውንም ለእርሱ የማፍሰስ ጊዜ መመደብ ይኖርባቸው ይሆናል። ከቶ ጾመው የማያውቁ ሰዎች ይህ ከራር ሊመስላቸው ይችላል፤ ነገር ግን የተቸገሩ ሰዎች በአስቸጋሪ ጊዜ አስቸጋሪ ነገሮችን ያደርጋሉ። ሌሎች ሰዎች ለሕይወታቸው ሰላምን ለማግኘት ሥር ነቀል ለውጥ ያስፈልጋቸዋል፤ ለጥቂት ጊዜ ቴሌቪዢናቸውን መዝጋት፣ ወይም በእያንዳንዱ ምሽት ለተወሰነ ጊዜ ተንቀሳቃሽ ስልካቸውን መዝጋት ያስፈልጋቸዋል። ምናልባት እናንተም ፍሬ የማይሰጠውንና መቆረጥ ያለበትን ነገር ለመወሰን ሕይወታችሁን መመርመር ይኖርባችሁ ይሆናል።

> ለራሳችን ከምንሰጣቸው እጅግ መልካም ስጦታዎች አንዱ ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻችን ጊዜ ማሳለፍ ነው።

እኔ ሁላችንም የተራዘሙ ወይም ጠንከር ያሉ የመለወጥና የመታደስ ጊዜያት እንደሚያስፈልጉን አምናለሁ። በግሌ በዓመት ሦስት ወይም አራት ጊዜ ገለል ብዬ ለብቻዬ የምሆንበትን ጊዜ ለመመደብ እሞክራለሁ። እነዚህን ጊዜያት ለመውሰድ ጥረት አደርጋለሁ፤ ምክንያቱም ለራሳችን ከምንሰጣቸው እጅግ መልካም ስጦታዎች መካከል አንዱ ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻችን ጊዜ ማሳለፍ መሆኑን ስለማምን ነው። እውነተኛ የሆኑ የፀጥታ ጊዜያት ያስፈልጉናል፤ ምክንያቱም በእነዚህ ጥልቅ በሆኑ የሰላምና የፀጥታ ስፍራዎች ከእግዚአብሔር ጋር በከፍተኛ ደረጃ ስለምንገናኝ ነው። ከእግዚአብሔር የተወሰነ "ቃል" አግኝቼአለሁ የሚል ስሜት እንዲኖረን አያስፈልግም፤ ወይም ደግሞ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ልምምድ ማግኘት አያስፈልገንም። ልዩ የሆነ፣ የተመደበ ጊዜ ለእርሱ በመስጠት እግዚአብሔርን ማክበር ለሕይወታችን ታላላቅ ውጤቶችን በማስገኘት መለወጥንና መታደስን ያመጣል። በዚህ ጊዜ የተሻሉ ውሳኔዎችን ስናደርግ፣ በቀላሉ የቅድስናን ባሕርይ ስናላይና በመላው ሕይወታችን በይበልጥ ስንደሰት እንገኛለን። ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር

ከምንሰጣቸው እጅግ አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ነው። ይህም እርሱ ለእኛ አስፈላጊያችን መሆኑንና ያለ እርሱም ሕይወትን በተገቢው መንገድ ልናስተናግድ የማንችል መሆናችንን ይገልጽለታል።

ስኬትን ለማግኘት ጥረት በምታደርጉበት ጊዜ ታማኞችና ቁርጠኞች መሆንን፣ እንዲሁም ኀይላችሁን ለማደስ ጌታን መጠበቅን አስታውሱ። ይህንን በምታደርጉበት ጊዜ ያለ እጅ መስጠት ጉዞአችሁን እንድትቀጥሉ የሚያስችላችሁን ኀይል ትቀዳጃላችሁ።


የምድረ በዳው ድምፅ

በ1897 በፊላደልፊያ "የጥቁሮች ስፈር" ውስን የገንዘብ አቅም ከነበረው ከተወደደ ቤተሰብ የተወለደችው ማሪያን አንደርሰን ለችግርና ለስደት እንግዳ አልነበረችም። እርሷ ገና የዐሥር ዓመት ልጅ ሳለች አባቷ ሲሞት የገንዘብ ችግር ተፈጠረ፤ እናቷም ማሪያንንና ሁለት እህቶቿን ለመደገፍ በጽዳትና በላውንደሪ ሠራተኝነት ተቀጥራ ትሠራ ጀመር።

የማሪያን አስደናቂ የመዘመር ችሎታ ያለዚህ ቢሆን ኖሮ ልታገኛቸው የማትችለውን እድሎች አስገኝላት። ዘሐብረት የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን (ዩኒያን ባፕቲስት ቸርች) ውስጥ መዘመር ስትጀምር ወዲያውኑ ሰዎቹ የእርሷን አስደናቂ የድምፅ ጥራት፣ ርዝመትና ብልጽግና በቀላሉ ሊገነዘቡ ቻሉ። ዝማሬዋ አንድ የተለየ ነገር እንደሆነ አወቁ። ደግሞም የማሪያን ቤተሰብ እርሷ መደበኛ የሆነ የድምፅ ሥልጠና እንድታገኝ ለማድረግ አቅማቸው የማይፈቅድ መሆኑን ተገንዘቡ፤ ስለዚህ ለእርሷ የድምፅ ትምህርት ክፍያ የሚያገለግል ገንዘብ ለማግኘት ማሪያን ሶስ ዘማሪ የሆነችበትን የገንዘብ ማሰባሰቢያ የሙዚቃ ድግሥ ቤተክርስቲያን አዘጋጀች።

ደግሞም ቤተሰቧ ለእርሷ የፒያኖ ትምህርት ገንዘብ ሰመክፈል አይችልም ነበር፤ ስለዚህ ፒያኖ መጫወትን በራሷ ተማረች። ደግሞም ቫዮሊን መጫወትን ለመማር በፊሰንች ጊዜ የራሷን መሣሪያ ለመግዛት ገንዘብ ለማግኘት ስትል ደረጃዎችን የመወልወል ሥራ ትሠራ ጀመር። በግልጽ እንደሚታየው እርሷ ለመዚቃ እውቀት ታማኝ ነበረች። በአንድ ወቅት በፊላደልፊያ የመዚቃ ትምህርት ቤት ለመግባት ልትመዘገብ ስትሄድ በአንድ ወጣት እንግዳ ተቀባይ ሴት መጥፎ አቀባበል ተደረገላት። ማሪያንም ምዝገባውን ለመከታተል የነበራትን ፍላጐት በምትገልጽበት ጊዜ እንግዳ ተቀባይዋ ሴት "ባለ ቀለሞችን አንቀበልም" የሚል መልስ ሰጠቻት።

በዐሥራ ዘጠኝ ዓመቷ ማሪያን ጁሴፔ በጌቲ ከተባለ በጣም ከታወቀ የድምፅ አስተማሪ ጋር ተዋወቀች፤ እርሱም ለዓመታት የእርሷ አስተማሪ፣ አሠልጣኝና ጓደኛ ሆነላት። የእርሷ ችሎታና እውቅና እያደገ ሲሄድ ለመዘመርና፣ እንዲያውም ለንብኘት አንኳ ግብዣ መቀበልን ጀመረች። ከእርሷ የልበ ሙሉነት ጥንካሬና ፀሎታዊ ከነበሩት ጠንካራ



ምዕራፍ 9

የስኬት እንቅፋቶችን ማሸነፍ

"በአንድ አጣብቂኝ በሆነ ሰፍራ በገባህና ሁሉም ነገር አንተን የሚቃወምህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ለአንድ ደቂቃ እንኳ ወደፊት ለመቀጠል የማትችል ሲመስልህ፣ ከዶ እጅ አትስጥ ምክንያቱም ሁኔታው የሚቀየርበት ትክክለኛ ሰፍራ ይህ በመሆኑ ነው::"

ሐሬት ቢቸር ስቶው::

አንድ አህያ በአንድ ጥልቅ በሆነ የውሃ ጉድጓድ ውስጥ ወደቀ፤ የአህያው ባለቤት የሆነ ገበሬም፣ አህያውን እንዴት እንደሚያወጣው ለማወቅ አልቻለም:: ገበሬው ብዙ ካሰበበት በኋላ ከሁሉም የተሻለው መፍትሔ አህያውን ከጉድጓዱ ውስጥ መቅበር ስለሆነ አንዳንድ ጓደኞቹን ለመጥራት ዐሰበ:: ገበሬው ነገሩን ሲያመዛዝነው አህያው ያረጀ ስለሆነ እርሱን ከጉድጓድ ለማውጣት መሞከር ብዙ ችግር መፍጠር ነው ብሎ ገመተ::

የአካባቢው ገበሬዎችም አካፋቸውን ይዘው መጡና ሁሉም በአህያው ላይ አፈር ይጨምሩ ጀመር:: አህያውም ለጥቂት ጊዜ አስከፊ ድምፅ ማሰማት ጀመረ:: ከዚያም አህያው ፀጥ አለ:: ሰዎቹም በጉድጓዱ ቁልቁል ሲመለከቱ አስገራሚ ነገር አዩ::

እነርሱ አንድ አካፋ ሙሉ አፈር በውሃው ጉድጓድ ውስጥ በጨመሩ ቁጥር፣ አህያው ከላዩ ላይ ያራግፈውና አፈሩ በላዩ ላይ በመሆን ፈንታ ከእግሩ ሥር ይሆን ጀመር:: እነርሱም ምስኪኑን አህያ ለመቅበር አፈር መጨመራቸውን ሲቀጥሉ፤ አህያውም ከላዩ ላይ ማራገፉን ቀጠለ! አህያውን ለመቅበር የሞከሩበት የአፈር ክምር ወደ

ዲጋፊዎች የተነሣ በ1924 በኒውዮርክ የከተማ አዳራሽ ለመዘመር ዝግጅት አደረጉ። በዚያም የተገኘው ሕዝብ በጣም አነስተኛ ከመሆኑና በአሉታዊ መንገድ ስለተዘገበ፣ ጭራሹንም መዚቃን ለመተው ታስቦ ጀመር።

ነገር ግን ማሪያን ወዲያውኑ ተመለሰች። ከዚያም በፊላደልፊያ ፊልሃርሞኒክ ሶሳይቲ አስተባባሪነት በተዘጋጀ የድምፅ ውድድር አሸናፊ ከሆነች በኋላ፣ በሌዊሶን ስታዲዮም በተካሄደው ውድድር ከሦስት መቶ በላይ ከሚሆኑ ተወዳዳሪዎች አሸናፊነትን አገኘች። ከዚያም አንደጋና ተብኔን ጀመረችና በ1928 በክርኔጅ አዳራሽ ብቻዋን (ሶሎ) ዘመረች።

አንደርሰን ምንም አንኳ ከፍተኛ የአፈጻጸም ችሎታ ቢኖራትም፣ በ1939 በዘር መድልዎ ምክንያት አንዳንድ አድሎችን ተከለከለች። በዚያው ዓመት የዋሽንግተን ዲ.ሲ የሕገ መንግሥት አዳራሽ ባለቤቶች፣ በቀለሟ ምክንያት አንዳትዘምር ከለከሏት። የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ባለቤት ወ/ሮ ኤሊያኖር ሩዘቬልት የሆነውን ነገር በሰማች ጊዜ፣ ማሪያን በሊንከን መታሰቢያ ስፍራ እንድትዘምር ዝግጅት አደረገችላት። በውጪ (በሜዳ ላይ) ቢተደረገው የመዚቃ ድግስ በግምት ሰባ አምስት ሺህ ሰዎች ተገኙ። ያ ሁኔታ በአሜሪካ የሕዝብ መብት እድገት ላይ ከፍተኛ ምዕራፍ ነበር፣ ከዚህም የተነሣ በዘር መድልዎና በሲፍትሐዊነት ይሰቃዩ ለነበሩት ለብዙ ሰዎች ሕልሞቻቸውን እንዲከተሉ ድፍረትን ሰጣቸው።

አንደርሰን በኒውዮርክ ሜትሮፖሊተን ኦፔራ ለመገኘት የመጀመሪያዋ አፍሪካ አሜሪካዊት ሶሎ ዘማሪ ለመሆን በቃች። ደግሞም በምረቃ ሥነ ሥርዐቶች ላይ ከመዘመሯም ሌላ፣ በ1963 የፕሬዚዳንታዊውን የነፃነት ሜዳሊያንና በ1991 ለሕይወት ዘመን ተግባር የፕሬሚ ሽልማትን ጨምሮ ብዙ የተከበሩ ሽልማቶችን አገኘች። የአርሲ ከፍተኛ ሙያ ወደ መደምደሚያው በተቃረበ ጊዜ፣ በ1956 በአንድ ወቅት በጠራቸው እንዳትገባ በከለከሏት ስፍራ፣ ማለትም በዋሽንግተን ዲ.ሲ የሕገ መንግሥት አዳራሽ አሸናፊ በሆነ የመዚቃ ድግስ የስንበት ጉብኝት አደረገች።

እናንተም ዛሬ ምንም ዐይነት በር የተዘጋባችሁ ቢመስላችሁ ወደፊት ሂዱ እንጂ ኩቶ እጅ አትስጡ። እናንተ በቁርጠኝነት ጽኑ እንጂ ዛሬ የማይቻሉ የሚመስሏችሁ አድሎች ነገ ለእናንተ ክፍት ይሆናሉ።

ላይ አደገና ብዙም ሳይቆይ ከጉድጓዱ ጫፍ ላይ አደረሰው፤ ከዚያም አህያው ከአፈሩ ላይ በቀላሉ ተራመደና ወደ ሜዳ ወጣ።

አህያው በዚያ ዝም ብሎ በመቆም አፈሩ እንዲቀብረው ቢፈቅድ ኖሮ አይድንም ነበር። ነገር ግን ከጉድጓዱ ውስጥ ለመውጣት ቆርጦ ነበር። አንድ አካፋ አፈር በላዩ ላይ ባረፈ ቁጥር፤ ያራግፈውና በአፈሩ ላይ ይቆማል።

እናንተም እንደ አህያው እንድታደርጉ እፈልጋለሁ። የሚያጋጥሙአችሁ ችግሮችና እንቅፋቶች ለሕይወታችሁ ግቦች የመረማመጃ ድንጋዮች እንዲሆኑ ተጠቀሙባቸው። የማይቻል የሚመስል ሁኔታ በመንገዳችሁ ላይ ቢጋረጥባችሁ፤ እንዲቀብራችሁ አትፍቀዱለት። አንቅፋቱን ለማሸነፍ የፈጠራ ችሎታ ይኑራችሁ። ለእናንተ እንዲሠራ እንጂ በእናንተ ላይ እንዳይሠራ ቁርጠኞች ሁኑ። ምንም እንኳ በችግሩ ላይ ለመቆም በአንድ ጊዜ አንዲት እርምጃ ብቻ መውሰድ የሚጠይቃችሁ ቢሆንም፤ ለእናንተ ጥቅም እንዲውል አድርጉት። እናንተን ሊያፍኑአችሁ የሚችሉት ሁኔታዎች የሚያጠነክሩአችሁና ወደ ዐዲስ ደረጃ ከፍ የሚያደርጓችሁ እንዲሆኑ ተጠቀሙባቸው። "እችላለሁ" የሚል ቁርጠኛ አስተሳሰብን ታዳብሩ ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሥራት ፈቃደኞች ሁኑ። የእርሱ ኀይል በእናንተ ውስጥ በመሥራት ላይ በመሆኑና፤ በመንገዳችሁ ላይ ምንም ነገር ቢደቀንባችሁ ኀይልን በሚሰጣችሁ በክርስቶስ ሁሉን በምትችሉበት ሐቅ ላይ ሆናችሁ ተንቀሳቀሱ (ፊልጵስዩስ 4÷13 ይመ)።

ስኬታማ የመሆን እርግጠኝነት

እውነተኛ ስኬት ለማንም ሰው ቢሆን በቀላሉ ወይም ያለ መሰናክል አይገኝም። ስኬት ጠንክሮ የመሥራት፤ የትዕግስት፤ የቁርጠኝነት፤ የፈጠራ ችሎታ ባለቤትነት፤ የመስዋዕትነትና ስህተትን አልፎ ወደፊት የመሄድ ውጤት ነው ነገር ግን ይመጣል። እናንተ የምትወድቁበት ብቸኛው ምክንያት እጅ መስጠታችሁ ነው፤ ደግሞም ተቃውሞ በሚያጋጥማችሁ ጊዜ ይህን ለማድረግ እንደምትፈተኑ የታወቀ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ እንደሚያስተምረን፤ እኛን ለማበሳጨትና ለማሸነፍ የሚፈልግ ጠላት አለ። የእርሱ ዋና ግብ እኛን "ሊሰርቅ፤ ሊገድልና ሊያጠፋ" ነው (ዮሐንስ 10÷10)፤ ደግሞም የሚውጠውን በመፈለግ [በክፍተኛ ረሃብ] "እንደሚያገሳ አንበሳ ወዲያና ወዲህ በመዞር" ጊዜውን ያሳልፋል (1ጴጥሮስ 5÷8)። ሰይጣን በተቻለው መንገድ ሁሉ በስኬታችን እኛን ለመቃወምና ጣልቃ ለመግባት ይጥራል፤ እኛ እጅ እንድንሰጥም ተስፋ ለማስቆረጥ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል።

እናንተ በማንኛውም የሕይወታችሁ አቅጣጫ ስኬታማ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ - በሥራችሁ፤ በግንኙነቶቻችሁ፤ በትዳራችሁ፤ በወላጅነታችሁ፤ በገንዘባችሁ፤ በጤንነታችሁ፤ በአገልግሎታችሁ፤ በፈጠራ ችሎታችሁ፤ የእግዚአብሔርን እቅድ ለመከተል በምታደርጉት ጥረትና በምትሠሩት በማንኛውም ሌላ ነገር ሁሉ ስኬታማ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ። ነገር ግን ዘላቂ የሆነ ስኬት ጥረትን እንደሚጠይቅ አውቃለሁ፤ እናንተም ስኬት ለማግኘት በምትሠሩበት ጊዜ፤ ጠላት ስኬቱን ሊሰርቅ፤ ሊገድልና ሊያጠፋ ይመጣል። እናንተ እንደጠበቃችሁት ስኬት በቀላሉ በማይገኝበትና በመንገዳችሁ ላይ እንደሚያጋጥማችሁ አይቀሬ የሆነውን እንቅፋት በምትጋፈጡበት ጊዜ፤ በጥንካሬ ጉዞአችሁን መቀጠል ወሳኝ ነው።

መሰናክልን ማስወገድ፡- ቁጥር 1 - የመሸሽ ፈተና

ጥሎ የመሸሽ ፈተና ሰው የመሆን አንዱ ክፍል ነው፤ ነገር ግን ለፈተና መማረክና እጅ መስጠት ተመሳሳይ ናቸው። በፈተና ላይ አንድ ነገር ሳናደርግ ዝም ብለን በመቀመጥ ወይም እግዚአብሔር እንዲያስወግደው በመመኘት ለማምለጥ አንችልም። ፈተና ከክርስትና ሕይወት ተጨባጭ እውነታዎች አንዱ ሲሆን እኛ ልናሸንፈው የሚገባን የስኬት እንቅፋት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሉቃስ 22÷40 ላይ፤ "ወደ ፈተና

> አማኞችን መፈተን የዲያብሉስ የሥራ ክፍል ነው። በሕይወት እስከኖርን ድረስ እንፈተናለን፤ ደግሞም ኢየሱስን እስከተከተልን ድረስ ሥራችን ፈተናን መቃወም ነው።

እንዳትገቡ ጸልዩ" ይላል። አማኞችን መፈተን የዲያብሎስ የሥራ አካል ነው። በሕይወት እስከኖርኝ ድረስ እንፈተናለን፤ ደግሞም ኢየሱስን እስክ ተከተልን ድረስ ሥራችን ፈተናን መቃወም ነው።

ሁልጊዜ የተስፋ መቁረጥና ጥሎ የመሸሽ ስሜቶች ከጠላት መሆናቸውን እኛ ስለማንገነዘብ፣ እንደዚህ ያሉትን ፈተናዎች እንደሚገባን አንቃወምም። እናንተ እጅ እንድትሰጡ ለመፈተን ጠላት በአእምሮአችሁ ውስጥ የሚተክላቸው አንዳንድ አሳቦች ከዚህ የሚከተሉትን ይመስላሉ፦

- ይህ በጣም አስቸጋሪ ነው። ብዙ ጥረትን ይጠይቃል።
- በርግጥ ይህን ለማድረግ ብቃት የለኝም።
- በጣም ብዙ ችግሮች ስለአሉብኝ ሁሉንም ልፈታቸው አልችልም።
- የሚረዳኝ ሰው የለኝም።
- ይህንን በመከታተሌ ጓደኞቼና ቤተሰቤ እብድ ነህ ይሉኛል።
- ይህ በጣም ብዙ መስዋዕትነትን ይጠይቃል።
- ይህን ለማድረግ ገንዘብ የለኝም።
- ይህን ለመጨረስ ከቶ አልችልም።
- ይህን ሥራ ለመሥራት በተስማማሁበት ጊዜ ምን እያሰብሁ ነበር?
- ይህ ከቶ እንደማይሠራ አውቄ ነበር።
- ወደ ዱሮው ሥራዬ /ከተማዬ/ኑሮዬ/ አገልግሎቴ መመለስ ያስፈልገኛል። ሁሉም ነገር እዚያ ይሻል ነበር።

ጥሎ የመሸሽ ፈተና የጠላት ሥራ መሆኑን መገንዘብ እንድትጀምሩ እፈልጋለሁ፤ ደግሞም እያንዳንዱን ፈተና በሁለንተናችሁ መቃወም እንድትጀምሩ እፈልጋለሁ። ከፈተና ጋር አትቀልዱ፤ ወይም ደግሞ ማንኛውም ፈተና ትንሽ ነው ብላችሁ አታስቡ። ጠላት ወደ ቸልተኝነት እንዲወስዳችሁ አትፍቀዱለት፤ ወይም ዐላማችሁን እንድትተዉ ጠላት የሚያቀርብላችሁን የምክንያቶች ዝርዝር እያዳመጣችሁ መደበትና ተስፋ ቢስነት እስኪመጣባችሁ ድረስ አትጠብቁ ዲያብሎስን ገና ከጅምሩ ተቃወሙት! በፈተና ላይ ጦርነት

አውጁ። ለጠላት ምንም ምህረት አታሳዩ። እጅ እንድትሰጡ የመፈተን ስሜት ሲመጣባችሁ፤ ወዲያውኑ በቅጽበት *"እኔ ትቼ አልሸሽም። አልሸነፍም። እግዚአብሔር እንዳደርገው ያዘዘኝን አፈጽማለሁ"* ብላችሁ መጮህ ያስፈልጋችኋል።

ከሠላሳ ዓመት በላይ በሆነው አገልግሎቴ፤ በተለይ ብዙ ጉዞ ባደረግንባቸው በቀደምቱ ዓመታት ውስጥ፤ ብዙ ጊዜ ትቼ ለመሸሽ ተፈትኜአለሁ። ሌሊቱን ሰብክ አድራ ባደርኩበት ሆቴል ክፍሎች ውስጥ ጠዋት በምነቃበት ጊዜ በስብከት አገልግሎቱና በቢሮ አካባቢ ችግሮች መኖራቸውን በምሰማበት ጊዜ ፈጽሞ የደከመሁባቸውና የዛልሁባቸው ብዙ ወቅቶች ነበሩ የቢሮቼን ችግሮች በተመለከተ ለምሳሌ አንድ ሰው ሥራ ትቶ ይሄዳል፤ የእኔን ትኩረት የሚሻ አስቸኳይ ጉዳይ ይኖራል፤ ያልጠበቅነው የሚከፈል ዕዳ ይኖራል፤ ወዘተ። አንዳንድ ጊዜ ፈጽሞ ተስፋ እቆርጣለሁ፤ አንዳንድ ጊዜም እንባ ይመጣብኛል። በራሴ ሕይወት ውስጥ ባሉት ጫናዎች እኔ ራሴ የመሸነፍ ስሜት እያለብኝ ሰዎች ችግሮቻቸውን አልፈው ወደፊት እንዲጓዙ ለመስበክ ብዙ ጊዜ ልብሴን ለብሼ ለመሄድ አልፈልግም ነበር።

በዓመታት ውስጥ፤ ብዙ እጅ የመስጠት ፈተናዎችን መቃወም ነበረብኝ፤ ደግሞም ፈተናን ለመቃወም ከሁሉ የሚበልጠው መንገድ ሥራን በጸሎት መሥራት መሆኑን ተምሬአለሁ። ፈተናን ለመቃወም በምትቆመብት ጊዜ የራሳችሁን የፈቃድ ኀይል ብቻ ለመጠቀም ከመሞከር ይልቅ መጸለይና የእግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ በጣም ጥበብ ያለበትና ውጤታማ አካሄድ ነው። የእርሱን ኀይል በምትፈልጉበት ጊዜ እርሱ ይሰጣችኋል።

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ወደ ፈተና እንዳይገቡ እንዲጸልዩ በአንድ ቀን ሁለት ጊዜ ነገራቸው። በእርሱ ዐይን ይህን ያህል ከባድ ስጋት የሚፈጥር ከሆነ፤ እኛም በትኩረት ልናየው ይገባናል። ሉቃስ 22÷40 እና ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች ተመልከቱ፦ "እዚያም በደረሱ ጊዜ 'ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ' አላቸው ... ከጸሎትም ተነሥቶ ወደ ደቀመዛሙርቱ መጣ፤ እነርሱም ከሐዘን የተነሣ ተኝተው አገኛቸውና

'ለምን ትተኛላችሁ; ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ' አላቸው" ይላል (ሉቃስ 22÷40 ፣ 45-46)።

ከእግዚአብሔር ጋር እየሠራችሁ ለመሸሽ ፈተና እጅ እንዳትሰጡ ጸልዩ። እርሱ የተጠራችሁለትን ነገር ለመፈፀም፣ እንድትሆኑ የሚፈልገውን ነገር ለመሆን፣ እንድታደርጉ የሚፈልገውን በሙሉ ለማድረግና እንድታገኙ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት እንዲረዳችሁ ጠይቁት።

መሰናክልን ማስወገድ ቁጥር 2፦ የግል ችግሮች

እግዚአብሔር የሰጠንን አንድ ሥራ ለመፈጸም የቆረጥን መሆናችንን ጠላት በሚያይበት ጊዜ፣ እጅ እንድንሰጥ ከሚያደርገባቸው ውጤታማ መሣሪያዎች አንዱ የግል ሥቃይ ነው። በሕይወት ዘመናቸው የግል ቀውሶችና ችግሮች ያጋጠሙአቸውን ብዙ ሰዎች እኔ አይቻለሁ፤ እኔም ራሴ ግቦችን ለመፈጸም ወይም ሕልሞችን እውን ለማድረግ ወደፊት በምራመድበት ጊዜ የግል ሥቃይ ተሞክሮ አለኝ።

አንድ ጊዜ ልጃችንን በሚመለከት በአንድ አስቸጋሪ ሁኔታ ልቤ በተሰበረበት ጊዜ አንድ ትምህርታዊ ጉባኤ ማካሄድ ነበረብኝ። እኔ ከምናገርበት ስፍራ ከመድረኩ በስተጀርባ አንድ አነስተኛ ክፍል ነበረች፤ ክፍሏ በንግግር ስብሰባዎች መካከል እረፍት ለመውሰድና ለመታደስ ጥሩ ስፍራ ነበረች። እኔም የምናገርበት ጊዜ ሲደርስ ወደ መድረኩ እሄድና ስብሰባውን እንደ ተለመደው እመራለሁ። ከዚያም ከመድረኩ በስተጀርባ እሄድና አለቅሳለሁ። የሚቀጥለው ስብሰባ ሲጀመር እንባዬን ጠርጌ እንደገና ኃላፊነቴን እፈጽማለሁ፤ ከዚያም ወደዚያች ትንሽ ክፍል ገብቼ ጥቂት አለቅሳለሁ። ይህንንም ኡደት ስብሰባው እስኪያልቅ እደጋግመዋለሁ። በግሌ በጣም እየተጐዳሁ ነበር፤ ቢሆንም ኃላፊነቴን እየተወጣሁ ነበር።

እኛ በቁርጠኝነትና በትጋት የምንጸና ሰዎች ለመሆን ከፈለግን፣ በግል ችግራችን ወቅት በሰላም ማለፍን መማር ያስፈልገናል። ጽኑ ባሕርይ ያላቸው ሰዎች፣ "እኔ ችግር ስላለብኝ ዛሬ ማታ ሥራዬን

ልሠራ አልችልም! እኔ በግል ቀውስ ውስጥ ነኝ፤ ስለዚህ ሰዎች እኔ እንዳገለግላቸው እንዴት ይጠብቃሉ?" አይሉም።

ይህ ለእናንተ ሞኝነት ሊመስላችሁ ይችላል፤ ነገር ግን የግል ችግሮቻቸው በሕይወታቸው ላይ ገዢ የሚሆኑባቸው ሰዎች አሉ፤ ሰዎቹ ከገቡት የተስፋ ቃል ውስጥ የትኛውን መፈጸምና የትኛውን መሠረዝ እንዳለባቸው የሚወስኑባቸው ችግሮቹ ናቸው። ሰዎቹ የግል ችግሮች ካሉባቸው፤ በቤተክርስቲያኑ በተመደቡበት የስንበት ዕለት የሕጻናት ማጫወቻ ክፍል ላለመሥራት ይወስናሉ። ሥራቸውን ለመሥራት ወይም ቃላቸውን ለመጠበቅ አይፈልጉም። አደርጋለሁ ያሉትን ነገር ሳያደርጉ ይቀራሉ፤ ምክንያቱም የግል ቀውሶቻቸው የገቡትን ቃል ላለመፈጸም ምክንያት የሚሆኑላቸው ስለሚመስላቸው ነው።

ከግል ችግር ጋር እየታገላችሁ ባላችሁበት ወቅት ሌላውን ሰው መርዳት እጅግ አስቸጋሪ ነው፤ ታማኝነትንና ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ራሳችሁ በጉዳት ላይ እያላችሁ፤ የተጐዱ ሰዎችን ማገልገል ትልቅ ተግዳሮት መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ። ራሳችሁ ችግር እያለባችሁ፤ የሌሎችን ሰዎች ችግር ማዳመጥ እጅግ ከባድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የግል ችግራችሁ ከፍተኛ ርህራሄን እንድታዳብሩ የሚረዳችሁና ይበልጥ ጥንካሬን ሊሰጣችሁ የሚችል ነገር ነው።

እናንተ በምትሰቃዩበት ጊዜም ቢሆን፤ በተቻለ መጠን ቃላችሁን መጠበቅና ሌሎችን ለመርዳት የሚቻላችሁን ሁሉ ማድረግ ይኖርባችኋል። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ እናንተ የገባችሁትን ቃል ለመጠበቅ ትጉሆች መሆን የሚያስፈልጋችሁና በአካባቢያችሁ ያሉትን ሰዎች ለመባረክ መንገድ መፈለግ ያለባችሁ በእነዚህ ወቅቶች ነው። የግል የፈተና ወቅቶች ለእግዚአብሔር የገባችሁትን ቃል የምትፈጽሙባቸውና እርሱን የምታገለግሉባቸው ትክክለኛ ወቅቶች ናቸው።

ሁላችንም በግል ችግሮች ውስጥ እናልፋለን፤ ደግሞም የገባነውን ቃል ለመጠበቅ የማንችልባቸው ወቅቶች አሉ፤ ነገር ግን

እንደዚህ ያሉትን ወቅቶች ለመቀነስ የተቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን። የእኛ ተግዳሮቶቻችን ጤንነታችንን፣ ልጆቻችንን፣ ትዳራችንን፣ ያረጁ ወላጆቻችንን፣ በሥራ ላይ ያለብንን ጫና፣ የጊዜ አጠቃቀማችንን፣ ወዘተ፣ የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ። እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን እቅድ ለመፈጸም ወደፊት በምንጓዝበት ጊዜ እነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሊያሰናክሉን አይገባም። በችግሮች ለመታገድ እምቢ የሚሉ ሰዎች በሥራቸው ላይ ትኩረት አድርገው ለመቆየት ቁርጠኞች የሚሆኑ ናቸው፣ ለእግዚአብሔር የተሰጡ፣ ለቤተሰባቸው በታማኝነት የሚፀኑ፣ በመንገዳቸው ላይ የሚያጋጥማቸውን ማንኛውንም እንቅፋት ለመጋፈጥ ቁርጠኞች የሚሆኑ ናቸው። እነርሱ በሕይወት ውስጥ አሸናፊዎች ናቸው።

መሰናክልን ማስወገድ ቁጥር 3፦ መገፋት

ሰዎች በሚገፉአችሁ ጊዜ፣ ማድረግ የሚገባችሁን ነገር ማድረግን ላትፈልጉ ትችላላችሁ፣ በዚህ ጊዜ የምትደበቁበትን ስፍራ ለማግኘትና ቁስላችሁን ለማስታመም ትፈልጉ ይሆናል። ነገር ግን ይህን አታድርጉ! የሚቃወማችሁ ወይም ሊያስቆማችሁ የሚሞክረው ማንም ይሁን፣ ወደፊት መጓዛችሁን ቀጥሉ።

ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ የሕይወታችሁን ሂደት ብትመለከቱ፣ እግዚአብሔር ወደ ዐዲስ ደረጃ ሊያሸጋግራችሁ በሚሞክርበት ጊዜ ሁሉ አንድ የሚቃወማችሁ ሰው ነበር። ያ ሰው በሆነ መንገድ፣ "ይህንን የምታደርግ ከሆነ እኔ የአንተ ጓደኛ አልሆንም" የሚል መልእክት አስተላልፎላችኋል። ብዙ ጊዜ ይህ ለምን እንደሚሆን ታውቃላችሁ? ምናልባት ከማንኛውም ነገር በላይ፣ ሰይጣን እኛ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመፈጸም ወደ ኋላ እንድንል በሰዎች የመገፋትን ሥቃይ ይጠቀምበታል። እኛ በምንወዳቸው ሰዎች የመገፋት ሥቃይ በጣም ሸካራ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ያዘዘንን ነገር ለማድረግ የነበረንን ቁርጠኝነት እንድንተው ያደርገናል። መገፋት፣ እኛ ማንንም ለማስደሰት ምንም ነገር ለማድረግ የማንችል መሆናችንን እንድናምንና እጅ እንድንሰጥ ያደርገናል። እኛ ሰዎችን ሁልጊዜ ለማስደሰት የማንችል

መሆናችንን ማስታወስ አለብን፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን ካስደሰትን፣ ዋናው ነገር እርሱ ነው።

ኢየሱስ በማቴዎስ 10 ÷ 5-14 የመገፋትን ጉዳይ አንስቶ ተናግሮአል። በዚህ ምንባብ ውስጥ፣ አንዳንድ ሰዎች እንደሚገፉአቸው ደቀመዛሙርቱን አስጠንቅቆአቸዋል፤ ይህንንም ተቃውሞ (መገፋት) እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ነግሮአቸዋል፦ "ማንም ሰው ሊያስተናግዳችሁ ወይም የምትናገሩትን ሊሰማ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ከቤቱ ወይም ከከተማው ስትወጡ የእግራችሁን ትቢያ አራግፋችሁ ውጡ" አለ (ቁጥር 14)። የዚህም እውነተኛ ትርጉም መገፋቱን (ተቃውሞውን) "አራግፎ" መውጣት ማለት ነው።

እግዚአብሔር እኔን በመንፈስ ቅዱስ በሞላኝ ጊዜ፣ እርሱ በሕይወቴ ለሚገልጠው ጥሪ እያስታጠቀኝ ነበር ይኸውም ቃሉን ማስተማር እንድጀምር ነበር። ያም በሆነ ጊዜ፣ ከዚህ በፊት የጠቀስሁት ትንሽ የመገፋት ተሞክሮ ደረሰብኝ። በሞላ ጐደል ሁሉም ጓደኞቼ፣ እኔ እብድ እንደሆንኩ ቆጠሩኝ። በዚያ ጊዜ እኔ በነበርሁበት አካባቢ ሴቶች መጽሐፍ ቅዱስን አይሰብኩም፤ ወይም አያስተምሩም ነበር። በዙሪያዬ የነበሩት ሰዎች በሙሉ የሚገፉኝ (የሚቃወሙኝ) መሆኑን ባወቅሁ ጊዜ፣ እግዚአብሔር እንዳደርግ በጠራኝ ነገር ላይ እጅ እንዳልሰጥ ቁርጠኛ መሆን ነበረብኝ።

በሕይወታችሁ ወደ ላይ "ከፍ" በምትሉበት ጊዜ - ሰዎች መልካም ነው ብለው የሚያስቡትን ነገር በምታደርጉበት ጊዜ፣ ወይም እውቅናን፣ ሞገስን ወይም ክብርን በምታገኙበት ጊዜ ብዙ ሰዎች ራሳቸውን ወደ እናንተ ማስጠጋት ይፈልጋሉ። ነገር ግን በሰዎች ዘንድ ተወዳጅነት የሌለው ወይም ያልተለመደ ነገር በምታደርጉበት ጊዜ፣ አንዳንድ ጓደኞቻችሁንም ልታጡ ትችላላችሁ። ለእግዚአብሔር አንድ ትልቅ ነገር ለመሥራት ከፈለጋችሁ፣ ለጥቂት ጊዜ መገፋትንና ብቸኝነትን ለመታገስ ፈቃደኞች መሆን ይኖርባችሁ ይሆናል። ነገር ግን ይህ ዋጋ ለእርሱ አይበዛበትም፤ በመጨረሻው ወደፊት በሚዳችሁ ትደሰቱበታላችሁ። ምንም ዐይነት መገፋት ቢያጋጥማችሁ፣ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ እንደሚቀበላችሁ እወቁ። እርሱ

የመገፋትን እንቅፋት አልፋችሁ በፊታችሁ ወዳለው ግብ እንድትጓዙ ይፈልጋል።

መሰናክልን ማስወገድ ቁጥር 4፦ በዐጭር ጊዜ ብዙ ነገርን መፈለግ።

በዓመታት ውስጥ ሰዎች "በአገልግሎትሽ ውስጥ እጅግ አስቸጋሪው ክፍል ወይም ተሞክሮ ምን ነበር?" ብለው ጠይቀውኛል። እኔም "መሠረቱን ስናስቀምጥ እጅ አለመስጠት ነው" የሚል ምላሽ ሰጥቻለሁ። ምንም እንኳ እጅ እንድንሰጥ የሚፈትኑን ብዙ ሁኔታዎች ያጋጠሙን ቢሆንም፣ በቀደምቱ ዓመታት ማለትም አገልግሎታችን በግልጽ ባልታየበትና ባልታወቀበት ጊዜ በትኩረትና በትጋት እንደ መጽናት ትልቅ ተግዳሮት የሆነብን ነገር የለም። በእርግጥ አገልግሎታችን ፍሬያማ እንዲሆን ፈልገን ነበር፣ ነገር ግን ይህን ከማግኘታችን በፊት ጠንካራ መሠረት እንደሚያስፈልገን እናውቅ ነበር። ይህም ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ መሠራት ነበረበት ማለት ነው።

ዴቭና እኔ በእግዚአብሔር የተጠራንለትን አገልግሎት ለማሳደግ በምንሞክርበት ጊዜ በግል ሕይወታችንም እያደግን ነበር። እግዚአብሔርም ስለ ጥራት፣ ስለ ሀቀኛነትና እንዲሁም ከግል ሕይወታችንና ከአገልግሎታችን ሁከትን ስለማስወገድ ለልባችን ይናገረን ነበር። ከመቼውም በበለጠ ሁኔታ ተወጥረን ነበር። ዴቭና እኔ እንዴት አብረን መሥራት እንዳለብን እየተማርን ነበር፣ ደግሞም ከግል ግንኙነታችን ውስጥ ሁከትን በማስወገድ ተግባር ላይ ጠንክረን ልንሠራበት የሚገባን ጉዳይ ነበር።

ብዙ የሚረዱን ሰዎች አልነበሩንም፣ እኛም ደግሞ ተሞክሮ አልነበረንም፣ ስለዚህ የምናደርገው ነገር ሁሉ ከባድ የእምነት እርምጃ ነበር። እያንዳንዱ ውሳኔ ለእኛ ትልቅ ነገር ነበር፣ እግዚአብሔርንም እንዴት መስማት እንዳለብን እየተማርን ነበር። በተለይ እኛ የምንችለውን ሁሉ እያደረግን፣ እድገቱ በጣም ዘገምተኛ ሲሆን ብዙ ጊዜ አድካሚና ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ ነበር።

እኔ ለዐምስት ዓመታት በሳሎናችን ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን በማስተማር ጀመርሁ። በእነዚያ ዓመታት በመጨረሻው ግማሽ ወቅት፣ እግዚአብሔር አንድ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በሌላ ሰው ቤት እንድንጀምር አደረገን፣ ስለዚህ በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ በግምት በሃያ አምስት ወይም በሠላሳ ሰዎች በሳምንት ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን አስተምር ነበር። በተጨማሪም ሌሎች ዐይነት አገልግሎቶችን አበረክት ነበር። ለምሳሌ፦ ማማከር፣ ሰዎች ከተለያዩ አሥራቶች ነፃ እንዲወጡ መርዳት፣ በከተማው ጉዳናዎች ላይ የወንጌል ሥርጭት በራሪ ወረቀቶችን ማሠራጨት፣ ብዙ መጸለይ - ማንኛውንም እግዚአብሔርን ለማገልገል የምችለውን ሁሉ አደርግ ነበር። እኔም ሌሎችን ለማገልገል መደበኛ ሥራዬን ተውሁ፣ ደግሞም ምንም እንኳ ገንዘብ ለማግኘት እየታገልን ቢሆንም እጅ እንዳንሰጥ እግዚአብሔር ጸጋውን ሰጠን።

ከዐምስት ዓመት በኋላ፣ እግዚአብሔር እድገትን ሰጠኝ። በሴይንት ሉዊስ ውስጥ ባለ በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለመሥራት ሄድኩና በዚያ ለዐምስት ዓመታት ሠራሁ። የመጀመሪያው ደመወዜ ስድሳ አምስት ዶላር ሲሆን ይህም ለእኔ እንደ ትልቅ ሀብት ነበር። በዚያም የሌቶች ስብሰባን ጀመርሁ። የእግዚአብሔር እጅ በዚያ ስብሰባ ላይ ነበረበት፣ ይህም በፍጥነት አደገና በየሳምንቱ ዐምስት መቶ ሴቶች ይሰበሰቡ ነበር።

ከጊዜ በኋላ፣ በዚያ ቤተክርስቲያን ተባባሪ መጋቢ ሆንኩ፣ ከዚያ በኋላም በቤተክርስቲያኒቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ውስጥ አስተማሪ ለመሆን ሄድኩ። ትንሽ በትንሽ እግዚአብሔር እያሠለጠነኝና እያጠነከረኝ ነበር፣ ነገር ግን እኔ ብዙ ጊዜ ከዚያ የበለጠ እፈልግ ነበር።

ጊዜው ደረሰና እግዚአብሔር ለልቤ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፦ *አሁን በዚህ ቤተክርስቲያን የምትሠሪውን ሥራ ጨርሻለሁ። የራሰሽን አገልግሎት ውሰጂና ወደ ሰሜን፣ ወደ ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ሂጂ አለኝ።* ጊዜ ቢወስድብኝም፣ ለዚህ ቃል በታዘዝሁ ጊዜ ከበፊቱ ይበልጥ ብዙ ስብሰባዎችን አካሄድ ጀመር፣ ነገር ግን ስብሰባዎቹ በመጠናቸው አነስተኛ ነበር። "እኔም ሁሉንም ነገር እንደገና

የምጀምር መስሎ ታየኝ! በርከት ያሉ ሰዎችን አገለግል ነበር፣ ነገር ግን እነርሱ በትናንሽ ቡድኖች ውስጥ ነበሩ፡- በአንድ ስፍራ ሰባ አምስት፣ በሌላ ስፍራ ስድሳ፣ በዚህ አንድ መቶ፣ በዚያ ሰማንያ አምስት ነበሩ። የአንድ መቶ አምሳ ወይም የሁለት መቶ ሰዎች ስብሰባ በምናካሂድበት ጊዜ፣ አንድ ትልቅ ነገር የምናደርግ ይመስለን ነበር! እኔም ከመቼውም በበለጠ ጥንካሬ እየሠራሁ የበለጠ ኃላፊነትም ነበረኝ።

በዓመቱ አገልግሎታችን እያደገ ስብሰባችንም እያደር በይበልጥ እየሰፋ ሄደ። ሦስት መቶ፣ ከዚያም አራት መቶ፤ ቀጥሎም አራት መቶ አምሳ ሰዎች ደረስን። በዚያን ጊዜ ይበልጥ እየታወቅንና በሌሎች ከተሞችም ስብሰባዎችን ለማካሄድ ጉዞ እየጀመርን ነበር። ከዚያ በኋላ ቢያንስ ለተወሰነ ወቅት እድገቱ አቆመ።

ነገር ግን አንድ ቀን ጠዋት ዴቭ ወደ ሥራ ለመሄድ በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በጎይል ጉበኘውና ማልቀስ ጀመረ። እግዚአብሔር ብዙ ሰዎች የሚኖሩበትን ሁኔታ አሳየውና ለዴቭ እንዲህ አለው፡- *በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ወደ ቴሌቪዥን እንድትሄዱ አዘጋጅቻችኋለሁ። አሁን ወደ ቴሌቪዥን እንድትሄዱ እፈልጋለሁ። አሁን ይህ አገልግሎት ወደ ቴሌቪዥን የሚሸጋገርበት ጊዜ ነው። ሰዎች የሚያስፈልጓቸው መልሶች እናንተ ዘንድ አሉ* አለው። እነዚያ መልሶች ሊኖሩን የቻሉት እግዚአብሔር እነዚያን የዘገምተኛ እድገት ወቅቶች እኛ ለሌሎች የምናካፍላቸውን ነገሮች እንድንማር ስለተጠቀመባቸው ነው።

እኛም ወደ ቴሌቪዥን በተሸጋገርን ጊዜ፣ አገልግሎታችን በሦስት ወራት ውስጥ ሦስት እጥፍ አደገ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጣም በፍጥነት ከማደጉ የተነሣ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን ለመጓዝ መርጥ ግዴታ ሆነብን። አሁን የሠራተኞቻችን ቁጥር በስብሰባዎቼ ይገኙ ከነበሩት ሰዎች የበለጠ ነው። አሁን እኛ ለወደፊቱ ታላቅ ራእይና እቅድ አለን፤ እኔም እግዚአብሔር አገልግሎታችንን በትክክለኛው መንገድና በትክክለኛው ጊዜ እንዳሳደገው በእውነት ለመናገር እችላለሁ። እኔ ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ አበሳጭ የነበርሁ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር በራሱ ትእግስት ስለመራን ደስ ብሎኛል።

እግዚአብሔር እንድታደርጉት የሚፈልገው ምንም ይሁን፣ እርሱ እስኪፈጽመው ድረስ ትእግስት ይኑራችሁ። እርሱ በውስጡ የሚያሳልፋችሁ የትምህርትና የዝግጅት ወቅት ምንም ያህል አዘጋሚ ቢሆን፣ በጉጉት ተቀበሉት። በዐጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገር አትፈልጉ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በራሱ ትክክለኛ ጊዜ እድገትን፣ ስፋትንና ዐዳዲስ እድሎችን በፊታችሁ በማምጣቱ የምታመሰግኑ ሁኑ።

መሰናክልን ማስወገድ ቁጥር 5 :- አለመመቸት

የምንኖረው "ሁሉም በቅጽበት" (ኢንስታንት) በሚል ህብረተሰብ ውስጥ ነው። ሁሉም ነገር ቀላል፣ ምቹና የተዘጋጀ እንዲሆን እንፈልጋለን። ትንሽ የሚሠራ ሥራ ባጋጠመን ጊዜ፣ "እ፣ ወዮልኝ። በጣም ከባድ ነው። በሳህን ማጠቢያው ውስጥ ያሉትን ዕቃዎች በሙሉ ማውጣት አለብኝ" እንላለን። እኔ የሳህን ማጠቢያ መሣሪያ በሌለበት ጊዜ ኖሬአለሁ፤ ስለዚህ ስለ ሳህን ማጠቢያ መሣሪያ (መኪና) ለሚያጉረመርሙ ሰዎች የምሰጣቸው ምክር ቢኖር፣ ሳህኖቹን በእጃችሁ ስለማታጥቡ ምስጋና ይኑራችሁ! ደግሞም እነርሱን ማድረቅ ስለሌለባችሁ አመስግኑ! የሚል ነው። ፎቆችን በጉልበታችን በደረጃ እንዳንወጣ ተንቀሳቃሽ ደረጃና አሳንሰር አለን። የምንወደውን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ማየትን እንዳናጣ ቁልፍ በመጫን ብቻ፣ በሌኮንዶች ውስጥ ምግባችንን እናበስላለን። ድንች እንዳንልጥ፣ እንዳንቀቅልና እንዳንፈጭ የተቆራረጠ ድንች አለን። አንዳንድ ነገሮችን ለማግኘት ከመኪናችን ውስጥ እንዳንወጣ የመስኮቶቹን ቁልፍ በመጫን አውቀው የሚከፈቱ ናቸው። ይህ ቁልፍ በመጫን፣ ያም ቁልፍ በመጫን፣ እንዲሁም ይህ በቅጽበት፣ ያም በቅጽበት የሚገኙ ነገሮች አሉን። እኛ የቀላል ነገርና የምቾት ሱሰኞች ሆነናል።

የእነዚህ ነገሮች ሁሉ አሳዛኝ ጉኑ፣ ምንም እንኳ እነዚህን ነገሮች እንደ "መልካም" ነገር ብንቆጥራቸውም፣ በብዙ መንገድ እኛን የሚጐዱ መሆናቸው ነው። እኛ አስቸጋሪውን መንገድ ብንከተል በውስጣችን አንድ መልካም ነገር የምናገኝ ሆኖ ሳለ እነዚህ ነገሮች ቀላል መውጫ እንድንፈልግ ያደርጉናል። እግዚአብሔር የማያውቀው ምንም ዐይነት እንቅፋት አያጋጥማችሁም። ጉዞአችሁ አስቸጋሪ

በሚሆንበት ጊዜ፣ ምንም እንኳ ዓለም "ቀላሉን መንገድ" ቢመርጥ፣ እግዚአብሔር ለምጹት እንዳልሠራችሁ አስታውሱ። እናንተ ብታውቁትም ባታውቁትም እርሱ ያቀዳችሁና ያስታጠቃችሁ ለመከራ ወቅት ነው። እርሱ ከእናንተ እጅግ መልካም የሆነ ነገር የሚወጣው ከባድ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙአችሁ እንዲሆን አድርጉ ፈጥሮአችኋል፣ እናንተም እነርሱን ስታሸንፉ ደስታና ጥንካሬ ይኖራችኋል።

መሰናክልን ማስወገድ ቁጥር 6፡- ምቀኝነት

ከዓመታት በፊት፣ ዴቭና እኔ ሲጋራ እናጨስ ነበር፣ እግዚአብሔርም እንድንተው እየመከረን ነበር። ሲጋራ ለጤንነታችን ጥሩ ካለመሆኑም በላይ ወጭን የሚያስከትል፣ የሚገማም ልማድ ነበር። ዴቭም ለእግዚአብሔር፣ "እኔ ማጨስን ማቆም እንደሚያስፈልገኝ አውቃለሁ፤ ነገር ግን እንድተው ጸጋህን እስክትሰጠኝ ድረስ ማጨሴን እቀጥላለሁ።" ስለዚህ አልጨነቅም፣ ባንተ እታመናለሁ አለ። በሚቀጥለው ቀን ሲነሣ፣ የማጨስ ፍላጐቱ ጠፋ፣ እስከ ዛሬም ድረስ፣ አንድም ሲጋራ አልፈለገም።

እኔ እንደ ዴቭ በቀላሉ ማጨስን ያቆምሁ ይመስላችኋል? አይደለም! እደግመዋለሁ፣ አይደለም! ገና ብዙ ልሰቃይ ነው! ስፍር ቁጥር የሌለው ብዙ ጊዜ ለመተው ሞክርሁ። እኔ "ለመገላገል" የሞክርኩበት የተደጋገመ ልማድ እንዲህ ነበር፣ ያለ ሲጋራ መቆየት አልቻልሁም፤ ስለዚህ ሄድኩና አንድ ባኮ ሲጋራ ገዛሁ። ከዚያም መተው አለብኝ አልሁና ሲጋራውን ወዲያ ጣልሁት። ቀጥሎም ሲጋራው ወደሚያስፈልገኝ ሁኔታ ደረስኩና ማግኘት አለብኝ ወደሚለው አሳብ ገባሁ፣ የጣልሁትን በሲጋራው መተርኮሻ አካባቢ መፈለግ ጀመርሁ! ከዚያ በኋላ ደግሞ ማጨስ መጥፎ መሆኑ ተሰማኝና እንደገና ሲጋራውን አውጥቼ ወረወርሁት። ከዚያም እንደገና በእኩለ ሌሊት ካለበት ቦታ ፈልጌ አቀጣጥለዋለሁ! እንዲህ ነበርሁ፣ ከምትገምቱት በላይ ከባድ የሆነ የሕሊና ወቀሳ ተሸክሜ ጠዋት ጠዋት ሲጋራ እያቦነንኩ ቀየሁ!

በዚያን ጊዜ፣ ዴቭና እኔ የምናመልከው በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ቤተክርስቲያን ነበር፣ እኔም ወደ መኪና ማቆሚያ ስፍራ ሹልክ ብዬ አሜድና የመኪናዬን መስኮት ወደ ታች አውርጄ በመኪናው ውስጥ ተኝቼ ሲጋራ አጨሳለሁ፣ እኔም የቤተክርስቲያን ጓደኞቻችን የማያውቁ ይመስለኝ ነበር። ነገር ግን በመስኮት ከሚወጣው ጭስ የተነሣ መኪናው በእሳት ተያይዞአል ብለው ሳያስቡ አልቀሩም።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ፣ ዴቭ ከሲጋራ ነፃ የሆነ ሕይወት እየኖረ ነበር። ብዙ ጊዜ፣ "ዴቭ፣ ይህ ከባድ አልሆነብህም እንዴ?" እያልሁ እጠይቀው ነበር። እርሱም "አይ አይደለም፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ከእኔ ጋር ነው" ብሎ ይመልስልኛል።

እኔም በታላቅ ቁጣ ሲጋራ እየፈለግሁ፣ "እሺ፣ የእርሱ ጸጋ ለእኔ የት አለ?!" ብዬ ለመጮህ እፈልግ ነበር። ምናልባት በዚያን ጊዜ እኔ ጸጋውን ለመቀበል በቂ እምነት አልነበረኝም፣ ነገር ግን ችግሩ ምንም ይሁን ምን፣ እኔ ሲጋራ እያጨስሁ ዴቭ በቀላሉ ሊተው በመቻሉ እቆጣ ነበር።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ የምንመኘውን ስኬት እንዳናገኝ የሚከለክለን እንቅፋት ምን እንደሆነ ተረድቼአለሁ፣ እርሱም እግዚአብሔር በሌሎች ሰዎች ሕይወት ስላደረገው ስኬት ያለን የምቀኝነት ዝንባሌ ነው። እኛ እየተሰቃየንና እየታገልን ሌሎች ሰዎች፣ ያለ ጥረት በእኛ አመለካከት፣ ፈጣን ስኬትን ማግኘታቸው ልክ አይደለም ብለን እናስባለን። የምቀኝነትን እንቅፋት ለማስወገድ አንዱ መንገድ፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ያለው እቅድ ፍጹም መልካም መሆኑን አምኖ መቀበል ነው። አንዳንድ ጊዜ ይህ ፍትሐዊ አይመስልም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የሚያደርገውን ያውቃል፣ ወደፊትም በእኛ እንዴት እንደሚጠቀምብን ያውቃል።

የእኔን የሲጋራ ማጨስ ሁኔታ በተመለከተ፣ በብዙ ጸሎትና በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ እንደዚህ አልሁ፣ "ማጨስን አቆማለሁ! በእግዚአብሔር እርዳታ እኔ ማጨስን ላቆም ነው! ምንም ያህል ከባድ ቢሆን ግድ የለኝም፣ እኔ አቆማለሁ!" አልሁ። ከዚያ በኋላ ለአንድ ወር

ያህል በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ አለፍሁና ሁሉም ነገር ተፈጸመ። በመጨረሻም ተሳካልኝ። ከቶ ሊጋራ አላጨስሁም፤ ለማጨስም ፈልጌ አላውቅም።

እግዚአብሔር እኔን እንደ ዴቭ በቀላሉ ለምን አልታደገኝም? እኔ አላውቅም። ነገር ግን አንድ ነገር አውቃለሁ፤ እርሱ ለሌሎች ባደረገው ነገር ምቀኝነት ሳያድርብኝ የእርሱን ጊዜ በእምነት መጠበቅ እንዳለብኝ ተምሬአለሁ።

መሰናክልን ማስወገድ ቁጥር 7፦ ራስ ወዳድነት

ከግባችን እንዳንደርስ የሚከለክለን ሌላው እንቅፋት፤ በተለይ በግል ቦታችንና በነፃነታችን ጉዳይ ራስ ወዳድ የመሆናችን ሐቅ ነው። እኛ ከቶ እጅ ላለመስጠት ታማኞች ለመሆን ከፈለግን፤ የራስ ወዳድነት ፍላጐታችንን ማስወገድ ይኖርብናል። "ራስን" በሚመለከት ረገድ ጽናትና ቁርጠኝነት አስቸጋሪዎች ናቸው። ለመሆኑ፤ እኔ ለአንድ ነገር ቃል ከገባሁና ጊዜው ሲደርስ እርሱን የመፈጸም ስሜት ባያድርብኝ ምን ይሆናል? እኛ ብዙ ጊዜ ነፃነት ማለት የምንፈልገውን ነገር በምንፈልገው ሰዓት ማድረግ ይመስለናል። ነገር ግን ሐቁ፤ ዘወትር በዚህ ዐይነት የምንኖር ከሆነ፤ እያደር በይበልጥ ራስ ወዳድ እንሆንና ራሳችንን ማዕከል የምናደርግ መሆናችን ነው።

እኛ እጅ ላለመስጠት ቁርጠኞች ካልሆንን በስተቀር፤ ዲያብሎስ የራስ ወዳድነት ፍላጐታችንን ተጠቅሞ ማድረግ የሚገባንን ነገር እንዳናደርግ ለመምከር ቀላል ይሆንለታል። ጽናት ስሜታችንን፤ ስሜታችን ምንም ይሁን ምን፤ መቆጣጠርንና ትክክለኛውን ነገር ማድረግን ይጠይቃል።

ነፃነታችንንና ቦታችንን መስዋዕት ማድረግና ለራሳችን ፍላጐት እምቢ ማለት ይኖርብናል። በሥጋችን ልንታመን አንችልም፤ ሥጋችን በአስፈላጊው ጊዜ ወደ አስፈላጊው ስፍራ አያደርሰንም። ሥጋችን ወደፊት መሄድ

ነፃነታችንንና ቦታችንን መስዋዕት ማድረግና ለራሳችን ፍላጐት እምቢ ማለት ይኖርብናል።

ሲገባን እንድንቆም ይፈልጋል። ሥጋችን በእድገታችን መስዋዕትነት - ቦታችንንና ነፃነታችንን ምክንያት በማድረግ ይፈትነናል። ሥጋችን ዐላማችንን መፈጸምንና ወደ ግባችን ለመድረስ ከሚያስከትለው ሥነ ሥርዐት ካለውና መሰጠት ካለበት ሕይወት ይልቅ፤ አሁን መልካም ስሜት ማግኘት የበለጠ ዋጋ ያለው መሆኑን ይነግረናል።

እግዚአብሔር እናንተ ስኬታማ እንድትሆኑ መፈለግ ብቻ ሳይሆን፤ ስኬታማ እንድትሆኑ ፈጥሮአችኋል። እናም ከዚህ ባነሰ ሁኔታ ላይ ረክታችሁ እንድትቀመጡ አይፈልግም። ውድቀቶች ወይም ስህተቶች ተሸናፊ እንዲያደርጉአችሁ አትፍቀዱላቸው፤ ይልቅስ ወደፊት የምትሸሹአቸውን ነገሮች እንዲያስተምሩአችሁ አድርጓቸው። ወደ ስኬት በምትጓዙበት ጊዜ እግዚአብሔርን ተጠባበቁና ጎይላችሁን እንዲያድሰው አድርጉ። ስኬት በቀላሉ አይመጣም፤ ነገር ግን፤ እናንተ ከጸናችሁ፤ ይመጣል።